# አማርኛ

## (እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ)

## የተማሪ መጽሐፍ

## 7ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ የተሰማማ


**አስማምቶ አዘጋጆች፡-** እንግዳ ዘውዴ (ዶ/ር)

አወቀ ፀጋዬ

ይኄይስ ባንታየሁ

**አርታኢ፡-** እንግዳወርቅ እንድርያስ

**ሌያውት ዲዛይን፡-** ኃይለማርያም መለሰ



የደ/ብ/ብ//ሕ/ክ/መ ትምህርት ቢሮ

# © የቅጂ መብት

ይህ መጽሐፍ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት በኩል በተገኘ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ ተዘጋጅቶ አጠቃላይ የሕትመት ወጪው በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ተሸፍኗል፡፡

የመጽሃፉ ሕጋዊ ቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም የደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ነው::

# ማውጫ

መግቢያ ........................................ ii

## ምዕራፍአንድ ........................................ 1

ተፈጥሮን ማድነቅ ........................................ 1

## ምዕራፍ አንድ ........................................ 11

ተፈጥሮን ማድነቅ ........................................ 11

## ምዕራፍ ሶስት ........................................ 21

በጎ ፈቃደኝነት ........................................ 21

## ምዕራፍ አራት ........................................ 31

የታዋቂ ሰዎች የሕይወት ታሪክ ........................................ 31

## ምዕራፍ አምስት ........................................ 42

ውሃና ጥቅሙ ........................................ 42

## ምዕራፍ ስድስት ........................................ 55

የሰዎች ሕገ ወጥ ዝውውር ........................................ 55

## ምዕራፍ ሰባት ........................................ 68

ማኅበራዊ ግንኙነት ........................................ 68

## ምዕራፍ ስምንት ........................................ 79

ሱስ ........................................ 79

## ምዕራፍ ዘጠኝ ........................................ 90

የሀገር ፍቅር ........................................ 90

## ምዕራፍ አስር ........................................ 100

የቃል ግጥም ........................................ 100

ዋቢ ጽሑፎች ........................................ 114

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ አማርኛን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በቋንቋው በብቃት ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ እንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላት፣ የሰዋስው እና የሥነጽሑፍ ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው። በተጨማሪም መጽሐፉ በዚህ ስለሚሰጡ ትምህርቶች ሽፋን መረጃ ይሰጣል። በመሆኑም ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## መሰረታዊ መርሆዎች

- ተማሪዎች በማኅበረሰቡ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ስልቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ።
- ተማሪዎች ስለእነዚህ የማዳመጥ ስልቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ከአዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ይናገራሉ።
- በቀጣይም በማኅበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ። ስለእነዚህ የምንባብ ይዘቶች የተጻፉ ምንባቦችን ከአነበቡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ጽሑፍ ይጽፋሉ።
- አራቱን ክሂሎች ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተማሩ በኋላ በክፍል አምስት፣ ስድስትና ሰባት የቀረቡትን የቃላት፣ የሰዋስውና የሥነጽሑፍ ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ።
- ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር በመተባበር ይማራሉ።

## በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ፡፡ ስለዚህ ወላጆች ከእነዚህ በርካታ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል፡፡

1. የእለቱን የትምህርት ይዘት በተመለከተ ከቴሌቪዥን፣ ከሬዲዮ ወይም ከድረገጽ ስለርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ፡፡
2. ልጆች የተሰጣቸውን የቤትሥራ ሲሠሩ፣ ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለ-መጠይቅ፣ ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው፡፡
3. ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ፡፡ በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ፡፡ ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፡፡
4. ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፡፡
5. ስለ-ርዕሰጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሑፎችን ከመጻሕፍት፣ ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ፡፡
6. በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)፤ ከዚያም ስለአነበቡት ጉዳይ ተወያዩ፡፡
7. ልጆች በክፍል ውስጥ ምን ምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ተወያዩ፡፡
8. የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው፡፡ ለምሳሌ፡- የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ ተሰድረዋል ወይ? በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ/መካከል/ ያሉት ሥርዓተነጥቦች (አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል ወይ? ወዘተ.
9. ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለአንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ. እንዲጽፉ አበረታቷቸው፡፡

# ምዕራፍ አንድ ፩

# ተፈጥሮን ማድነቅ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሌሎችን ሀሳብ ታዳምጣላችሁ
- ስለ ተፈጥሮ ምንነት ትወያያላችሁ፡፡
- ለክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ጽሑፍ ታነባላችሁ፡፡
- የተፈጥሮን የተለያዩ ገፅታ ትለያለችሁ፡፡
- አንቀፅ ትፅፋላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ





"ዓባይ"

## ድመ ማዳመጥ

1. ስለ ተፈጥሮ ምን ታውቃላችሁ?
2. ስለ ወንዞች አጠቃቀም የምታውቁትን በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን የጋራ ድምዳሜ ተራ በተራ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡
3. ከላይ ከቀረቡት ስእሎች ምን ተረዳችሁ?

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ፡-

አባይ በሚል ርእስ የቀረበውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ በመጻፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

“የአባይ ወንዝ እና የህዳሴው ግድብ” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የህዳሴው ግድብ በየትኛው ክልል ይገኛል?
   - ሀ. ሶማሌ
   - ለ. አማራ
   - ሐ. ደቡብ
   - መ.ቤኒሻንጉል ጉሙዝ
2. ህዳሴ ግድቡ የግርጌ ውፍረት ስንት ሜትር ነው?
   - ሀ. 120 ሜትር
   - ለ. 135 ሜትር
   - ሐ. 130 ሜትር
   - መ. 125 ሜትር
3. አባይን በተመለከተ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   - ሀ. ከዓለማችን ረጃጅም ወንዞች አንዱ ነው፡፡
   - ለ. የአንድ ሀገር ብቻ ተፋሰስ ነው፡፡
   - ሐ. የግድቡ ከፍታ 145 ሜትር ነው፡፡
   - መ. አባይ 6696 ኪ.ሜትር ርዝመት አለው፡፡

4. በአዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የአባይ ወንዝ የተነፃፀረው ከየትኛው ወንዝ ጋር ነው?
   ሀ. ከአማዞን
   ለ. ከአዋሽ
   ሐ. ከተከዜ
   መ. ከዛየር
5. የህዳሴው ግድብ ሲጠናቀቅ ስንት ሜጋ ዋት ያመነጫል?
   ሀ. 5200 ለ. 6450 ሐ. 5000 መ. 6000

**መልመጃ ሁለት፡-**

ከአዳመጣችሁት ምንባብ ለወጡ የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የህዳሴው ግድብ ተገንብቶ ሲያልቅ ለሀገር እድገት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል፡፡
2. የመኖሪያ ቤታችን የኤሌክትሪክ ፍጆታ እየጨመረ ነው፡፡
3. በትምህርቴ ጥሩ ውጤት የማምጣት ውጥን አለኝ፡፡
4. ነገ ደመና እንደሚኖርና ዝናብ እንደሚጥል ተተንብይዋል፡፡
5. የአስፓልት መንገዱ እንዳይበላሽ የመንገድ ዳር ተፋሰስ ሊሰራለት ይገባል፡፡
6. የህዳሴው ግድብ ከፍታ 145 ሜትር ነው፡፡
7. የአባይ ወንዝ በዓለም ላይ ካሉ ረጃጅም ወንዞች በግንባር ቀደምነት ተጠቃሽ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

**መልመጃ አንድ፡-**

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ የንግግር መመሪያ መሰረት ታላቁ የህዳሴ ግድብ መገንባቱ ለሀገር ልማት ምን ጥቅም እንደሚሰጥ በቡድን ተወያዩ፡፡ ከውይይቱም በኋላ ከየቡድናችሁ አንድ አንድ ሰው በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

በተግባር አንድ በአቀረባችሁት ንግግር መሰረት እርስ በእርስ አስተያየት ተሰጣጡ፡፡ አስተያየታችሁ በቋንቋ አጠቃቀምና ሀሳብ አገላለጽ ዙሪያ የሚያነጣጥር ይሁን፡፡

## ክፍል ሶስት፡- አንብቦ መረዳት

"የደቡብ የተፈጥሮ ገፀ-በረከት- ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ"




### ቅድመ ንባብ

1. ተማሪዎች ለሽርሽር የተለያዩ ቦታዎችን ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ? ካወቃችሁ የትና መቼ?
2. የተፈጥሮ መስህብ ማለት ምን ማለት ነው? ከሰው ሰራሽ መስህቦችስ በምን ይለያል
3. በደቡብ ክልል ምን ምን አይነት የተፈጥሮ መስህቦች የሚገኙ ይመስላችኋል? የምታውቋቸውን መስህቦች ስም ጥቀሱ፡፡

### ጊዜ ንባብ

#### ትዕዛዝ፡-

"የደቡብ የተፈጥሮ ገፀ-በረከት- ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ" የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ በየመሀሉ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል እየሰጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

### "የደቡብ የተፈጥሮ ገፀ-በረከት- ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ"

የነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ በአርባ ምንጭ ከተማ አቅራቢያ በአባያና ጫሞ ሀይቆች መካከል ይገኛል፡፡ አባያና ጫሞን ከሚከፍለው የመሬት ሽንተረር ከከተማይቱ በስተምስራቅ በኩል ከነጭ ሳር ጋር ሁለቱንም ሀይቆች እና ግዙፍ ምእራባዊ ተራሮችን ጨምሮ በዙሪያቸው ለእይታ የሚማርክ ገጽታ ያለው ስፍራ ነው፡፡ በሁለቱ ሀይቆች መሀል ያለው ከፍታ መሬት የእግዜር ድልድይ

በመባል ይጠራል። አርባ ምንጭ-አርባ ምንጮች ከከተማው በታች ካለው ጫካ የከርሰ ምድር ውስጥ ከሚፈልቁትና ከሚፈሱት ጅረቶች ስሙን ይወስዳል። ይህ ማራኪ ስፍራ በኢትዮጵያ ከሚገኙ የዱር አራዊት መገኛ ስፍራዎች ታላላቅ የዱር አራዊት የሚኖሩበት ፓርክ ተድርጎ ይቆጠራል።

## ከላይ ከቀረበው አንቀጽ ስለ ነጭ ሳር ፓርክ ገጽታ ምን ተረዳችሁ? የተረዳችሁትን ለመምህራችሁ በቃል ንገሩ።

514 ካሬ ኪሎ ሜትር በሚሸፍነው የፓርኩ ክልል የተለያዩ እንሰሳት ይኖራሉ። ከነዚህም መካከል የሜዳ አህዮች በሳቫና እና በደረቅ ቁጥቋጦዎች አካባቢ ይኖራሉ። በጫካው ውስጥ ደግሞ 188 የተመዘገቡ የአእዋፍ ዝርያዎች ይኖራሉ። በጎብኚዎች መታየት ካለባቸው ብርቅዬ የዱር እንሰሳት ድኩላዎች፣አጋዘኖች፣የሜዳ አህዮች፣ ኩዱዎች፣ዝንጀሮዎች በየብስ የፓርኩ ክፍል ሲገኙ አዞዎች በሀይቆቹ ውሀ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። ከአእዋፍ ዝርያዎች ደግሞ በቀይ የተከፈለ ቀንደ ቢል፣ ግራጫ ሆርን ቢል፣ንስር፣ቡስተርድ፣ እና አቢሲኒያ መሬት ቀንደ ቢል ይገኙበታል። ስፍራውን ተራሮች እና የተራሮች ዳራ ተጣምረው በጣም ማራኪ ያደርጉታል።

ከነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ በስተሰሜን በኩል የአባያ ሀይቅ ገጽታ በውሃው ውስጥ ባለው የከርሰ ምድር ሀይድሮክሳይድ ጭነት ምክንያት የጨለመ ቀይ አስገራሚ ንጽጽር ይፈጥራል። በስረኛው መሰረት በኩልፎ ወንዝ ዙሪያ ሰፊ የከርሰ ምድር ጫካ እንዲሁም አርባ ምንጮች አርባ ምንጭ ከተማ የተሰየመበት ውብ የፓርኩ ገጽታዎች ናቸው። የስምጥ ሸለቆው ምእራባዊ ጠርዝ ወደ ምእራብ አስደናቂ ዳራ ያጎናጽፈዋል።

በመጀመሪያ እይታ በሁለቱ ሀይቆች መካከል ያለውን ባህረ ገብ መሬት ሲለቁ የሚያጋጥሙት የነጭ ሳር ሜዳዎች በሚያስደንቅ ሁኔታ ባዶ ይመስላሉ። ነገር ግን ይህ ማለቂያ የሌለው ወርቃማ ነጭ ሳር የአጋዘን፣ የሜዳ አህያና የአጋዘን መንጋዎች በስፋት ይገኙበታል።

በውሃማው የፓርኩ ክፍል አዞዎች እና አሳዎች በብዛት ይገኙበታል። የዓባይ ፐርች እየተባለ የሚጠራው የአሳ ዝርያ 100 ኪሎ እንደሚመዝን ይነገራል።

(ከኢትዮ ቪዥን ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት መልመጃዎች

### መልመጃ አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. በነጭ ሳር ፓርክ ውስጥ ስንት የአዕዋፍ ዝርያዎች ይገኛሉ?
2. የፓርኩን ገጽታ ማራኪ ያደረጉት የተፈጥሮ መስህቦች ምን ምን ናቸው? ጥቀሷቸው፡፡
3. በፓርኩ ከሚገኙ አጥቢ እንስሳት መካከል አራቱን ጥቀሱ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

የሚከተሉት አረፍተ ነገሮች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት፣ ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡ ሀሰት ለሆኑት የማስተካከያ አስተያየት አቅርቡ፡፡

1. ነጭ ሳር ፓርክ ነጭ የተባለው ከአባያ ሀይቅ የውሀ መልክ በመነሳት ነው፡፡
2. በነጭ ሳር ፓርክ የየብስ እንጂ የውሀ ውስጥ እንሰሳት የሉም፡፡
3. በነጭ ሳር ፓርክ ውስጥ ስጋ በል የሆኑ እንሰሳት የሉም፡፡
4. ነጭ ሳር ብ ስራ ነው የተባለው በውስጡ በሚኖሩት እንሰሳት አይነትና ብዛት ነው፡፡
5. ፓርኩን በየአመቱ በርካታ አገር ጎብኚዎች ይጎበኙታል፡፡

### መልመጃ ሦስት፡-

ለሚከተሉት ቃላት እና ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ሸንተረር
ለ. ከርሰ ምድር
ሐ. ማራኪ
መ. ብርቅዬ
ሠ. ዳራ
ረ. ባህረ ገብ
ሰ. ማለቂያ የሌለው

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

**አንቀፅ**

የአንቀፅ ምንነት፡- አንቀፅ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ የሚብራራበት አነስተኛ የድርሰት አካል ነው፡፡ አንቀፅ የዓረፍተ ነገሮች ድምር ውጤት ነው፡፡ በአንድ አንቀፅ ውስጥ ሁለት ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡-

1. ሀይለ ቃል፡- የአንቀፁን አጠቃላይ ሀሳብ ጠቅልሎ የሚይዝ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡
2. ዝርዝር አረፍተ ነገሮች፡- በሀይለ-ቃሉ ላይ የቀረበውን ሀሳብ በዝርዝር የሚያብራሩ ዓረፍተ ነገር ናቸው፡፡ ምሳሌውን ከማስታወሻው በታች ይመልከቱ

**ምሳሌ፡-**

<u>ብቸኝነት ጣጣው ብዙ ነው</u>፡፡ ሰው ማህበራዊ ፍጡር በመሆኑ ከብቸኝነት መራቅ አለበት፡፡ አለበለዚያ የብቸኝነት ኑሮ ለሚያስከትላቸው ችግሮች ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ብቸኛ ሰው የሚያነጋግረውን ፍለጋ መዋተቱ አይቀሬ ነው፡፡ ብቸኝነትን ለመሸሽ ሲባል ወደ ተለያዩ ሱሶች ሊገባ ይችላል፡፡ ነጋ ጠባ መበሳጨትና ራስን መጣልም የብቸኝነት መዘዞች ናቸው፡፡

ከላይ በቀረበው አንቀፅ ውስጥ የተሰመረበት የአንቀፁ ሀይለቃል ሲሆን ሌሎቹ አምስት ዓረፍተ ነገሮች ሀይለ-ቃሉን የሚያብራሩ መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡


የአንቀፅ ቅርፅ፡- የአንድ አንቀፅ ቅርፅ የሚወሰነው ሀይለ-ቃሉ በሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ እነሱም፡-

1. ሀይለቃሉ መጀመሪያ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 
2. ሀይለቃሉ መሀል ላይ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መሀል ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 

3. ሀይለቃሉ መጨረሻ ላይ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መጨረሻ ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 
4. ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ሲመጣ፡- ሀይለ-ቃሉ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ሲመጣ የአንቀፁ ቅርፅ ይሄን ይመስላል፡፡ 

**መልመጃ አንድ፡-**

ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ከታች የቀረበላችሁን ቢጋር በመከተል "ቱሪዝም" በሚለው ርዕስ ሁለት አንቀፅ ጻፉ፡፡




**መልመጃ ሁለት፡-**

ተማሪዎች "ቱሪዝም" በሚል ርዕስ የፃፋችሁትን አንቀፅ በቡድን በመሆን እርስ በእርስ ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት

**ማስታወሻ**

**ተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት**

ቃላት ማለት በስርዓት የተሰደሩ ፊደላት ስብስብ ነው፡፡ ቃላትን ተዘውታሪና ያልተዘወተሩ (አዳዲስ ቃላት) ብለን መክፈል እንችላለን፡፡

1.ተዘውታሪ ቃላት፡- በእለት ተዕለት ኑሯችን በተደጋጋሚ የምንጠቀማቸው ቃላት ናቸው፡፡ ምሳሌ፡- በላ፣ ልብስ፣ ምግብ … የመሳሰሉት ናቸው፡፡

2.ያልተዘወተሩ፡- በእለት ተዕለት ኑሯችን ውስጥ አልፎ አልፎ የምንጠቀማቸው እንግዳ የሆኑ ቃላት ናቸው፡፡ ምሳሌ፡- ተግዳሮት፣ ጥቁር እንግዳ… የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## መልመጃ አንድ፡-

ከዚህ በታች በቀረቡት ዓ. ነገሮች ውስጥ የሚገኙትን ተዘውታሪ እና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን በመለየት ፃፉ፡፡

1. የኤርሚያስን ሙግት አልቻልኩትም፡፡
2. ለገና ዋዜማ እመጣለሁ ብሎኛል፡፡
3. አቶ ሙሳ ሰርክ ወደ መስጊድ ይመላለሳሉ፡፡
4. "በአዘቦት ቀን እመጣለሁ" ብሎ እስካሁን የውሃ ሽታ ሆነ፡፡
5. ባረጋ ኳሷን ወደ ሰማይ አጎናት፡፡
6. ወደ ስራ ለመሄድ ሥነሳ ጥቁር እንግዳ መጣብኝ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ቢያንስ አምስት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

# ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

## መልመጃ አንድ፡-

መምህራችሁ በሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ በማለት ለዩ፡፡

1. የክረምቱ ዝናብ ከቤት አያስወጣም፡፡
2. አባቴ ከመጣ ሽርሽር ይወስደኛል፡፡
3. ህፃናት ከአቅማቸው በላይ ስራ መስራት የለባቸውም፡፡
4. ፈተና ስለደረሰ በርትተን እናጥና፡፡
5. የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር በፈተናው ዙሪያ ማብራሪያ ሰጡ፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

ከላይ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች መሰረት አምስት ነጠላ እና አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ የንግግር መመሪያ፣ ስለአንቀጽ ምንነት፣ ስለተዘውታሪና ተዘውታሪ ያልሆኑ ቃላት፣ እንዲሁም ስለነጠላና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ተምረናል፡፡
- ንግግር በዝግጅት ወይም ያለ ዝግጅት ሊቀርብ የሚችልና ሀሳብ አፍልቀን ለሌሎች የምናስተላልፍበት ክሂል ነው፡፡ በዝግጅት ሲቀርብ መረጃ ተሰብስቦ እና ማስታወሻ ተዘገጅቶ ተናገሪው ማስታወሻውን እያየ ሀሳቡን የሚያቀርብበት መንገድ ሲሆን ያለዝግጅት ደግሞ ያለ ማስታወሻ የመጣለትን ሀሳብ እያፈለቀ የሚናገርበት ስልት ነው፡፡ አቀራረቡ ጥንቃቄን የሚፈልግ ነው፡፡
- አንቀፅ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ የሚተላለፍበት የድርሰት አነስተኛ አካል ነው፡፡ አንቀፅ የዓረፍተ ነገሮች ድምር ውጤት ሲሆን በአንድ አንቀፅ ውስጥ ሁለት ዓይነት ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡- ሀይለቃልና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡
- ቃል ማለት በስርዓት የተሰደሩ ፊደላት ስብስብ ሲሆን ቃላትን ተዘውታሪና ያልተዘወተሩ (አዳዲስ ቃላት) ብለን መክፈል እንችላለን፡፡
- ዓረፍተ ነገሮች ከመዋቅር (ከቅርፅ) አንጻር ነጠላ እና ውስብስብ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ስለ ተፈጥሮ ማድነቅ ምን እንደተረዳችሁ ተናገሩ፡፡
2. የአንድን አንቀፅ ቅርፅ የሚወሥነው ምንድን ነው?
3. የሀይለ ቃል እና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮችን ልዩነት ተናገሩ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት ፪

# የቤተሰብ እቅድ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-


- የሚነበብላችሁን ምንባብ በጥሞና አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቡን በቃል ትገልጻላችሁ፡፡
- በቤተሰብ እቅድ ምንነት ላይ ትወያያላችሁ፡፡
- ቀላል ሁነቶችን አጥንታችሁ በቃል ትተርካላችሁ፡፡
- የቤተሰብ እቅድን መሰረት አድርገው በሚሰጡ አስተያየቶች ላይ የተለያዩ መረጃዎችን በማቅረብ ትከራከራላችሁ፡፡
- ስዕሎችን ተመልክታችሁ የሚያስተላልፉትን መረጃ ታብራራላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

“ ልጅ በእድሉ ያድጋል?”





## ቅድመ ማዳመጥ

1. የቤተሰብ ምጣኔ ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምን ማለት ነው?
2. ልጅ በእድሉ ያድጋል በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ?
3. ከላይ ከቀረበው ስዕል ምን ተረዳችሁ?

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ፡-

“ልጅ በእድሉ ያድጋል” የሚለውን የማዳመጥ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመያዝ በንቃት አዳምጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

“ልጅ በእድሉ ያድጋል” በሚል ርዕስ በአዳመጣችሁት ጽሑፍ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. የእነ ህብስት ቤተሰብ ብዛት ስንት ነው?
2. “የሚላስ የሚቀመስ” ከቤት ጠፋ በሚል የቀረበው ሀሳብ ምንን ይገልፃል?
3. የህብስት ትዳር ሰላም ያጣው በምን ምክንያት ነው?
4. የነዘምዘም ቤተሰብ በሰላም እና በፍቅር የተሞላው በምን ምክንያት ነው?
5. የጥሩ ጓደኝነት ተምሳሌት ናቸው፡፡ ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ምን ጠቀሜታ አለው?

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ቁልፍ ቃላት እና ሀረጋት ከታች በቀረቡት ያልተሟሉ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ደፋ ቀና | የዕለት ጉርስ | ዶሮ ሳይጮህ |
| የበኩር | ባልደረባ | ባልንጀራ |

1. አልማዝ የበቀለ ________________ ልጅ ነች፡፡
2. መገርሳ የዕለት ኑሮውን ለማሻሻል____________________ይላል፡፡
3. ____________-ከቤት የወጣ ጀምበር እስክትጠልቅ አልተመለሰም፡፡

4. የመስሪያ ቤቱ የስራ ____________የሆነው አቶ ሀሰን ከመኪና አደጋ ለጥቂት ተረፈ፡፡
5. ለተሰንበት የዘቢባ ______________ነች፡፡

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ትዕዛዝ፡-

1. ከታች የቀረበውን ቢጋር መሰረት በማድረግ የሁነቶችን ቅደም ተከተል በመጠበቅ አጭር ንግግር አድርጉ፡፡

የቤተሰብ እቅድ አለመጠቀም → በቤተሰብ ውስጥ ሰላምና ፍቅር መጥፋት → የትዳር መፍረስ → የልጆች መበተን

2. የቤተሰብ ምጣኔን በተመለከተ “ልጅ በእድሉ ያድጋል” የሚለውን ሀሳብ በመደገፍ ወይም በመቃወም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ክርክር አድርጉ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### “የቤተሰብ እቅድ”



### ቅድመ ንባብ

1. የሥነ-ተዋልዶ አገልግሎት ምንድን ነው?
2. “ልጅ ሀብት ነው” በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? ምክንያታችሁን

በቃል ግለፁ

3. በአካባቢያችሁ የሥነ-ተዋልዶ አገልግሎት ይሰጣል?

## ጊዜ ንባብ

**መልመጃ አንድ፡-**

“የቤተሰብ እቅድ” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

### “የቤተሰብ እቅድ”

የሴቶችን መብት ማረጋገጥ ለልማት ያለው አበርክቶ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ እ.ኤ.አ በ1994 በካይሮ ላይ የተደረገው ዓለም አቀፍ የሥነ-ህዝብ እና ልማት ጉባኤ ከፍተኛ መነቃቃትን ፈጥሯል፡፡ በወቅቱ የሥነ-ተዋልዶ ጤናን ማስፋፋት እና የፆታ እኩልነትን ማስፈን የአንድ ሀገር የልማት እንብርት ተደርጎ መወሰዱ የጉባኤው ስኬት ነበር፡፡ ከጉባኤው ሩብ ምዕተ ዓመት በኋላ ዓለም ፈጣን እድገት ያስመዘገበች ሲሆን በዓለም ደረጃ የእርግዝና መከላከያ አቅርቦት በ25 በመቶ እድገት አሳይቷል፡ ፡ የእናቶች እና የህጻናት ሞትም በከፍተኛ ደረጃ መቀነሱን የተባበሩት መንግስታት የሥነ-ህዝብ መረጃ ያመለክታል፡፡

እ.ኤ.አ በ2019 በዓለም ዙሪያ 1.9 ቢሊዮን እድሜያቸው ከ15-49 ዓመት በመውለድ እድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች መካከል 1.1 ቢሊዮን የሚሆኑት ሴቶች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት የመጠቀም ፍላጎት አላቸው፡፡ ከነዚህ ውስጥ 842 ሚሊዮን የሚሆኑት የእርግዝና መከላከያዎችን እየተጠቀሙ ሲሆን 270 ሚሊዮን የሚሆኑት ደግሞ የእርግዝና መከላከያ እየፈለጉ አገልግሎቱን ያላገኙ ናቸው፡፡

*ከላይ በቀረበው ምንባብ የተጠቀሱ ቁጥራዊ መረጃዎች ምን ምን ናቸው? ሁኔታው በሀገራችንስ ምን የሚመስል ይመስላችኋል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ እ.ኤ.አ በ2019 በተጠና ጥናት መሰረት ማንኛውንም አይነት ዘመናዊ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ምጣኔ እ.ኤ.አ በ2005 ከነበረበት 14% በ2019 ወደ 41% አድጓል፡፡ ሆኖም ባለፉት 5 ዓመታት በወቅቱ ከነበሩት እርግዝናዎች መካከል 17% የሚሆኑት ያልታቀዱ ነበሩ፡፡ ይባስ ብሎ እድሜያቸው ከ18-19 ከሆኑ አፍላ ወጣት ሴቶች መካከል 10% የሚሆኑት በለጋነት እድሜያቸው የልጅ እናት የሆኑ ሲሆኑ 2% የሚሆኑት ደግሞ በጥናቱ ወቅት የመጀመሪያ ልጃቸውን አርግዘው ተገኝተዋል፡፡

የሀገራችን የሥነ-ህዝብ ፖሊሲ እና የሥነ-ተዋልዶ ጤና እስትራቴጂ ሁሉም ሰዎች በተለይ እናቶች እና አፍላ ወጣቶች የእርግዝና መከላከያ ዘዴ ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ በርካታ የሰብዓዊ መብቶችን፣ የሕይወት እና የነጻነት፣ የአመለካከት እና ሀሳብን የመግለፅ እንዲሁም የመስራት እና የመማር መብትን ብሎም ከፍተኛ የጤና እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ያትታል፡፡ የእርግዝና መከላከያ መጠቀም ከእርግዝና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የጤና አደጋዎችን በሴቶች በተለይም በአፍላ ወጣት ሴት ልጆች ላይ እንዳይከሰት ይከላከላል፡፡

በልጆች መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት ባነሰ ጊዜ የሚለያይ ከሆነ የህጻናት ሞት መጠን የዕድሜ ልዩነታቸው ከ2-3 ዓመት ከሆኑት ጋር ሲነፃፀር በ45 ከመቶ ከፍ ያለ ሲሆን በአራት ወይም ከዚያ በላይ ዓመታት ከሚለያዩት ጋር ሲነጻፀር ደግሞ በ60 በመቶ ከፍ ይላል፡፡ የትምህርት እድሎችን ለማስፋፋት እና ለሴቶች አቅም መጎልበት እንዲሁም ለሀገራችን ዘላቂ የህዝብ እድገት እና ኢኮኖሚያዊ ልማት የቤተሰብ እቅድ አገልግሎት ፍቱን መድኃኒት ሲሆን በርካታ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡

የሥነ-ተዋልዶ ጤና ከቤተሰብ እቅድ አገልግሎት በተጨማሪ የተሟላ የዕናቶች እና የሕጻናት ጤና አገልግሎትን ማዳረስን፣ የአፍላ ወጣቶችን ጤና፣ ኤች አይቪን ጨምሮ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን መከላከል እና ማከምን፣የመካንነት ችግርን መለየት እና ማከምን፣ የማህፀን ጫፍ ካንሰር ልየታ እና ህክምናን፣ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን መከላከልን እና ተጎጅዎችን ማከምን ብሎም ሌሎች ወሳኝ አገልግቶችን የሚያጠቃልል የጤና አገልግሎት ቢሆንም ስር የሰደዱ የተዛቡ አመለካከቶች እና መሰረተ ቢስ አሉቧልታዎች ህዝባችን አገልግሎቶቹን በአግባቡ እንዳይጠቀም ማነቆ ሆነውበታል፡፡

ምንጭ፡- (ወይ አዲስ አበባ መጽሔት፣ቅፅ 1፣ቁጥር 8፣2013 ዓ.ም)

## ድህረ ንባብ

**መልመጃ አንድ፡-**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. እ.ኤ.አ በ2019 በዓለም ዙሪያ የእርግዝና መከላከያ እየፈለጉ አገልግሎቱን ያላገኙ ሴቶች ምን ያህል ናቸው?
2. በሥነ-ተዋልዶ ውስጥ ምን ምን አገልግሎት ይሰጣል?

3. በሀገራችን ኢትዮጵያ የእርግዝና መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ምጣኔ እ.ኤ.አ በ2019 በስንት በመቶ ከፍ አለ?
4. እ.ኤ.አ በዓለም እድሜያቸው ከ15-49 ዓመት የሆኑ ሴቶች ብዛት ስንት ነበር?
5. የምንባቡን ዋና መልዕክት አጠር አድርጋችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ?

## መልመጃ ሁለት:-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ አውድ መሰረት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ::

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1 | ፍቱን | ሀ. | ያልተረጋገጠ መረጃ |
| 2 | አሉባልታ | ለ. | የተስፋፋ |
| 3 | ማነቆ | ሐ. | ችግር |
| 4 | እንብርት | መ. | ማሳደግ |
| 5 | ስር የሰደደ | ሠ. | ወጥመድ |
| 6 | ማጎልበት | ረ. | ሃያ አምስት ዓመት |
| 7 | ሩብ ምዕተ-ዓመት | ሰ. | ወሳኝ |
| | | ሸ. | መሰረት |

## መልመጃ ሶስት:-

ከላይ የቀረበውን ምንባብ በየተራ እየወጣችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡ::

## መልመጃ አራት:-

**ተማሪዎች ከታች የቀረበውን ስዕል መሰረት በማድረግ የተረዳችሁትን መልዕክት የሀሳብ ፍሰቱን ጠብቃችሁ ሁለት አንቀፅ ፃፉ::**



## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

### ኢ-መደበኛ ጽሑፍ

ጽሑፍ በአጠቃቀም ጊዜ ሁለት መልኮች አሉት፡፡ እነሱም፡-

1. መደበኛ ጽሑፍ፡- ይህ የጽሑፍ አይነት በመስሪያ ቤቶች፣ በመጽሄቶች፣ በጋዜጦች ፣ በሬድዮ ዝግጅቶች በትምህርት ቤቶች በሌሎችም ማኅበራዊ መስኮች የምንጠቀምበት የጽሑፍ አይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- አባቴ ትናንት ማታ ደውሎልኝ በጣም ተገርሜ ነበር፡፡ ወዲያው ወደ ክፍል እንደገባሁ የክፍል ጓደኞቼ ዛሬኮ ልደትሽ ነው ብለው ይበልጥ አስገረሙኝ፡፡ ምን አይነት ተዓምር ነው!

2. ኢ-መደበኛ ጽሑፍ ለሀሳብ ቅደም ተከተሉ፣ ለድምፀቱ መለዋወጥ፣ ለሰዋስዋዊ ቅንብሩ፣ ለቃላት መረጣው፣ እምብዛም ጥንቃቄ የማያደርግ የጽሑፍ አይነት ነው፡፡ ምሳሌ፡-

   ሀ. ፋዘር ትናንት ማታ ደውሎልኝ በጣም ሰርፕራይዝ አድርጎኝ ነበር፡፡ ወዲያው ወደ ክላስ እንደገባሁ ክላስ ሜቶቼ ዛሬኮ በርዝደይሽ ነው ብለው ይበልጥ ሰርፕራይዝ አደረጉኝ፡፡ አሜዚነግ ነው!

   ለ. ባሌላ ለመግዛት ተገበያ ሄጄ፣ ጀምበሪቱ አናት አናቴን ወቅጣኝ የራስ ህመሜን ቀሰቀሰችብኝ፡፡ እንዲሁ ስደናበር ተቤቱ ልደርስ ጥኢት ሲኸረኝ ዝናቡ መዓቱን ለኸኸብኝ፡፡

   ሐ. አባቴ ከች ሲል ሀርድ ሊበጥስብኝ መስሎኝ ከቤታችን ጓዳ አንድ ጥግ ላይ ሻግ አልኩኝ፡፡ ሲስተር ልታስፎግረኝ መስሎኝ ኸረ ሙድ የለውም አልኳት፡፡

**መልመጃ አንድ፦**

ከላይ የቀረበው ማስታወሻ ውስጥ ያሉትን አንቀጾች መሰረት በማድረግ ባለ ሶስት አንቀፅ ኢ-መደበኛ ጽሑፍ ጻፉ።

**መልመጃ ሁለት፦**

የፃፋችሁትን አንቀፅ መሰረት በማድረግ ከጓደኞቻችሁ ጋር እርስ በእርስ ተራረሙ።

## ክፍል አምስት፦ ቃላት

### የቃላት አውዳዊ ፍች

### ትዕዛዝ

ቀጥሎ የቀረበውን አንቀጽ በማንበብ በምንባቡ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ።

ኃይሉ ከስኬት ይደርስበታል የተባለው ስራ ውጤት አልባ ሆኗል። ይህ ክፉ አጋጣሚ ደግሞ ለቤተሰቦቹ እና ለእርሱ ተስፋ የሚያስቀርጥ መሆኑ አልቀረም። ውሎ አድሮ አብረውት ይሰሩ የነበሩ ጓደኞቹ ከጥሩ ደረጃ ደረሱ። ሀይሉ ግን ስራውን የማሻሻል እድል ሳያገኝ ቀረ።

ሀ. ስኬት____________________
ለ. አልባ _______________
ሐ. ውሎ አድሮ_______________
መ. ደረጃ ____________________
ሠ. እድል ____________________

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### የአሁን ጊዜ

#### ማስታወሻ

ጊዜ የኃላፊ፣ የአሁን እና የትንቢት (የወደፊት) ተብሎ በሶስት ይከፈላል፡፡ የአሁን ጊዜ የሚባለው አንድ በአሁን ሰዓት የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው፡፡ አሁን የሚባለው አንድ ሰው ስለአንድ ድርጊት ንግግር የሚያደርግበት ጊዜ ነው፡፡ የአሁን ጊዜ የሆነ ግስ እየ- የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና ነው የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ምሳሌ፡- ቅድስት ምሳዋን እየበላች ነው፡፡

#### መልመጃ አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የአሁን ጊዜ ከሆኑ አዎ ካልሆኑ አይደለም በማለት መልሱ፡፡

1. ዘማች ትናንት ወደ ጅንካ ሄደ፡፡
2. ጩቃ ነገ ወደ ዩኒቨርሲቲ ይጓዛል፡፡
3. ኮሬ  ፈተና ስለደረሰበት እያጠና ነው፡፡
4. ትናንት መምህራችን የቤት ስራውን አርመው መለሱልን፡፡
5. እናቴ ገበያ ሄዳ ነበር፡፡
6. የስፖርት ክፍለ ጊዜ በመሆኑ ተማሪዎቹ ኳስ እየተጫወቱ ነው፡፡

#### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች በተሰጣችሁ ምሳሌ መሰረት የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ አምስት

ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ሀና ወደ ገጠር እየሄደች ነው፡፡

ለ. ዘበርጋ ፈተና በመፈተን ላይ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ክርክር፣ ኢ-መደበኛ ጽሑፍና የአሁን ጊዜ የሚሉ ይዘቶችን ተምረናል፡፡ ክርክር ሁለት ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ዳኞችን በመሰየም የሚያደርጉት ስርዓት ያለው ሙግት ነው፡፡

ኢ-መደበኛ ጽሑፍ ለሀሳብ ቅደም ተከተሉ፣ ለድምፀቱ መለዋወጥ፣ ለሰዋስዋዊ ቅንብሩ፣ ለቃላት መረጣው፣ … እንብዛም ጥንቃቄ የማያደርግ የጽሑፍ አይነት ነው፡፡

የአሁን ጊዜ የሚባለው አንድ በአሁን ሰዓት የሚፈፀም ወይም በመፈፀም ላይ ያለ ድርጊትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው፡፡ አሁን የሚባለው አንድ ሰው ስለአንድ ድርጊት ንግግር የሚያደርግበት ጊዜ ነው፡፡ የአሁን ጊዜ የሆነ ግስ እየ- የሚል ምዕላድ ሊያስቀድምና ነው የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ ለወጡ ጥያቄዎች በጽሑፍ መልስ ስጡ፡፡

1. በአንድ ቤተሰብ ውስጥ የልጆችን ቁጥር መመጠን ምን ጠቀሜታ እንዳለው ዘርዝሩ፡፡
2. ባለ አንድ አንቀፅ መደበኛ ጽሑፍ ፃፉ፡፡
3. ሶስት የአሁን ጊዜን የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡


# ምዕራፍ ሶስት ፫

# በጎ ፈቃደኝነት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ሀሳብ በቃል ታብራራላችሁ፡፡
- ስለበጎ ፈቃደኝነት ፅንሰ ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- የምንባቡን ዋና እና ንኡሳን ሀሳቦች ለይታችሁ ትገልፃላችሁ፡፡
- የበጎ ፈቃደኞችን የስምሪት ገጽታዎች ትለያላችሁ፡፡
- ከጽሑፍ ውስጥ ተዘውታሪ ቃላትን ለይታችሁ ትዘረዝራላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

"የበጎ ፈቃደኝነት ተምሳሌት"



## ቅድመ ማዳመጥ

1. ከላይ በቀረበው ፎቶ ላይ የምትመለከቷቸውን ሴት ታውቋቸዋላችሁ? ካወቃችኋቸው በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን ስለእርሳቸው ምን ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. “ኦቲዝም” ሲባል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ

“የበጎ ፈቃደኝነት ተምሳሌት” በሚል ርእስ የተዘጋጀውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ሃሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ጻፉ፡፡ መምህሩ ለሚያቀርቡላችሁ ጥያቄዎች መልሳችሁን በቃል አቅርቡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

“የበጎ ፈቃደኝነት ተምሳሌት” በሚል ርዕስ ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ዘሚ የኑስ የተወለዱት መቼ እና የት ነው?
2. ባለ ታሪኳ ለራሴ በገባሁት ቃልኪዳን መሰረት ሲሉ ምን ለማለት ፈልገው ነው?
3. ዘሚ የኑስ ለወጣት ልጆች ካስተላለፉት መልዕክቶች መካከል ቢያንስ ሶስቱን ተናገሩ?
4. ባለታሪኳ ጆይ የኦቲዝም ማዕከልን ለመመስረት ያነሳሳቸው ምክንያት ምንድን ነው?
5. ከበጎ ፈቃደኝነት ውጭ ባለታሪኳ በምን ስራ ላይ ተሰማርተው ነበር?
6. የታሪኩን ዋና መልዕክት ባጭሩ ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### መለመጃ ሁለት፡-

በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ቃላት በ “ለ” ስር ከተሰጡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1 | ደጃፍ | ሀ. | ተጎናፀፉ |
| 2 | ክህሎት | ለ. | ውጤት |
| 3 | እርግማን | ሐ. | ችሎታ |
| 4 | እርግማን | መ. | በር |
| 5 | በርካታ | ሠ. | ፍርጃ |
| 6 | ስኬት | ረ. | ፍርጃ |
| 7 | ተቀዳጁ | ሰ. | ብዙ |
| 8 | ተቀዳጁ | ሸ. | ውድቀት |
| | | ቀ | አስተዋፅኦ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ትዕዛዝ

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን እርስ በእርስ ስለመረዳዳት ከተወያያችሁ በኋላ ተራ በተራ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "በጎ ፈቃደኝነት ምንድን ነው?"







## ቅድመ ንባብ

“በጎ ፈቃደኝት ምንድን ነው?” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት ቀጥሎ የቀረበውን የሰንጠረዥ ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ። ምንባቡን አንብባችሁ ስታበቁ ተመልሳችሁ ያወቃሁት የሚለውን በትክክል ሙሉ።

| የበጎ ፈቃደኝነት | | |
|---|---|---|
| ስለ በጎ ፈቃደኝነት የማውቀው | ስለ በጎ ፈቃደኝነት ማወቅ የምፈልገው | ስለ በጎ ፈቃደኝነት ያወቅሁት |
| - | - | - |
| - | - | - |
| - | - | - |
| - | - | - |

## ጊዜ ንበብ

### ትዕዛዝ

“በጎ ፈቃደኝነት ምንድን ነው?” የሚለውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ።

### “በጎ ፈቃደኝነት ምንድን ነው?”

በጎ ፈቃደኝነት ማለት በግለሰብ ወይም በቡድን የሚከናወን ግለሰብን፣ ቡድንን ወይም ድርጅትን ለማገልበትና ለማሳደግ ያለምንም ዓይነት የገንዘብ ክፍያ አገልግሎቶችን የምንሰጥበት ሂደት ነው። በጎ ፈቃደኝነት ለበጎ ፈቃደኛው እና ለማኅበረሰቡ በርካታ ጥቅሞች አሉት። በጎ ፈቃደኝነት የክህሎት ልህቀት ከማጎልበቱም ባሻገር ብዙውን ጊዜ በበጎነት ለመራመድ እና የሰዎችን ሰብዓዊ ሕይወት ለማሻሻል ይረዳል። ብዙ በጎ

ፈቃደኞች በሰለጠኑበት ወይም በተካኑት ሙያ ለምሳሌ:- እንደ ህክምና፣ ትምህርት ወይም ድንገተኛ እርዳታ በመሳሰሉ ዘርፎች የሚያገለግሉ ሲሆን ሌሎች ደግሞ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ለተጎዱ ወገኖች አስፈላጊውን አገልግሎት ይሠጣሉ።

እ.ኤ.አ ታኅሳስ 5 ቀን 2011 ዓ.ም በዓለም ዙሪያ 80 ያህል ሀገሮችን ያቀፈ የመጀመሪያው የዓለም የበጎ ፈቃደኞች መርሀ ግብር በተባበሩት መንግስታት ስር በአሜሪካ ኒውዮርክ ተቋቁሟል። የዚህ መርሀ ግብር ዋና ዓላማው በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተሻለ ግንዛቤን ከማስፋቱም ባሻገር የ21ኛውን ክፍለ ዘመን አዳዲስ እሳቤዎችን ከበጎ ፈቃደኝነት ዓለም አቀፍ ወሰን እና ተመጣጣኝነት ጋር የተዋሀደ ዓላማ ይዞ ነበር የተነሳው።

በመላው ዓለም ባሉ አብዛኛው ማኅበረሰቦች ውስጥ በጎ ፈቃደኞች በኢኮኖሚ እና በማኅበራዊ ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያድርጋሉ። በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች በፈቃደኝነት በልዩ ልዩ ተግባራት በመሳተፍ የሚሊኒየሙን የልማት ግቦች ለማሟላት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ከማበርከታቸውም ባሻገር ለወገኖቻቸው በእውቀታቸው እና በጉልበታቸው እያገለገሉ የመንፈስ እርካታን በሰፊው እየሸመቱ ይገኛሉ።

*ተማሪዎች ስለ በጎ ፈቃደኝነት ምን ተገነዘባችሁ? በቀጣዩ የምንባቡ ክፍል በሀገራችን ስላለው የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ምን የሚነገር ይመስላችኋል?

በሀገራችን በጎ ፈቃደኝነት የማኅበረሰቡ የእለት ተእለት የሕይወት መገለጫ ነው። ህዝቡ ለችግረኞች፣ ለአረጋዊያን እና ለወላጅ አልባ ህፃናት ተሰብስቦ በደቦ በማረስ፣ በመውቃትና ሰብስቦ ጎተራ በመክተት የበጎ ፈቃድ ስራዎችን ለበርካታ ዘመናት ሲያከናውን ኖሯል። ከዚህም ባሻገር ካመረተው እህል ከፍሎ ከመስጠት ጀምሮ በጉልበቱና በሙያው ለችግረኞች መድረስን የሚያውቅ ህዝብ ነው።

ኢትዮጵያዊያን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡት በችግር ወቅት ብቻ አይደለም። በደስታ ጊዜም ማኅበረሰቡ እርስ በእርስ ይረዳዳል። ለዚህም ማሳያነት የደቦ ወይም ወንፈል ባህልን መጥቀስ ይቻላል። ይህን ለረዥም ጊዜ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣውን መልካም የማኅበረሰብ ልማድ በተጠናከረ መልኩ በማስቀጠል በሀገራችን ባሉ አንገብጋቢ ጉዳዮች እና ትኩረት በሚገባቸው ተግባራት ዙሪያ ወጣቱን የማኅበረሰብ አካል በማንቃትና በማሳተፍ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎትን ማስቀጠልና ማስፋፋት ለሀገር እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

ምንጭ:- (ኤ.ሲ.ፒ.ኤሲ የትምህርት ቦርድ የት/ቤት የበጎ ፈቃደኞች መመሪያ ማኑዋል)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. የዓለም የበጎ ፈቃደኞች መርሀ ግብር በተባበሩት መንግስታት የተቋቋመው መቼ ነው?
2. በዓለም ላይ ምን ያህል ሰዎች በበጎ ፈቃደኝነት ተግባራት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ ተብሎ ይገመታል?
3. በመጨረሻው አንቀፅ ይህን ለረዥም ጊዜ ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ የማኅበረሰብ ልማድ የተባለው ምንድን ነው?
4. በጎ ፈቃደኝነት ማለት ምን ማለት ነው? ምንስ ጥቅም አለው?
5. በጎ ፈቃደኝነት ለሀገራችን አዲስ ጉዳይ ነው፡፡ በሚለው ሀሳብ ትስማማላችሁ? መልሳችሁን በምክንያት በማስደገፍ መልሱ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ቃላት እና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የዓለም የበጎ ፈቃደኞች <u>መርሀ ግብር</u> በኒውዮርክ ተቋቋመ፡፡
2. ለረዥም ጊዜ <u>ሲወርድ ሲወራረድ</u> የመጣ የማኅበረሰቡ ልማድ ነው፡፡
3. እህሉን ከጎተራ ከተቱት፡፡
4. የመንፈስ እርካታን በሰፊው <u>እየሸመቱ</u> ነው፡፡
5. ያለምንም አይነት የገንዘብ <u>ድጎማ</u> ይሰራሉ፡፡
6. በጎ ፈቃደኝነት የክህሎትን <u>ልህቀት</u> ይጨምራል፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

### ማስታወሻ

#### የማግባቢያ ጽሑፍ

የማግባቢያ ጽሑፍ አይነት ሰዎችን ለአንድ ዓላማ ወይም ተግባራት ለመቀስቀስ እና ለማሳመን የሚረዳ የጽሑፍ ዐይነት ነው፡፡ አግባቢ ጽሑፍ በአንባቢው አስተሳሰብ ላይ ጫናን በመፍጠር አመለካከቱን ለመቀየር ጥረት ያደርጋል፡፡

ምሳሌ፡-

አረጋሽ ዘለቃ እባላለሁ፤ በዚህ ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪ ስሆን በዘንድሮው ዓመት በሚካሄደው የተማሪዎች ፓርላማ እጩ ተወዳዳሪ ነኝ፡፡ እኔን ብትመርጡ እናንተን በመወከል በርካታ ስራዎችን በትጋት እሰራለሁ፡፡

ከዚህም ውስጥ፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር እና ወተመህ አባላት ጋር በመነጋገር ወቅታዊና አዳዲስ መጻሕፍት ተገዝተው በትምህርት ቤታችን ቤተ-መጻሕፍት ውስጥ እንዲገቡ አደርጋለሁ፡፡ እዲሁም የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ለመማር ማስተማሩ ምቹ ይሆን ዘንድ ከትምህርት ቤቱ ማኅበረሰብ ጋር በመመካከር እንዲሻሻል አደርጋለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሥነ-ምግባር ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በመለየት የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ አደርጋለሁ፡፡ በመጨረሻም በትምህርት ቤቱ በሚከናወኑ ወቅታዊ እና አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ በግንባር ቀደምነት በመሳተፍ ማንኛውንም ጥቅማጥቅም አስከብርላችኋለሁ፡፡ በመሆኑም በመጪው ምርጫ የእናንተን ድምጽ እንደማገኝ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ፡፡

**መልመጃ አንድ፡-**

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን መመሪያ መሰረት በማድረግ ባለ ሶስት አንቀፅ የማግባቢያ ጽሑፍ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

የፃፋችሁትን አንቀፅ  ተለዋውጣችሁ ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ጥምር ቃላት

**ማስታወሻ**

### ጥምር ቃላት

ጥምር ቃል ማለት ሁለት የተለያዩ ፍቾች ያላቸው ቃላት አንድ ላይ ተጣምረው የሚመሰርቱት አዲስ ትርጉም ያለው ቃል ነው፡፡

ምሳሌ፡- ትምህርት ቤት የሚለው ጥምር ቃል ትምህርት እና ቤት ከሚሉ ሁለት ቃላት የተመሰረተ ነው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ብረት ድስት፣ ሀኪም ቤት፣ ብረት ምጣድ፣ አየር መንገድ፣ ፖሊስ ጣቢያ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ቤተ እምነት፣ ቤተ ዘመድ፣ ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡

### መልመጃ አንድ፡-

ከላይ በማስታወሻው በቀረበው ምሳሌ መሰረት የምታውቋቸውን ስድስት ጥምር ቃላት ፃፉ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

“በጎ ፈቃደኝነት ምንድን ነው?” ከሚለው ምንባብ ውስጥ ከአንደኛው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አስር ተዘውታሪ ቃላትን ለይታችሁ በማውጣት ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

#### ነጠላ እና ብዙ ቁጥር

ነጠላ ቁጥር የሚባለው አንድ ነገርን ብቻ የሚገልፅ ነው፡፡ ብዙ ቁጥር የሚባለው ደግሞ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን ሚገልፅ ነው፡፡

| ምሳሌ፡- | ነጠላ ቁጥር | ብዙ ቁጥር |
|---|---|---|
| | ቤት | ቤቶች |
| | ቃል | ቃላት/ቃሎች |
| | ተማሪ | ተማሪዎች |

### ትዕዛዝ፡-

ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ነጠላ እና ብዙ ቁጥር በማለት ከለያችሁ በኋላ ዐረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ካህን | ታሪክ | ጥሬ |
| ሰማያት | አልባሳት | ግጥም |
| ቀን | በሬዎች | መጻሕፍት |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምእራፍ ስለ ማዳመጥ መመሪያ፣ ስለማግባቢያ ጽሑፍ፣ ስለጥምር ቃላት፣ ስለብዙ ቁጥርና ነጠላ ቁጥር ተምረናል፡፡
- ማዳመጥ የሚከናወነው በንቃት በመሆኑ ንቃትን ከማይጠይቀው ከመስማት እጅግ ይለያል፡፡ በማዳመጥ ሂደት ውስጥ ሁልጊዜም መረዳትና ማገናዘብ ይኖራል፡፡ ማዳመጥ የሰው ልጅ ተግባቦታዊ ሂደት መሰረት ነው፡፡ ከመናገር፣ ከመጻፍና ከማንበብ በበለጠ ብዙ ጊዜ የምናጠፋው በማዳመጥ ነው፡፡ የማዳመጥን ችሎታ ለማሳደግና ለማዳበርም ንቁ ተሳታፊ መሆን፣ ማስታወሻ መያዝ፣ ትኩረት ማድረግ፣ ወዘተ. ተገቢ ነው፡፡
- የማግባቢያ ጽሑፍ ሰዎችን ለአንድ ዓለማ ወይም ተግባር ለመቀስቀስ እና ለማሳመን የሚረዳ የጽሑፍ ዐይነት ነው፡፡ አግባቢ ጽሑፍ በአንባቢው አስተሳሰብ ላይ ጫናን በመፍጠር አመለካከቱን ለመቀየር ጥረት ያደርጋል፡፡
- ጥምር ቃል የምንለው ሁለት የተለያየ ፍቺ ያላቸው ቃላት አንድ ላይ ተጣምረው የሚፈጥሩት ለሌላ አዲስ ትርጉም ያለው ቃል ነው፡፡
- ነጠላ ቁጥር የሚባለው አንድ ነገርን ብቻ የሚገልፅ ሲሆን ብዙ ቁጥር ግን ከአንድ በላይ የሆኑ ነገሮችን የሚገልፅ ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. የተሰጣችሁን ቃላት በመጠቀም ጥምር ቃላት መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አልጋ | ሐ. ዳቦ | ሠ. ሰርግ |
| ለ. አየር | መ. ጦር | ረ. ሰማይ |

2. የሚከተሉትን ነጠላ ቁጥሮች ወደ ብዙ ቁጥር ቀይሩ፡፡

ሀ. ፍየል

ለ. ገዳም

ሐ. መስጊድ

መ. መምህር

ሠ. ወፍ


# ምዕራፍ አራት ፬

# የታዋቂ ሰዎች የሕይወት ታሪክ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሚነበብላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ ፍሬ ሀሳቡን በቃል ታብራራላችሁ፡፡
- የሕይወት ታሪክን ምንነትና አፃፃፍ ትገልፃላችሁ፡፡
- ከጽሑፉ ውስጥ በምክንያትና ውጤት ተዛምዶ የተብራሩ ነጥቦችን ትለያላችሁ፡፡
- በአካባቢያችሁ የሚገኙ ታዋቂ ሰውን የሕይወት ታሪክ ትፅፋላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

"ዶክተር ቦጋለች ገብሬና በጎ ተግባራቸው"



## ቅድመ ማዳመጥ

1. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚባሉት ሶስቱን ጥቀሱና ለምን ጎጂ እንደተባሉ አብራሩ፡፡
2. የሕይወት ታሪክ ሲጻፌ ምን ምን ነገሮችን ማካተት ያለበት ይመስላችኋል?
3. በፎቶው የሚታዩት ባለታሪክ በምን ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ይመስላችኋል?

❖ ጊዜ ማዳመጥ

## ትዕዛዝ

“ዶክተር ቦጋለች ገብሬ እና በጎ ስራቸው” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ ቁልፍ ሀሳቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

“ዶክተር ቦጋለች ገብሬ እና በጎ ስራቸው” በሚል ርዕስ በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

1. ቦጋለች ገብሬ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት የት ነበር?
2. ባለታሪኳ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን እንዲዋጉ ያነሳሳቸው ነገር ምንድን ነው?
3. ባለ ታሪኳ ከእህታቸው ጋር በመሆን የመሰረቱት ማኅበር ዋነኛ ስራው ምንድን ነው? የት የት አካባቢስ ስራውን ያከናውን ነበር?
4. በምንባቡ ውስጥ የኢትዮጵያ ሴቶች አመጽ አቀጣጣይ የተባሉት ሰው ማን ናቸው?
5. ባለታሪኳ ለስራቸው እውቅና ያገኙት ከየትኞቹ ተቋማት ነው?
6. ባለታሪኳ በአቋቋሙት ማኅበር ምን ያህል ሰዎች ተጠቃሚ ሆኑ? ከእነዚህ ምን ያህሎቹ ሴቶች ናቸው?

### መልመጃ ሁለት፡-

የሚከተሉት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ የያዙትን አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ሳይንቲስት
2. የመብት ተሟጋች
3. ያልተለመደ
4. ማብቃት
5. ማንቃት
6. አይነኬ
7. አመጽ

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ማስታወሻ

### የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ

በጽሑፍ ወይም በንባብ የቀረበ የአንድ ግለሰብ ታሪክ የሕይወት ታሪክ ይባላል፡፡ የሕይወት ታሪክ በአብዛኛው የሚዘጋጀው በታላላቅ ሰዎች ሕይወት ዙሪያ ነው፡፡ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡- የራስ የሕይወት ታሪክ እና የግለሰብ የሕይወት ታሪክ በመባል ይታወቃሉ፡፡

1. የራስ የሕይወት ታሪክ፡- የራስ የሕይወት ታሪክ ሲፃፍ
    - የትውልድ ስፍራን እና ዘመንን መግለፅ
    - ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መግለፅ
    - የትምህርት ደረጃን መግለፅ
    - ያበረከትነውን አስተዋፅኦ በቅደም ተከተል መፃፍ
    - ታሪካችንን ቀላል እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ማቅረብ
2. የግለሰብ የሕይወት ታሪክ፡-
    - ታሪኩ ስለሚፃፍለት ግለሰብ መረጃ መሰብሰብ፣ ማደራጀት እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
    - የትውልድ ቦታና ዘመንን፣ የሞተ ከሆነ የሞተበትን ዘመን መግለፅ
    - ስለአስተዳደጉ ሁኔታ መግለፅ
    - ስለፈፀማቸው ተግባሮች እና ስላበረከታቸው አስተዋጽኦዎች ማተት
    - ታሪኩን ቀላል እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ ማቅረብ ይኖርብናል

**መልመጃ አንድ፡-**

ከላይ የቀረበውን መመሪያ ካነበባችሁ በኂላ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩበት፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረበውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የዶክተር ሀዲስ አለማየሁን የሕይወት ታሪክ በማቀናጀት አጠር አድርጋችሁ በንግግር አቅርቡ፡፡

| የባለታሪኩ ስም | ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ |
|---|---|
| የአባት ስም | ቄስ አለማየሁ ሰለሞን |
| የእናት ስም | ወይዘሮ ደስታ አለሙ |
| የትውልድ ቦታ | ደብረ ማርቆስ አውራጃ ጎዛምን ወረዳ |
| የትውልድ ዘመን | ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ. ም |
| የተሰማሩበት የስራ መስክ | ደራሲ፣ አምባሳደር (1935-1966) በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ለሀገራቸው አገልግለዋል |
| የፃፏቸው መጻሕፍት | ፍቅር እስከ- መቃብር፣ ተረት ተረት የመሰረት፣ ወንጀለኛው ዳኛ፣ ትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም፣ የልምዣት፣ ወዘተ. |
| ለሌሎች አርዓያ የሆኑበት ተግባር | ለኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በጣሊያን ወረራ ወቅት ለሀገራቸው በአርበኝነት አገልግለዋል፡፡ |
| ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩበት ቀን | ህዳር 26 1996 ዓ. ም |

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### “አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት”





## ቅድመ ንባብ

1. ፌሊጣዊ ንግግር ሲባል ምን ማለት ነው? ከምታውቋቸው ፌሊጣዊ ንግግሮች ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
2. በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ታዋቂ የሆኑት በየትኛው ርቀት ይመስላችኋል?
3. ከላይ በምስሉ የምትመለከቷቸው አትሌት ማን ይባላሉ?

## ጊዜ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

“አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት” የሚለውን ምንባብ በማንበብ በየመህሉ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡

### “አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት”

“ለኢትዮጵያ ህዝብ እና ለሀገሬ በገባሁት ቃል ኪዳን መሰረት ሬሳዬ የሚወጣው ከሩጫው ሜዳ ነው፡፡” የሚሉት አትሌት ዋሚ ቢራቱ የተወለዱት ጥር 11 ቀን 1907 ዓ.ም ነው፡፡ የአቶ ቢራቱ በራቂ እና የወይዘሮ ወርቂ አያና ልጅ የሆኑት ዋሚ፣ የትውልድ ስፍራቸው ከአዲስ አበባ ከተማ 21 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ሱሉልታ ወረዳ አካኮና መነ አብቹ በተባለው ቀበሌ ገበሬ ማህበር ነው፡፡

ዋሚ የስድስት ወንዶች እና የአምስት ሴት ልጆች አባት፣ የሃያ አንድ ልጆች አያት እና የአስራ አንድ ልጆች ቅድመ አያት ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ስፖርት ፈር ቀዳጅ ከሆኑት መካከል አንዱ አትሌት ሻለቃ ዋሚ ቢራቱ በ93 ዓመት እድሜያቸው የካቲት 18 ቀን 1999 ዓ.ም በጃን ሜዳ በተካሄደው ሃያ አራተኛው ሀገር አቋራጭ ውድድር በአዋቂዎች ምድብ ከነስለሺ ስህን እና ታደሰ ቶላ እንዲሁም ከሌሎች አትሌቶች ጋር ተሰልፈው ሲሮጡ ታይተዋል፡፡

የልጅነት ዘመን ትዝታቸውን ከጊዜው መርዘም አኳያ እጅግ በጣም ሩቅ እና አውስተው የማይጨርሱት መሆኑን ቢናገሩም፣ በአጭሩ “እኔ በወጣትነትና በልጅነት ዘመኔ እኩዮኤን እና የበላዮቼን ከአስር እስከ አስራ ሁለት ጊዜ በላይ በሩጫ ደርቤ አልፋቸው ነበር፡፡ ወላጆቼ ያሳደጉኝ በማር እና በወተት በጨጨብሳ እና በጭኮ ነው፡፡ ከእረኝነት ወደ ግብርናው ሙያ የተሸጋገርኩት እንደ ሰንጋ ፈረስ እየተቀለብኩ ሲሆን የጎደለብኝ ነገር አልነበረም፡፡ አፍላ ወጣት ሳለሁ እናቴ ከገበያ ቡና ጠቅልላ

ያመጣችበትን የጋዜጣ ቅዳጅ ተመለከትኩ። በጋዜጣው ላይ አንድ ፀጉረ ልውጥ ሰው ሲሮጥ ይታያል፤ ያ ጋዜጣ ስለ ሰውየው አሸናፊነት እና ጥንካሬ የሚገልጽ ሀሳብ አስፍሯል። እሱን ከተመለከትኩ በኋላ ለአራት ዓመታት ያህል በአእምሮዬ ሳወጣ ሳወርድ ቆየሁ።"

*ተማሪዎች አትሌት ዋሚ ቢራቱ የት አካባቢ ተወለዱ? በቀጣዩ የታሪክ ክፍል ምን የሚያጋጥማቸው ይመስላችኋል?

አትሌት ዋሚ ወደ አትሌቲክስ ስፖርት የመጡት መስከረም 5 ቀን 1945 ዓ.ም ወደ ውትድርናው ዓለም ከገቡ በኋላ ነው። በወቅቱ የኢትዮጵያ ግዛት በነበረችው አስመራ ውስጥ በነባር እና በአዲስ ወታደሮች መካከል በተደረገው የሩጫ ውድድር አንደኛ ወጡ። በዚህ አይነት መንገድ የአትሌቲክሱን ህይወት "ሀ" ብለው ጀመሩ። በሀገር ውስጥ የማራቶን ውድድር ሲኖር የሚቀናቀናቸው ጠፋ። "በባዶ እግሬ በመሮጥ እና አበበ ቢቂላን ወደ ውድድሩ ዓለም በመሳብ፣ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፋና ወጊ ነኝ" የሚሉት ዋሚ ቢራቱ በ1953 ዓ.ም በጃፓን ቶኪዮ ላይ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድር ሻምበል አበበ ቢቂላን ተከትለው ሁለተኛ ወጥተዋል።

ሀገራችንን በመወከል በምስራቅ አፍሪካ፣ በጃፓን፣ በቼክ ሪፐብሊክ እና በቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ተወዳድረው አመርቂ ውጤት አስመዝግበዋል። ዋሚ በሀገር፣ በአህጉር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተካሄዱ ውድድሮች ሃምሳ አንድ ወርቅ፣ አርባ አራት የብር እና ሰላሳ የነሀስ ሜዳሊያዎችን ለመሸለም በቅተዋል። በተለይም በመስከረም 1996 ዓ.ም ቱሪዝም ኮሚሽን ባዘጋጀው ውድድር የሃያ አንድ ኪሎ ሜትሩን እሩጫ በ 2:05 ደቂቃ በመፈፀም አድናቆትን ያተረፉ አንጋፋ አትሌት ናቸው። የሻለቃ ዋሚ ቢራቱ ታሪክ እጅግ ረጅም፣ ሰፊና ጥልቅ ነው፤ ደማቁ ዋሚ በቀጣይ የአትሌቲክስ ታሪክ ሲወሱ የሚኖሩ አንጋፋ አትሌት ናቸው።

ምንጭ፡- (ደማቆቹ፣ 2000ዓ.ም የአንዳንድ ኢትዮጵያውያን የሕይወት ውልብታ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. አትሌት ዋሚ ቢራቱ ወደ አትሌቲክሱ ዓለም የገቡት በቀጥታ ነበር።
2. የባለታሪኩ ወታደራዊ ማዕረግ ሻምበል ነበር።

3. ዋሚ ቢራቱ ወደ አትሌቲክስ ዓለም የተሳቡት በአንድ ብጣሽ ጋዜጣ ላይ ባዩት ምስል ነበር፡፡
4. የዋሚ ቢራቱ ልጆች ቁጥር ከልጅ ልጆቻቸው ቁጥር ይበልጣል፡፡
5. ዋሚ ቢራቱ በተለያዩ ውድድሮች ሃምሳ አንድ የወርቅ ሜዳሊያዎችን አግኝተዋል፡፡
6. አትሌቱ በ1953 ዓ.ም ቶኪዮ ላይ በተደረገው ውድድር ሻምበል አበበ ቢቂላን በማስከተል አንደኛ ወጥተዋል፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ከምንባቡ የወጡት ቃላት በ "ለ" ስር ካለው ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| 1 | አመርቂ | ሀ. እድሜ ጠገብ |
| 2 | አንጋፋ | ለ. ርቀት |
| 3 | ያተረፉ | ሐ. የማይታወቁ |
| 4 | አፍላ | መ. አጥጋቢ ያልሆነ |
| 5 | ደማቅ | ሠ. ወጥመድ |
| | | ረ. ደብዛዛ |

## መልመጃ ሶስት፡-

ከታች የቀረበውን ማስታወሻ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ ተወያዩበት፡፡ ቀጥሎም አንጋፋው የአትሌቲክስ አባት በሚለው ምንባብ ውስጥ የቀረቡ ፈሊጣዊ ንግግሮችን ለይታችሁ ፍቻቸውን ተናገሩ፡፡

### ማስታወሻ

#### ፈሊጣዊ አነጋገር

ፈሊጣዊ ንግግር ከቋንቋ የአነጋገር ስልቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የሚፈጠረውም በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ቃላትን በልዩ ልዩ ዘዴ በመጠቀም ነው፡፡ ፈሊጣዊ ንግግር እያንዳንዱ ቃል ከሌሎች ቃላት ጋር በሚቀናጅበት ጊዜ መጀመሪያ የነበረውን ፍቺ ሙሉ በሙሉ በመቀየር አዲስ ፍቺ የሚሰጥበት መንገድ ነው፡፡

ምሳሌ፡- "ሁለት ልብ" የሚለውን የሁለት ቃላት ቅንጅት ብንመለከት ወላዋይ (ለመወሰን የተቸገረ) የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

### አያያዥ ቃላትና ሀረጋት

አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ለብቻቸው ትርጉም አይሰጡም፡፡ ነገር ግን ተግባር አላቸው፡፡ ይኸውም፡-

- ከአንድ ሀሳብ ወደሌላ ሀሳብ ለመሸጋገሪያነት
- የቀደመውን ሀሳብ ከሚቀጥለው ማጠናከሪያ ጋር ለማቆራኘት
- አፍራሽ ወይም ተቃራኒ ሀሳቦችን ለማገናኘት
- ለቀደመው ሀሳብ ምክንያት ሰጪ ሀሳብን ለማስከተል
- የጊዜ ቅደም ተከተል ያላቸውን ሀሳቦች ለማያያዝ ወዘተ. ያገለግላሉ፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ተጨማሪ ሀሳቦችን የሚያክሉ፡- በተጨማሪም፣ እንዲሁም፣ ቀጥሎም…

ለ. ተቃራኒ ሀሳቦችን የሚያያይዙ፡- ይሁን እንጂ፣ የሆነው ሆኖ፣ ነገር ግን፣ ዳሩ ግን…

ሐ. ምክንያት ሰጪ ሀሳብን ለማስከተል፡- በዚህ የተነሳ፣ ምክንያቱም፣ ስለዚህ…

መ. የሀሳብ ቅደም ተከተልን የሚጠብቁ አያያዦች፡- ከዚህ በኋላ፣ ቀጥሎም፣ በተመሳሳይ ጊዜ…

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን አያያዥ ቃላትና ሀረጋት በዓረፍተ ነገሮቹ ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው አስቀምጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ይሁን እንጂ | አለበለዚያ | እና |
| ወይም | ስለሆነም | በተጨማሪም |

1. በጣም ሀይለኛ ዝናብ ጣለ፤ ______________ ምንም ጉዳት አላደረሰም፡፡
2. ወደ ሐረር የሚሄደው በመኪና ________________ በባቡር ነው፡፡
3. የወባ በሽታ እየተስፋፋ መጥቷል፤ _____________ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል፡፡
4. መምህራችን ትዕግስትን _________ ከድጃን ቢሮ እንዲመጡ ነገረቻቸው፡

5. ጥሩ ውጤት ለማምጣት በርትተን ማጥናት ይኖርብናል፤ ____________ የወላጅና የመምህር ክትትል ያስፈልገናል፡፡
6. ገንዘቤን በሰላም መልስልኝ፤ ____________ፍርድ ቤት እገትርሃለሁ፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ አንብባችሁ በየግላችሁ አያያዥ ቃላትን በመጠቀም ስድስት ስድስት ዓረፍተ ነገሮች መስርቱ፡፡

**መልመጃ ሶስት፡-**

የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያን በመከተል የራሳችሁን ወይም አንድ የቅርብ ቤተሰባችሁን ሰው የሕይወት ታሪክ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ተዘውታሪና ፈሊጣዊ ቃላት

**መልመጃ አንድ፡-**

ከታች የቀረቡትን ተዘውታሪ ቃላት በመጠቀም ስድስት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. እንቅፋት
2. ቁርስ
3. ለበሰ
4. ተከዘች
5. ሰዓት
6. ቅንነት

**መልመጃ ሁለት፡-**

ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ፈሊጣዊ ንግግሮች ከሰንጠረዡ ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቂም አረገዘች | የሞቀ ቤት | ልብ አቁስል |
| አመድ አፋሽ | ሀሞቱ ፈሰሰ | ውሃ በላው |
| አፈ ቅቤ | አይኑ ቀላ | ስራ ፈት |
| ገፀ በረከት | ሰማይ ቅርቡ | ቅስሙ ተሰበረ |

1. ስንት የለፋሁበትን ስራ ____________፡፡
2. ____________ስለሆነ ጊዜውን በአልባሌ ቦታ ያጠፋል፡፡

3. በሰማው ዜና ______________________::
4. ለበርካታ ዓመታት ለሰራችው መልካም ስራ________________- ተበረከተላት::
5. የነገሩትን የማይሰማ ________________ ነው::
6. ______________ እያለው ወደ ጎዳና ወጣ::
7. ያልተፈጠረ ነገር የተፈጠረ አስመስላ የምታቀርብ_________________ ናት::
8. ስራውን መስራት ሳይጀምር ______________________::
9. ከሉባባ ጋር በማይረባ ጉዳይ ስለተጣላች __________________::
10. ምንም እንኳን ለሰዎች መልካም ስራ ብትሰራም የማትመሰገን_______ ናት::

### መልመጃ ሶስት፡-

አስር አስር ፈሊጣዊ ንግግሮችን ከነፍቻቸው በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ::

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### መልመጃ አንድ፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻና መመሪያ መሰረት ከታች ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ስማዊ ሀረጎች ለዩ::

1. ወንድሜ የስንዴ ዳቦ ሰጠኝ::
2. የታመመው ልጅ ወደ ሀኪም ቤት ሄደ::
3. ወይንሸት ጎበዝ ተማሪ ናት::
4. ሰሚራ ጥቁር እስክርቢቶ ገዛች::
5. ከድጃ ወደ አዲስ አበባ ሄደች::

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች በቀረቡት ስማዊ ሀረጎች ዓረፍተ ነገር መስርቱ::

1. የገብስ ቆሎ
2. የቆዳ ጫማ
3. ቀይ ወጥ
4. አሮጌ መኪና
5. የላም ወተት
6. የስዕል ደብተር

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ ሕይወት ታሪክ አፃፃፍ፣ ስለ ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ ስለ አያያዥ ቃላትና ሀረጋት፣ እንዲሁም የሀረግ አይነቶችን ተምረናል፡፡
- በጽሑፍ ወይም በንባብ የቀረበ የአንድ ግለሰብ ታሪክ የሕይወት ታሪክ ይባላል፡፡ የሕይወት ታሪክ በአብዛኛው የሚዘጋጀው በታላላቅ ሰዎች ሕይወት ዙሪያ ነው፡፡ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም፡- የራስ የሕይወት ታሪክ እና የሌላ ግለሰብ የሕይወት ታሪክ በመባል ይታወቃሉ፡፡
- ፈሊጣዊ ንግግር ከቋንቋ የአነጋገር ስልቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን የሚፈጠረውም በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ቃላትን በልዩ ልዩ ዘዴ በመጠቀም ነው፡፡
- አያያዥ ቃላት ወይም ሀረጋት ለብቻቸው ትርጉም አይሰጡም፡፡ ነገር ግን ተግባር አላቸው፡፡
- ሀረግ ትርጉም ያላቸው ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት መዋቅር ነው፡፡ የሀረጉም ዓይነት በሀረጉ ውስጥ ዋና ሆኖ በሚገባው ቃል ዓይነት ይወሰናል፡፡ ዋናው ቃል ሆኖ የሚገባው ቃል የሀረጉ መሪ ይባላል፡፡ በዚህም መሰረት ስማዊ ሀረግ፣ ቅጽላዊ ሀረግ፣ ግሳዊ ሀረግ፣ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ፣ መስተዋድዳዊ ሀረግ ተብለው በአምስት ይከፈላሉ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከታች ለቀረቡት ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍቾች ስጡ፡፡
   ሀ. ቃል አጠረው — ሐ. ሰማይ ጠቀስ
   ለ. አመለቢስ — መ. በሬ ወለደ
2. ከታች የቀረቡትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም የምክንያትና ውጤት ትስስርን የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡
   ሀ. ይሁን እንጂ — ሐ. በዚህ የተነሳ
   ለ. እንዲሁም
3. ቀጥሎ የተሰጡትን ቃላት በመጠቀም ስማዊ ሀረግ መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቦርሳ | ኳስ | ሳጥን |
| ምንጣፍ | ሰው | እስክርቢቶ |

4. የሕይወት ታሪክ ሲጻፍ የሚካተቱ ነገሮችን ዘርዝሩ፡፡


# ምዕራፍ አምስት ፭

# ውሃና ጥቅሙ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች


ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- የሚደመጡ ንግግሮችን አዳማጣችሁ ፍሬ ሀሳቦችን ለይታችሁ ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ስለውሃ ጥቅም ትገልጻላችሁ፡፡
- ሰለ ውሃ ጥቅም የየራሳችሁን አመለካከትና አቋም ትገልፃላችሁ፡፡
- ከምንባቡ ውስጥ ያሉ አዳዲስ ቃላትን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- የውሃ አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### “ውሃና የውሃ ጥቅም”



## ቅድመ ማዳመጥ

"ውሃና የውሃ ጥቅም" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ ቀጥሎ ያለውን ሰንጠረዥ ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ፡፡ ንባቡ እንዳለቀ ወደኋላ ተመልሳችሁ ያወቅሁት የሚለውን ክፍል በትክክል ሙሉ፡፡

| ውሃና የውሃ ጥቅም | | |
|---|---|---|
| ስለውሃና የውሃ ጥቅም የማውቀው | ስለውሃና የውሃ ጥቅም ማወቅ የምፈልገው | ስለውሃና የውሃ ጥቅም ተጨማሪ ያወቅሁት |
| -<br>-<br>-<br>- | -<br>-<br>-<br>- | -<br>-<br>-<br>- |

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ ፡-

"ውሃና የውሃ ጥቅም" በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ለይታችሁ በማስታወሻ ደብተራችሁ ጻፉ፡፡ ማስታወሻችሁን በመጠቀምም መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. ከሰውነታችን ውስጥ ምን ያህል እጅ ውሃ ነው?
   ሀ. ሶስት አራተኛው          ሐ. አንድ አራተኛው
   ለ. አንድ ሶስተኛው          መ. ሁለት ሶስተኛው

2. ለውሃ መበከል ምክንያት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ከፋብሪካ የሚወጡ ጽዳጆች ሐ. የአረምና የተባይ ማጥፊያዎች
   ለ. ከመኖሪያ ቤት የሚወጡ ጽዳጆች መ. ሁሉም
3. የውሃ ብክለት በምን በምን ላይ ጉዳት ያደርሳል?
   ሀ. በጤና ለ. በኢኮኖሚ ሐ. በአካባቢ መ. ሁሉም
4. ከሚከተሉት ውስጥ የውሃ ወለድ በሽታ ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ታይፎይድ ለ. ኮሌራ ሐ. ጉንፋን መ. ጃርዲያ
5. የአንጎላችን ምን ያህል በመቶው ውሃ ነው?
   ሀ. ሰባ በመቶው ሐ. ሃያ ሰባት በመቶው
   ለ. ሰባ ሁለት በመቶው መ. ሰማንያ ሁለት በመቶው
6. በሁለተኛው አንቀፅ “ይህ ፈሳሽ” የተባለው ምንድን ነው?
   ሀ. ውሃ ለ. ደም ሐ. ምራቅ መ. ዘይት

## መልመጃ ሁለት፡-

በ “ሀ” ስር ለቀረቡት ቃላት በ “ለ” ስር ከቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| “ሀ” | | “ለ” | |
|---|---|---|---|
| 1 | ዝውውር | ሀ. | ውጤት |
| 2 | ምቹ | ለ. | ጎጅ |
| 3 | በአግባቡ | ሐ. | መንስኤ |
| 4 | ምክንያት | መ. | ተስማሚ |
| 5 | ትስስር | ሠ. | እንቅስቃሴ |
| 6 | መርዛማ | ረ. | መተግበር |
| 7 | ማከናወን | ሰ. | ጠቃሚ |
| | | ሸ. | ቁርኝት |
| | | ቀ. | በስርዓት |

## መልመጃ ሶስት፡-

ከታች በሳጥኑ ውስጥ የተሰጡትን ቃላት በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢ ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ብዚል | ያሳያሉ | ተህዋሲያን |
| አንፃር | አልሚ | መዛመት |

1. በሽታ የሚያስተላልፉትን----------------------ለማስወገድ እጃችንን በተደጋጋሚ መታጠብ አለብን፡፡
2. ------------------- ምግቦችን መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ ነው፡፡
3. የኮሮና ቫይረስ -------------- አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡
4. ወጣቶች ያሰቡበት ደረጃ ላይ እንዳይደርሱ እንቅፋት ከሆኑት ነገሮች አደንዛዥ እጽ አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ---------------
5. “የውሃና የእናት መጥፎ የለውም” የሚል------------ በሀገራችን አለ፡፡
6. ውሃ ከጥቅሙ -------------------- ተገቢው ትኩረት አልተሰጠውም፡፡


## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡-

ውሃና ጥቅሙ በሚል ርዕስ ከአዳመጣችሁት ምንባብ የወሰዳችሁትን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ስለውሃ አይነቶች እና ጠቀሜታ ውይይት አድርጉ፡፡

መልመጃ ሁለት፡-

በውሃ አጠቃቀም ዙሪያ ያላችሁን አመለካከትና ፍላጎት በምክንያትና ውጤት በማስደገፍ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡



## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### “ለውሃ ስም አነሰው”



## ቅድመ ንባብ

1. ለውሃ ብክነትና ብክለት ምክንያቶቹ ምን ምን ይመስላችኋል?
2. የውሃ ብክለት የሚያስከትለውን ጉዳት ዘርዝሩ፡፡
3. ከላይ ከቀረበው ምስል ምን ተረዳችሁ?

## ጊዜ ንባብ

### ትዕዛዝ፡-

“ለውሃ ስም አነሰው” የሚለውን ምንባብ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ፡፡ በየመሀሉ በመምህራችሁ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡፡

### “ለውሃ ስም አነሰው”

ከማልና መቅደስ የድል በትግል ትምህርት ቤት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በምሳ ሰዓት ምሳቸውን ከተመገቡ በኋላ መምህራቸው በሰጧቸው የቤት ስራ ዙሪያ በትምህርት ቤታቸው ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሚገኘው ትልቅ ዛፍ ስር አረፍ ብለው “ለውሃ ስም አነሰው” በተባለው ርዕስ ዙሪያ ስለሚፅፉት አንቀጽ እየተወያዩ ነው፡፡

- ከማል፡- “ዛሬ የአማርኛ መምህር የሰጡን የቤት ስራ ግራ ገብቶኛል” ፡፡
- መቅደስ፡- “እንዴት ከማል?”
- ከማል፡- “ ‹ለውሃ ስም አነሰው› በሚለው ርዕስ ዙሪያ ሶስት አንቀጽ ጻፉ ያሉት፡፡”
- መቅደስ፡- “ታዲያ ምን ችግር አለው? ውሃ እኮ ከእለት ተእለት ሕይወታችን ጋር ጥብቅ ግንኙነት አለው፤ ስለዚህ ሊከብድህ አይገባም፡፡”
- ከማል፡- “መፃፍማ ቀላል ነው፤ ነገር ግን እንዴት አድርጌ ሶስት አንቀጽ ላሟላ?”
- መቅደስ፡- “ለመሆኑ ስንት አይነት የውሃ አይነቶች እንዳሉ ታውቃለህ?፡፡”
- ከማል፡- “እሱማ አውቃለሁ አምስተኛ ክፍል የተቀናጀ ሳይንስ ላይ ተምረናል፡፡ እነሱም፡- ለመጠጥ አገልግሎት የሚውል ለምሳሌ የምንጭ እና የቧንቧ ውሃ፤ እንዲሁም ለመጠጥ አገልግሎት የማይውል በተለያዩ ንጥረ ነገሮች የተበከለ የውሃ አይነት አለ፡፡ ለምሳሌ የውቅያኖስ፣ የባህር እና የወንዝ ውሃ ይጠቀሳሉ፡፡”
- መቅደስ፡- “ልክ ነህ እኔም አስታወስከኝ፤ በመጀመሪያ ግን ሕይወት ያለው ነገር ለመኖር ውሃ እንደሚያስፈልገው በዝርዝር እንጽፋለን፤ ምድራችንም

70 በመቶው በውሃ የተሸፈነ ነው፡፡”

- ተማሪዎች የከማልና የመቅደስ ውይይት መነሻ ምክንያቱ ምንድን ነው? በቀጣዩ የውይይት ክፍልስ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

- ከማል፡- “ጥሩ ብለሻል መቅደስ፣ ጥሩ ውሃን ግን በምን እንለየዋለን?”
- መቅደስ፡- “ጥሩ ውሃ የሚባለው በተፈጥሮ ንጥረ ነገሮች የበለፀገ ነው፡ ፡ እነሱም፡- ማግኒዥየም፣ ካልሲየም፣ ፖታሺየም፣ ሶዲየም፣ ወዘተ. የያዘ ነው፡፡”
- ከማል፡- “እንዴ መቅዲ በጣም ልክ ነሽ፤ ትዝ አለኝ ውሃኮ ሌሎችም ጥቅሞች አሉት፡፡ ለምሳሌ ለኃይል ማመንጫነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፤ የተለያዩ ወንዞች ተገድበው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ በመሆን የሚያገለግሉት ውሃ ሲኖር ብቻ ነው፡፡”
- መቅደስ፡- “ልክ ነህ ከማል ከዚህ በተጨማሪ በመስኖ የተለያዩ አዝዕርቶችን ለማብቀል ውሃ ከፍተኛ ጥቅም አለው፤ በዚህ ደግሞ ድህነትና ርሀብን መዋጋት እንችላለን፡፡ በተጨማሪም ውሃ የተለያዩ የዓሳ ምርቶችን ስለሚሰጥ ዓሳ አስጋሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡”
- ከማል፡- “ከዚህ በተጨማሪ የሰው ልጆች አዕምሯቸውን ለማደስና የእረፍት ጊዜያቸውን ለማሳለፍ የውሃ ዳርና የውሃ ላይ መዝናኛዎችን ይመርጣሉ፡፡”
- መቅደስ፡- “ውሃ የዚህን ያክል ጥቅም ካለው ለምንድን ነው? በአግባቡ የማንጠቀመው?”
- ከማል፡- “እውነትሽን ነው፤ ይህ ለረዥም ጊዜ ሲከነክነኝ የነበረ ጉዳይ ነው፤ ግን እንዴት ነው? ከብክነት መከላከል የምንችለው?”
- መቅደስ፡- “ውሃን ስንጠቀም ብዙ ባለማፍሰስ፣ እንዲሁም ቧንቧዎችን ከፍቶ ባለመተው፣ ከዚህም በተጨማሪ ውሃን በድጋሚ በመጠቀም፣ ለምሳሌ ልብስ ባጠብንበት ውሃ ቤትና ሽንት ቤቶችን በመወልወል ወዘተ. የመሳሰሉትን ተግባራት በመፈጸም ነው፡፡”
- ከማል፡- “እስካሁን ብዙ ነገር አንስተናል፤ ነገር ግን ስለ ውሃ ብክለት አላወራንም፡፡”
- መቅደስ ፡- “አዎ በጣም ልክ ነህ! ውሃን የሚበክሉ ንጥረ ነገሮች በውሃ ውስጥ መገኘት ውሃን ተበከለ ያሰኘዋል፡፡”
- ከማል፡- “በርካታ ሰዎች ለውሃ ብክለት ተጠያቂዎች ናቸው ማለት ነው፡

፡ ምክንያቱም የሚጸዳዱትና ቆሻሻ የሚጥሉት በውሃማ አካላት ላይ ነው፡፡"

- መቅደስ፡- "አንተ ካልከው በተጨማሪ ከፋብሪካ የሚለቀቁ ፅዳጆች (ቆሻሻዎች)፣ በወንዞች ዳርቻ ልብስ ማጠብና መፀዳዳት፣ ከመፀዳጃ ቤት አላግባብ ወደ ወንዝ የሚለቀቁ ፍሳሾች ለውሃ ብክለት መንስኤዎች ናቸው፡፡"
- ከማል፡- "ታዲያ ከእኛ ምን ይጠበቃል?"
- መቅደስ፡- "ከእኛማ የሚጠበቀው ውሃ እንዳይባክን እና እንዳይበከል ባገኘነው አጋጣሚ ለክፍል ጓደኞቻችን እና ለቤተሰቦቻችን ማስተማር ነው፡፡"
- ከማል፡- "በጣም ትክክል ነሽ፤ ለካ ይህ ሁሉ ጥቅም አለው፡፡ ይህን ስላልተረዳን ነው በአግባቡ የማንይዘው፡፡ መምህራችን ትክክል ናቸው 'ለውሃ ስም አነሰው' በሚል ርዕስ አንቀጽ ጻፉ ያሉን፤ በይ ሰዓቱ ስለደረሰ ወደ ክፍላችን እንሂድ"፡ ፡ ብለው ውይይታቸውን ጨርሰው ወደ ክፍላቸው ገቡ፡፡

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

"ለውሃ ስም አነሰው" በሚል ርዕስ በአነበባችሁት ምንባብ መሰረት የሚከተሉትን የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ውሃ ተበከለ የሚባለው ምን ሲሆን ነው?
2. የምድራችን ምን ያህል በመቶው በውሃ የተሸፈነ ነው?
3. በተፈጥሮ ማዕድን የበለፀገ ውሃ ምን ምን ንጥረ-ነገሮችን ይይዛል?
4. ለውሃ መበከል በምክንያትነት የተጠቀሱት ምን ምን ናቸው?
5. ሁላችንም ለውሃ ብክለት ተጠያቂዎች ነን ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. "ለውሃ ስም አነሰው" የሚለውን ሀሰብ አብራርታችሁ ፃፉ፡፡
7. የውሃ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. የበለፀገ
2. ማመንጨት
3. አዝዕርት
4. አሳ አስጋሪዎች
5. ሲከነክነኝ
6. ጽዳጆች
7. መበከል
8. መባከን

## መልመጃ ሶስት፡-

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች በማንበብ የሚያስተላልፉትን ሀሳብ ምክንያትና ውጤት ብላችሁ ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. አበባው ውሃ ባለመጠጣቱ ጠውልጓል፡፡

ምክንያት = ውሃ ባለመጠጣቱ
ውጤት = ጠውልጓል

ለ. የተደሰተው አዲስ ልብስ ስለተገዛለት ነው፡፡

ምክንያት = አዲስ ልብስ ስለተገዛለት

ውጤት = የተደሰተው

1. በሙስና ስለተጠረጠረ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋለ፡፡

ምክንያት =
ውጤት =

2. ኃይለኛ ራስ ምታት ስላመመኝ ከትምህርት ቤት ቀረሁ፡፡

ምክንያት =
ውጤት =

3. ውሃን በአግባቡ አለመያዝ ለተለያዩ በሽታዎች ያጋልጣል፡፡

ምክንያት =
ውጤት =

4. ትምህርቱን ያቋረጠው ደጋፊ አልባ በመሆኑ ነው፡፡

ምክንያት =
ውጤት =

5. ጥሩ ውጤት ያስመዘገበው ጠንክሮ በመስራቱ ነው፡፡

ምክንያት =
ውጤት =

6. በርካታ ሰዎች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ባለማድረጋቸው የኮሮና ቫይረስ በጣም ተስፋፋ፡፡

ምክንያት =

ውጤት =

7. ሕይወቷ ሊያልፍ የቻለው ቶሎ ወደ ሆስፒታል ባለመሄዷ ነው፡፡

ምክንያት =

ውጤት =

8. የትራፊክ አደጋ የተስፋፋው በአሽከርካሪዎችና በእግረኞች ቸልተኝነት ነው፡፡

ምክንያት =

ውጤት =

### ተግባር፡-

በውሃ ወለድ ስለሚተላለፉ በሽታዎች ምንነትና ስለሚያስከትሉት ጉዳት ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከአካባቢያችሁ ወይም ከቤተ መጻሕፍት መረጃ ሰብስባችሁ በመምጣት በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

#### ተራኪ ጽሑፍ

ይህ የጸሑፍ ዓይነት ተከታታይነት ያላቸውን ድርጊቶች እና ሁነቶች መሰረት አድርጎ ከመነሻው እስከ መድረሻው ድረስ የሚሆነውን ነገር እየተረከ ለአንባቢ በማድረስ ላይ ያተኩራል፡፡ በተራኪ ጽሑፍ ውስጥ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ እንዲህ ሆነ፣ ከዚያም እንዲህ ተደረገ በሚል አቀራረብ የነገሮችን አከናወንና አፈፃፀም በትረካ ያቀርባል፡፡ በዚህም አንባቢው የሁነቶችን፣ የክስተቶችን እና የድርጊቶችን ትስስር በቅርበት መከታተል የሚችልበት መንገድ ያመቻቻል፡፡ ተራኪ ጽሑፍ ልቦለዳዊ ወይም ኢ-ልቦለዳዊ ሊሆን ይችላል፡፡ የበለጠ ግልጽ እንዲሆንላችሁ ከማስታሻው ቀጥሎ የቀረቡትን ምሳሌዎች ተመልከቱ፡፡

ምሳሌ አንድ፡- ልቦለዳዊ ተራኪ ጽሑፍ

… የዚያኑ እለት ማታ የባቡር ትኬት አስቆረጥኩና ጓዜን ጠቅልዬ ጉዞ ወደ ሐረርጌ ጀመርኩ፤ ሲነጋጋ ድሬድዋ ከተማ ደረስኩ። አልጋ ተከራይቼ አጎቴ ቤት ጎራ አልኩና ብጠይቅ ለስራ ጉዳይ ወደ ሌላ ቦታ መሄዱን ባለቤቱ ነግራኝ ወደ ቤት እንድገባ ጠየቀችኝ። ያለሁበትን ማወቅ ተሳነኝ፤ መላው አለም በተቃውሞ የተነሳብኝ መሰለኝ። የአጎቴን ባለቤት ጥያቄ ምላሽ ሳልሰጥ እንዳበደ ሰው ከንፌ ወደ ተከራየሁት ቤርጎ ተጓዝኩ። ቤርጎ ቤቱ ጋር እንደደረስኩ ወደ ቡና ቤት ገባሁ። መላ ህዋሳቴ ዝሏል። አሳላፊው እስኪደንቀው ድረስ ሶስት ቡና አከታትዬ ጠጥቼ ወጣሁ።…

ምሳሌ ሁለት፡- ኢ-ልቦለዳዊ ተራኪ ጽሑፍ

ቀኑ እለተ አርብ መጋቢት አራት 2012 ዓ.ም ነው፤ ገና በማለዳ ነበር ወደ ትምህርት ቤት ያቀናሁት። ወዲያው ወደ ትምህርት ቤቱ የሚኒ ሚዲያ ቢሮ ገባሁ። አስታውሳለሁ "ሀገሬን አልረሳም" የሚለውን የንዋይ ደበበን ሙዚቃ ድምፁን ከፍ አድርጌ ከፈትኩት። ተማሪዎች ሰዓት እየደረሰ ስለነበር እየተንጠባጠቡም ቢሆን ወደ ሰልፍ ቦታው እየተጠጉ ነበር። ሙዚቃው እንዳለቀ የሀገራችንን ብሔራዊ መዝሙር ተማሪዎች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ዘመሩ። በመቀጠልም የትምህርት ቤታችን ርዕሰ መምህር በተማሪዎች ሥነ-ምግባር ዙሪያ ጠንከር ያለ መልዕክት አስተላለፉ። እኔም ተማሪዎቹን ወደ ክፍላቸው እንዲገቡ ካዘዝኩ በኋላ የማስተምርበት ክፍለ ጊዜ እስኪደርስ ቁርስ ለመብላት በትምህርት ቤታችን የመምህራን ምግብ ቤት ጎራ አልኩኝ።

ቁርሴን ተመግቤ ሻሂ እየጠጣሁ እያለ ድንገት ዓይኔ በግድግዳው የተሰቀለው ቴሌቪዥን ላይ አረፈ። ጋዜጠኛው የሶስት ሰዓቱን ዜና እያነበበ ነበር። ድንገት የአድማጭን ቀልብ የሳበው ሰበር ዜና በጋዜጠኛው አንደበት ሲስተጋባ ሁሉም ሰው በድንጋጤ ተዋጠ። "የመጀመሪያው የኮሮና ተጠቂ ኢትዮጵያ ውስጥ ተገኘ" ሲል ቤቱ በአንዴ በድንጋጤ ድባብ ተሞላ። የጀመርኩትን ሻሂ እንኳን ሳልጨርስ በሀዘን ስሜት ከምግብ ቤት ስወጣ ተማሪዎች ከግቢ እየወጡ ነበር። መምህራንም በየፊናቸው በድንጋጤ ተውጠው ይሯሯጣሉ። በግቢው ውስጥ የነበረው ትዕይንት በሕይወት ዘመኔ ከማልረሳቸው ትዝታዎች ውስጥ አንዱ ነው።

**መልመጃ አንድ፡-**

የማትረሱትን ገጠመኝ መሰረት በማድረግ ባለ ሁለት አንቀጽ ተራኪ ጽሑፍ ፃፉ።

**መልመጃ ሁለት፡-**

በመልመጃ አንድ የፃፋችሁትን ተራኪ ጽሑፍ በመቀያየር እርስ በእርስ ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የቃላት እማሬያዊ ፍች

**መልመጃ አንድ፡-**

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት እማሬያዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ሚጥሚጣ
2. ቀፎ
3. ንብ
4. ሚዛን
5. ፍየል
6. መሬት
7. ጨለማ
8. ቆቅ
9. ባህር
10. ወንበር

**መልመጃ ሁለት፡-**

ከላይ ፍች በሰጣችሁባቸው ቃላት ዓረፍተ ነገር መስርቱባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ጣልያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ግልብጥ ብሎ ወጣ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

### ገቢር እና ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች

ዓረፍተ ነገሮችን ገቢርና ተገብሮ ብሎ በሁለት መክፈል ይቻላል፡፡

ሀ. ገቢር ዓረፍተ ነገሮች፡- ትኩረት የሚያደርጉት ተግባሩን የፈጸመው ባለቤት (ድርጊት ፈፃሚው ) ላይ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

- ሙሉጌታ አበባ ተከለ፡፡
- ሌባው ገንዘቤን ሰረቀኝ፡፡
- ልጆቻችንን ወደ መናፈሻ እንወስዳለን፡፡

ለ. ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች፡- ትኩረት የሚያደርጉት በተሳቢ (ድርጊት ተቀባይ) ላይ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

- አበባው ተተከለ፡፡
- ገንዘቤ ተሰረቀ፡፡
- ልጆቻችን ወደ መናፈሻ ይወሰዳሉ፡፡

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ገቢርና ተገብሮ በማለት ለይታችሁ ፃፉ፡፡

1. አልማዝ ብርጭቆውን ሰበረችው፡፡
2. መኪናው የተገዛው በአባቴ ነው፡፡
3. መስታወቱ በልጆች ተሰበረ፡፡
4. አቤል ኳሷን ለጋት፡፡
5. ነቢያት ለስርዓተ ፆታ ክበብ ሰብሳቢነት ተመረጠች፡፡
6. ሱልጣን ከኤች አይቪ ኤድስ ራሱን ይጠብቃል፡፡
7. ውሻው የታሰረበትን ሰንሰለት በጠሰው፡፡
8. ህፃናቱ በአሰሪዎቻቸው የጉልበት ብዝበዛ ተደረገባቸው፡፡
9. ዙቤይዳ ባህሏን የሚያንፀባርቅ ልብስ ለበሰች፡፡

10. እንስሳቱ ግጦሽ ቦታ ተሰማሩ፡፡

**መልመጃ ሁለት፡-**

አምስት ገቢር ዓረፍተ ነገር ከመሰረታችሁ በኋላ ወደ ተገብሮ ዓረፍተ ነገሮች ለውጡ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ቃላት አውዳዊ ፍች፣ ስለ አረፍተ ነገሮች ምክንያትና ውጤት፣ ስለ ተራኪ ጽሑፍ ምንነት፣ እንዲሁም የገቢርና ተገብሮ አረፍተ ነገር አይነቶችን ተምረናል፡፡
- ገቢር ዓረፍተ ነገር ትኩረት የሚያደርጉት ተግባሩን የፈጸመው ባለቤት ወይም የድርጊት ፈፃሚ ላይ ሲሆን፣ ተገብሮ ዓረፍተ ነገር ደግሞ ትኩረት የሚያደርጉት በተሳቢ ወይም በድርጊት ተቀባይ ላይ ነው፡፡
- ተራኪ ጽሑፍ ተከታታይነት ያላቸውን ድርጊቶች እና ሁነቶች መሰረት አድርጎ ከመነሻው እስከ መድረሻው ድረስ የሚሆነውን ነገር እየተረከ ለአንባቢ ያደርሳል፡፡ በተራኪ ጽሑፍ ውስጥ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ እንዲህ ሆነ፣ ከዚያም እንዲህ ተደረገ በሚል አቀራረብ የነገሮችን አከናወንና አፈፃፀም በድርጊት ወይም በጊዜ ቅደም ተከተል በትረካ ያቀርባል፡፡ ተራኪ ጽሑፍ ልቦለዳዊ ወይም ኢ-ልቦለዳዊ ሊሆን ይችላል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ተራኪ ጽሑፍ ምን አይነት ጽሑፍ ነው?
2. ከታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ገቢርና ተገብሮ በማለት ለዩ፡፡
   - ሀ. ፍቅርተ መጽሐፍ ገዛች፡፡
   - ለ. ደርቤ በሬውን ተሰረቀ፡፡
   - ሐ. ልጆቹ በወንድማቸው ተመሰገኑ፡፡
   - መ. ድመቶቹ ወተቱን ጠጡት፡፡
3. ለሚከተሉት ቃላት እማሬያዊ ፍች ስጡ፡፡
   - ሀ. እባብ
   - ለ. እስስት
   - ሐ. አሳማ
   - መ. ወንፊት


# ምዕራፍ ስድስት ፮

# የሰዎች ሕገ ወጥ ዝውውር

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- ከአዳመጣችሁት ምንባብ ዋናውን ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- የሰዎችን ሕገ ወጥ ዝውውር መንስኤዎችን ትገልፃላችሁ፡፡
- ስለ ሕገወጥ ሰዎች ዝውውር ጉዳት መረጃ ሰብስባችሁ ንግግር ታደርጋላችሁ፡፡
- ምንባቡን በትክክል ታነባላችሁ፡፡
- የሰዎች ዝውውር የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ታብራራላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

### "ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር"





## ቅድመ ማዳመጥ

1. ስለሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ታውቃላችሁ?
2. ለምን ሰዎች በሕገወጥ መንገድ ከሀገር የሚወጡ ይመስላችኋል?
3. ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል የየግል ሀሳባችሁን ተናገሩ፡፡

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ፡-

“የሰዎች ዝውውር” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ህጋዊ የሰዎች ዝውውር ከሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በምን ይለያል?
2. ለሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት እነማን ናቸው?
3. መዳረሻ ሀገራት የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
4. በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ወቅት ሀሰተኛ መረጃና ተስፋ የሚሰጡት እነማን ናቸው?
5. የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያቶችን ዘርዝሩ፡፡
6. ከሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዴት ራሳችንን መጠበቅ እንችላለን?
7. የአዳመጣችሁትን ምንባብ ዋና መልዕክት በአጭሩ ግለፁ፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

በ“ሀ” ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ“ለ” ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንጀል | ሀ. | ያሰለባ |
| 2 | መመልመል | ለ. | ምክንያት |
| 3 | ምንጭ | ሐ. | ድንገት |
| 4 | ተጎጂ | መ. | ማባበያ |
| 5 | በር ከፋች | ሠ. | ባለማስተዋል |
| 6 | መደለያ | ረ. | ሚተላለፉባቸው |
| 7 | የሚያቋርጧቸው | ሰ. | ማጨት |
| 8 | ግዳጅ | ሸ. | ሕገ-ወጥ ተግባር |
| 9 | በጭፍን | | ያለፈቃድ |
| | | | መነሻ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ትዕዛዝ ፡-

ስለ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ጉዳት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን የቡድናችሁን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### "የሶስቱ አንስት የስደት ታሪክ"

### ቅድመ ንባብ

### ትዕዛዝ

ከታች ለቀረቡት ቃላት በፍቻቸው ዙሪያ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ሕገ ወጥ | እንግልት |
| ዳግም | ራዕይ |
| ቋጥሮ | ጫና |

## ጊዜ ንብባ

### ትዕዛዝ:-

"የሶስቱ አንስት የስደት ታሪክ" የሚለውን ምንባብ በየግል እያነበባችሁ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ምላሽ እየሰጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ።

### "የሶስቱ አንስት የስደት ታሪክ"

ሶስቱንም የተዋወቅኋቸው በአንድ የሙያ ስልጠና ላይ ነው። አንድ የሚያደርጋቸው ሶስቱም ከስደት ተመላሽ መሆናቸውና የሙያ ስልጠና መውሰዳቸው ነው። በመጀመሪያ ገጠመኟን አሐዱ ብላ ያወጋችመኝ በምኖርበት አካባቢ የቤት እቃ መሸጫ ሱቅ ከፍታ የምትሰራ ወይንሸት ረጋሳ የምትባል ወጣት ናት። ይህች ወጣት በሕጋዊ መንገድ ወደ ተባበሩት ዓረብ ኤምሬት ለስራ ፍለጋ በመሄድ ሰርታ የተመለሰች ነበረች። የመጀመሪያ ጉዞዋን አድርጋ ሁለት ዓመት ያህል እንደሰራች አሰሪዎቿ የተወሰነ ጊዜ ያህል እረፍት ሰጥተዋት ወደ ኢትዮጵያ መጣች። እንደመጣች ግን ቤተሰቦቿ ወደሚገኙባት ደሴ ከተማ አላመራችም ነበር። እረፍቷን ጨርሳ እስክትሄድ ድረስም ከአዲስ አበባ ውልፍት አላለችም።

ከተማ ውስጥም ስትዘዋወር በአግባቡ ተሸፋፍና ነበር። ነገር ግን ከውጭ ሀገር የተላከ በማስመሰል እቃዎችን እዚሁ ገዝታ ለቤተሰቦቿ ልካ እንደነበረ ታስታውሳለች። ይህን ያደረገችበትን ምክንያት ስታብራራም ቤተሰቦቿ እና ዘመዶቿ ከእርሷ ብዙ ስለሚጠብቁ ሀገር ቤት ብትሔድ እያንዳንዱን ቤተሰብ በስጦታ እቃና በገንዘብ ማንበሽበሽ ባለመቻሏ ነበር። እናም እረፍቷን እስክትጨርስ ቤት ተከራይታ ወደ ተባበሩት አረብ ኢምሬት ተመለሰች።

አሁንም ጠቅልላ ወደ ሀገሯ ብትመለስም ቤተሰቦቿ ጋር ያስገባኛል ብላ የምታስበውን ያህል ገንዘብ ስላልያዘች በያዘቻት ጥሪት የራሷን የእቃ መሸጫ ሱቅ ከፍታ እዚያው እያደረች ኑሮዋን ተያይዛዋለች። እንደ እሷ አይነት መጠነኛ ጥሪት ቋጥረው በሀገር ላይ ለመሥራት ቢያልሙም የዘመዶቻቸውን ፍላጎት ባለማሟላታቸው ብቻ ለዳግም ስደት የሚዳረጉ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በርካታ ናቸው። ከእነዚህም አብዛኞቹ ሕጋዊ የጉዞ እና የሥራ ፈቃድ ሰነዶች ሳይኖራቸው በሕገ ወጥነት በሰው ሀገር የኖሩ እና በብዙ የስደተኝነት ቀውስ ውስጥ እያለፉ ያሉ ናቸው።

ሁለተኛዋ ወጣት አዲስ አበባ ሳሪስ አቦ አካባቢ ተወልዳ ያደገችው ነጃት ሱሌይማን ሌላዋ ታሪኳን ያካፈለችኝ ስትሆን እሷም የስደት ህይወትን ቀምሳ በቃኝ ብላ ወደ ሀገሯ የተመለሰች ሰልጣኝ ናት። ወጣቷ በሱዳን አንድ ባለ ሀብት ቤት ተቀጥራ

ትሰራ የነበረ ሲሆን በስደት ህይወት ብዙ የተለያዩ መከራዎችን ብታሳልፍም አብረን ወደ ጣልያን እንሻገራለን ካለችው የፍቅር ጓደኛዋ አንድ ሴት ልጅን አግኝታለች:: ልክ መፀነሷን እንዳወቀች ትሰራበት የነበረውን ቤት ለቃ በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል በትራንስፖርት ሀገሯ እንደገባች የምትናገረው ነጃት የልጇ አባት ተሳክቶለት ካሰበበት ጣሊያን መግባቱን ትናገራለች::

ትዳር እዚያና እዚህ እንዲሆን የፈረደባት ስደትን የምትረግመው ነጃት ጓደኞቿ ጠንክረው ሰርተው፣ የተወሰነ ጥሪት አግኝተው፣ ቤተሰብ አፍርተው ስትመለከት አራት የባከኑ ዓመታትን እንደአሳለፈች ትናገራለች:: “አሁንም አልረፈደም” የምትለው ነጃት በምግብ ስራ ስልጠና ወስዳ የእለት ጉርሷን የምታገኝበት የስራ መስክ ላይ በመሰማራት ስደት ያበረከተላትን ፀጋ (ልጇን) ማሳደግ እንደምታስብ ተናግራ ሌሎችም ወደ ውጭ ለመውጣት ከመጓጓታቸው በፊት ቆም ብለው እዚህ ያሉ አማራጮችን ማጤን የሚገባቸው መሆኑን ታስረዳለች:: ህይወት በስደት ከባድ ነው:: ሰው ተሰዶ ጥሪት ካልያዘ ለምን ይሰደዳል? በተቻለ መጠን የአቅሙን ያህል በሀገሩ ከሰራ ከሰው ሀገር የማይሻል ምንም የለም ትላለች::

*ተማሪዎች እስከ አሁን ከቀረበው ታሪክ ምን ተረዳችሁ? ሶስተኛዋ ባለታሪክስ ምን የሚገጥማት ይመስላችኋል?

“እንደ ዝምታ መካሪ እንደ ስደት ኑሮ አስተማሪ የለም” በማለት ስለስደት ህይወቷ ስጠይቃት ምላሽ መስጠት የጀመረችው ሶስተኛዋ ወጣት ብርቱካን ኪሮስ ናት፤ በአርሲ ነገሌ ተወልዳ እንዳደገች ትናገራለች:: እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ ከተማረች በኋላ ለመሰናዶ ትምህርት መግቢያ ውጤት እንዳላመጣች የተረዳችው ወጣት የተወሰነ ዓመት በአረብ ሀገር ሰርታ የራሷ የምትለውን ድርጅት ለመክፈት በአላት ህልም የተነሳ በህጋዊ መንገድ ወደ ኩዌት አቀናች:: በቤት ሰራተኝነት የተቀጠረችው ይህች ወጣት ቀንና ሌሊት ተሰርቶ የማያልቀው የአረብ ሀገር ስራ የወገብ በሽተኛ እንዳደረጋት ትናገራለች::

በወር የምታገኘውን ገንዘብ በሙሉ ለቤተሰቦቿ በመላክ እጇ ላይ ምንም ገንዘብ ባለመኖሩ እስኪሞላ ቆይ ዛሬ ቆይ ነገ ስትል ለአምስት ዓመታት በከባድ የስራ ጫና ውስጥ ሰውነቷ ላይ ያለው ስጋ አልቆ በአጥንቷ የምትሄድ ሲመስል አሁን በቃኝ በማለት የያዘቻትን ይዛ ወደ ሀገሯ ተመለሰች:: ለማገገም ከዓመት በላይ እንደ ፈጀባት የምትናገረው ብርቱካን ሰውነቷ ተመልሶ መንፈሷ ሲረጋጋ ትዳር ይዛ አንድ ልጅ ለማፍራት በቅታለች:: አሁንም በምግብ ዝግጅት ሙያ ስልጥና የራሷን ትንሽ ምግብ ቤት ለመክፈት ማቀዷን የተናገረች ሲሆን “ብልህ ከሰው ስህተት ይማራል”

የሚባለውን ብሂል ከግንዛቤ በማስገባት ከእኛ ሕይወት በመማር ራሳችሁን አድኑ በማለት ጉዳቱ ላልደረሰባቸው፤ ግን ደግሞ ስደትን ለአሰቡ ወገኖች ታሳስባለች፡፡

ለአብነት ያህል እነሱን አነሳን እንጂ የሀገራቸው መሬት እየናፈቃቸው በበረሃ ወድቀው የቀሩ፤ ከነሙሉ አካላቸው ተሰደው አካል ጉዳተኛ ሆነው የተመለሱ፤ በአቅም በጉልበታችን ሰርተን እንለወጣለን ብለው ከሀገራቸው ከወጡ በኋላ ያሰቡትና የሚሆነው አልገናኝ ብሏቸው አእምሯቸውን የሳቱትን ቤት ይቁጠራቸው፡፡ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ሄደው በደረሱበት ሀገር ያልተገባ እንግልት ላይ ከሚወድቁት በላይ የባህር ሲሳይ የሆኑትም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡ ወጣትነት ጉልበት ነው፡፡ እድሜው በራሱ የሞከሩትን የሚያሳኩበት ባይሳካ እንኳን ተጨማሪ ተስፋዎች የሚታዩበት ነው፡፡

በአፍላ የወጣትነት እድሜ ሮጦ የማይጠገበውን ጉልበት ሀገር ላይ አፍስሶ ሀገርን ከማሳደግ ይልቅ ለምን አቅማችንን፣ ላብንና ወዛችንን ላልተመጣጠነ ክፍያ እናፈስሳለን? ለምን አፍላውን እድሜያችንን፣ አጠቃላይ ማንነታችንን በ "ሕጋዊ ባርነት" እናጣዋለን? የነገ ተስፋና ጸጋዎቻችንን በራሳችን እጅ ከማጨለማችን በፊት የነገ ራዕያችንን እንዴት በሀገራችን ማሳካት እንደምንችል ለማሰብ ከራሳችን ጋር እንማከር እላለሁ፡፡

ምንጭ፡- (አዲስ ዘመን ሐምሌ 25/2013፣ ለክፍሉ እንዲመጥን ተሻሽሎ የተወሰደ)

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአነበባችሁት ምንባብ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት፣ ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

1. ከሶስቱ ባለታሪኮች ውስጥ በስደት ሕይወት ውስጥ ልጅ የወለደችው ነጃት ሱሌይማን ናት፡፡
2. "እንደ ዝምታ መካሪ እንደ ስደት አስተማሪ የለም" የምትለው ወይንሸት ረጋሳ ናት፡፡
3. ምንባቡ የስደትን ጠቀሜታ በደንብ ያብራራል፡፡
4. ሶስቱን ባለታሪኮች የሚያመሳስላቸው ከስደት ሕይወታቸው ትምህርት መውሰዳቸውና ተስፋ አለመቁረጣቸው ነው፡፡
5. ነጃት በሱዳን ቀይታዋ የግል ሆቴል በመክፈት በርካታ ገንዘብ ሰብስባ ወደ ሀገሯ ተመልሳለች፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

ከታች ለተሰጡት ቃላትና ሀረጋት ተመሳሳይ ፍቻቸውን ከምንባቡ ውስጥ ካሉት አንቀፆች ፈልጉ፡፡

1. አሐዱ ብላ (አንቀጽ 1)
2. ፀጋ (አንቀጽ 5)
3. ራዕይ (አንቀጽ 9)
4. ዕሪት (አንቀጽ 3)
5. ውልፊት (አንቀጽ 1)
6. እንግልት (አንቀጽ 8)

## መልመጃ ሶስት፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ ማስታወሻ መሰረት "የሶስቱ አንስት የስደት ታሪክ" የሚለውን ምንባብ አንብባችሁ ፍሬ ሀሳቡን በቃል አብራሩ፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

#### ገላጭ ጽሑፍ

ገላጭ ጽሑፍ አንድ ነገር ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራራና ብያኔ የሚሰጥ ወይም የአንድን ነገር የአሰራር ሂደት የሚገልፅ፣ እንዲሁም ሁነቶችንና ነገሮችን በተመለከተ ለሚነሱ ለምን፣ እንዴት፣ ምን ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ የድርሰት አይነት ነው፡፡ ገላጭ ድርሰት ሀተታውን የሚያቀርበው እንደ ተራኪ ድርሰት በጊዜ ቅደም ተከተል ተመስርቶ ሳይሆን በተጠየቅ አካሄድ ተመስርቶ ነው፡፡ ይህም ከቀላል ወደ ከባድ በመሄድ በምክንያትና ውጤት ተንተርሶ ነው፡፡

ምሳሌ፡- አልማዝ ጥልቀት ባለው የመሬት ከርሰ ምድርና እጅግ ከፍተኛ በሆነ የሙቀት ኃይል የተፈጠረ ብቻ ሳይሆን በጥንካሬው ተወዳዳሪ የሌለው ማዕድን ነው፡፡ አሁን የሰው ልጅ ከጥልቀት እየቆፈረ የሚያወጣው የአልማዝ ማዕድን ቢሆንም ከመሬት እንብርት በእሳተ ገሞራ አማካኝነት የወጣ ነው፡፡ አልማዝ እጅግ የከበረና ውድ ከመሆኑም በላይ በውስጡ ልዩና የእሳት ጨረር (ብርሃን) የሚያንፀባርቅ ግሩም ውበትና ሞገስ የሚያጎናጽፍ ጌጥ ጭምር ነው፡፡ ስለሆነም ከውስጡ የሚያንፀባርቀው የእሳት ብርሃን ጥልቅ ፍቅርን፣ ጥንካሬው ደግሞ ዘላቂነት ያለው መዋደድን ያሳያል፡፡

### መልመጃ አንድ:-

ተማሪዎች ከላይ በቀረበው ማስታወሻ መሰረት ስለ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በተመለከተ ከታች የቀረበውን ቢጋር ተመርኩዛችሁ ሁለት አንቀፅ ገላጭ ጽሑፍ ጻፉ፡፡

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምንድን ነው?

ከሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እንዴት ራሳችንና ቤተሰባችን እንጠብቃለን?

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር

የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ምን ጉዳት አለው?

### መልመጃ ሁለት:-

ጥንድ ጥንድ በመሆን የጻፋችሁትን ገላጭ ጽሑፍ ተቀያይራችሁ ስለ ሰዎች ዝውውር የሚያብራራ መሆኑንና ገላጭነቱን በተመለከተ ተነጋገሩ፡፡

## ክፍል አምስት:- ቃላት

### የቃላት ፍካሬያዊ

#### ማስታወሻ

#### ፍካሬያዊ ፍች

ባለፈው ምእራፍ ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እንዳላቸው በመገንዘብ ስለእማሬያዊ ፍች በዝርዝር አይተን ነበር፡፡ አሁን ደግሞ ስለፍካሬያዊ ፍች እንመለከታለን፡፡

ፍካሬያዊ ፍች ማለት አንድ ቃል ከጥሬ ትርጉሙ ባሻገር ሊኖረው የሚችለው ሌላ ተደራቢ ፍች ነው፡፡ ፍካሬያዊ ፍች ብዙውን ጊዜ የሚመሰረተው በንጽጽር ላይ ነው፡፡ ንጽጽሩም ከአንድ ማኅበረሰብ ባህል፣ ልማድና እምነት ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡

| ምሳሌ፡- | ቃል | ፍካሬያዊ ፍች |
|---|---|---|
| | ቀዳዳ | ነገር የማይቋጥር |
| | አልጋ | ዙፋን |
| | ድንጋይ | የማይሰማ |
| | ጎመን | አቅመቢስ |

### መልመጃ አንድ፡-

ከላይ በማስታወሻው በቀረበው ምሳሌ መሰረት ከታች ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ሙጫ
2. አልጫ
3. መሰላል
4. መዥገር
5. . አጎዛ
6. ነፋስ
7. አሳማ
8. እሾህ
9. ጅማት
10. ቁጠማ

### መልመጃ ሁለት፡-

ቀጥለው በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ፍካሬያዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የማታ <u>እንጀራ</u> ይስጥህ ብለው መረቁት፡፡
2. ሁሌም የሚገርመኝ የኤርሚያስ <u>አንበሳነት</u> ነው፡፡
3. <u>ጩልሌው</u> ደላላ አባቴን አታሎ ቤታችንን በርካሽ ዋጋ አሸጠው፡፡
4. የእሷን <u>ክብሪትነት</u> ብዙ ሰዎች ተረድተዋል፡፡
5. ታናሽ ወንድሜ በትምህርቱ <u>እሳት</u> ሆነ፡፡
6. <u>እስስት</u> የሆኑ ሰዎችን ባህርይ መረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡
7. ሕፃኑ <u>ዱባ</u> ስለሆነ ለማንሳት ከበደኝ፡፡
8. በጎጂ ሱሶች ምክንያት <u>ቤቷን</u> አፈረሰች፡፡

### መልመጃ ሶስት፡-

ከላይ ከተሰጡት ቃላት ውጭ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያላቸው አምስት አምስት ቃላት በመጻፍ በቡድን ሆናችሁ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ማስታወሻ

### የዓረፍተ ነገር ስልቶች

ዓረፍተ ነገር የተሟላ መልዕክትን የሚያስተላልፍ በስርዓት የተቀናጁ የቃላት ስብስብ ነው። ማንኛውም ዓረፍተ ነገር ሲዋቀር የተለያዩ አገልግሎቶች ይኖሩታል፡ ፡ ሁሉም ዓረፍተ ነገሮች አንድ ዓይነት ተግባር የላቸውም። በዚህም መሰረት ዓረፍተ ነገሮችን ከአገልግሎታቸው አንጻር በአራት ከፍሎ ማየት ይቻላል።

1. **ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር ፡-** ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር ስለአንድ ጉዳይ የሚያትትና የሚገልፅ የዓረፍተ ነገር ስልት ነው። ይህ ዓረፍተ ነገር በአሉታ ወይም በአዎንታ መልክ ሊቀርብ ይችላል።

አዎንታዊ ዓረፍተ ነገር አንድ ድርጊት በተወሰነ ጊዜና ቦታ፣ በተወሰነ ምክንያት የተፈፀመ ወይም የተከሰተ መሆኑን ይገልፃል።

ምሳሌ፡- ነገ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ።

አየለ ጠንቃቃ ሾፌር ነው።

አሉታዊ ዓረፍተ ነገር የአፍራሽነት ባህርይ የሚታይበት የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡ ፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በተግባሩ አንድ ድርጊት አለመፈፀሙን ወይም አለመከሰቱን ጠቋሚ ነው።

ምሳሌ፡- ነገ ትምህርት ቤት አልሄድም።

አየለ ጠንቃቃ ሾፌር አይደለም።

2. **መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር፡-** አንድን መልዕክት በጥያቄ መልክ ለማስተላለፍ ወይም ለማቅረብ የሚያገለግል የዓረፍተ ነገር ስልት ነው። መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገሮችን ለመመስረት የሚረዱ ተዋቃሪዎች እንደ ምን፣ ማን፣ እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ወዴት፣ ለምን፣ ስንት ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው። ዓረፍተ ነገሮች መጠይቃዊ መሆናቸውን የምናውቀው በአረፍተ ነገሩ መጨረሻ ላይ በሚመጣው የጥያቄ ምልክትና በድምጸቱ ነው።

   ምሳሌ፡- ኤች አይቪ ኤድስን እንዴት መከላከል እንችላለን?

   ለምን የቤት ስራህን አልሰራህም?

ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር፡- ሀሳባችንን በትዕዛዝ መልክ ለመግለጽ የሚያገለግል የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኘው ግስ በትዕዛዝ አንቀፅ የተቀመጠ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፀጉርሽን አበጥሪ፡፡

አልጋውን አንጥፍ፡፡

3. አጋኖአዊ ዓረፍተ ነገር፡- አንድን መልዕክት በመደነቅ፣ በመገረም እና በትዝብት ወዘተ. በመሳሰሉት ኃይለኛ ስሜቶች ለማስተላለፍ የሚያገለግል የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡

ምሳሌ፡- አ! እንዴት ያለች ቆንጆ ልጅ ናት፡፡

ይገርማል! ቡድናችን በሰፊ ውጤት አሸነፈ፡፡

## መልመጃ አንድ፡-

ተማሪዎች ከላይ በተሰጠው ማስታወሻ ውስጥ የተሰጡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን የዓረፍተ ነገር ስልቶች ለዩ፡፡

1. ወደ ትምህርት ቤት ስትመጡ መታወቂያችሁን ያዙ፡፡
2. ጠንክሮ መማር ለምን ይጠቅማል?
3. አካል ጉዳተኛዋ እህቴ አንደኛ በመውጣቷ ተሸለመች፡፡
4. ፋጡማ ጧት ቁርሷን አልበላችም፡፡
5. አትሌት ጥሩነሽ ድንቅ ብቃቷን አስመሰከረች፡፡
6. ዋ! አበባውን እንዳትቆርጡ፡፡
7. ሙዘይን ለምን ትምህርት ቤት አልመጣም?
8. ወደ ቤታችሁ ስትሄዱ በሩን ዝጉት፡፡
9. ሀገርን መውደድ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡
10. ጠንክሮ ባለማጥናቱ ዝቅተኛ ውጤት አመጣ፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

ከላይ በቀረቡት የዓረፍተ ነገር ስልቶች ሁለት ሁለት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ አቀላጥፎ ማንበብ፣ ገላጭ ጽሑፍ፣ የቃላት ፍካሬያዊ ፍች እንዲሁም ስለ ዓረፍተ ነገር ስልቶች ተምረናል፡፡
- አቀላጥፎ ማንበብ ማለት ፊደላትን፣ ቃላትንና ሀረጋትን በትክክል፣ በፍጥነትና መልዕክት ሰጪ በሆነ መንገድ የማንበብ ችሎታ ነው፡፡
- ገላጭ ጽሑፍ አንድ ነገር ምን ማለት እንደሆነ የሚያብራራና ብያኔ የሚሰጥ ወይም የአንድን ነገር የአሰራር ሂደት የሚገልፅ፣ እንዲሁም ሁነቶችንና ነገሮችን በተመለከተ ለሚነሱ ለምን፣ እንዴት፣ ምን ወዘተ. ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ የድርሰት አይነት ነው፡፡
- ፍካሬያዊ ፍች ማለት አንድ ቃል ከጥሬ ትርጉሙ ባሻገር ሊኖረው የሚችለው ሌላ ተደራቢ ፍች ነው፡፡ ፍካሬያዊ ፍች ብዙውን ጊዜ የሚመሰረተው በንጽጽር ላይ ነው፡፡ ንጽጽሩም ከአንድ ማኅበረሰብ ባህል፣ ልማድና እምነት ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡
- የዓረፍተ ነገር ስልቶች ከአገልግሎታቸው አንፃር ሀተታዊ፣ መጠይቃዊ፣ ትዕዛዛዊና አጋኗዊ በመባል ይታወቃሉ፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ፍካሬያዊ ፍች በመስጠት ዓረፍተ ነገሮች መስርቱባቸው

   ሀ. ድንክ　　ሐ. ምስሶ　　ሠ. መጋዝ

   ለ. ዶማ　　መ. ወንፊት　　ረ. መንጠቆ

2. የሚከተሉትን አዎንታዊ ዓረፍተ ነገሮች ወደ አሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች ቀይሩ፡፡

   ሀ. አያንቱና አስቴር ነገ ይመጣሉ፡፡

   ለ. ዘነበ ዛሬ ወደ ሐረር ይሄዳል፡፡

   ሐ. ለዓመት በዓል በግ ገዛሁ፡፡

   መ. ሶስና በማለዳ ተነስታ ቁርሷን በላች፡፡

3. ስለገላጭ ጽሑፍ ምንነትና ባህርያት አብራሩ፡፡
4. ቀጥለው በቀረቡት ቃላት በትዕዛዛቸው መሰረት ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

   ሀ. ሰበረ (መጠይቃዊ)

   ለ. ጠመጠመ (አሉታዊ)

   ሐ. አልገደለም (አዎንታዊ)

   መ. ዘጋ (ትዕዛዛዊ)

   ሠ. አሸነፈ (አጋኖዓዊ)

# ምዕራፍ ሰባት ፯

# ማኅበራዊ ግንኙነት

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- በጥልቀት አዳምጣችሁ ዝርዝ ሀሳቦችን በቃል ትገልጻላችሁ፡፡
- የማኅበራዊ ግንኙነትን አስፈላጊነት ትገልፃላችሁ፡፡
- በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ አስረጅ ጽሑፍ ትፅፋላችሁ፡፡
- ውስብስብ ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

"ጎፋ መስቃላ ዮ"





## ቅድመ ማዳመጥ

1. ማኅበራዊ ግንኙነት ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ ሰዎች በህብረት በመሆን ምን ምን ስራዎችን ያከናውናሉ?
3. የጎፋ ማኅበረሰብ በየትኛው የደቡብ ክልል አካባቢ ይገኛል?

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ:-

"ጎፋ መስቃላ ዮ" የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ፈሊጣዊ ንግግሮች ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ።

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ:-

ከታች ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች በቃላችሁ አጭር መልስ ስጡ።

1. የጎፋ ማኅበረሰብ የት አካባቢ ይገኛል? ከአዲስ አበባስ በስንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል?
2. በጎፋዎች ቋንቋ መሰረት የመስከረም ወር ምን ተብሎ ይጠራል?
3. የሚለቀሙት የችቦ ጭራሮዎች ቀጥ ያሉ መሆናቸው የምን ተምሳሌት ነው?
4. የበዓሉ ዝግጅት የሚጀምረው ከመቼ ጀምሮ ነው?
5. የጎፋዎችን ማኅበራዊ ግንኙነት ከበዓሉ አከባበር አንጻር በአጭሩ ግለፁ።

### መልመጃ ሁለት:-

"ጎፋ መስቃላ ዮ" በሚል ርዕስ በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ።

1. በጎፋ ማኅበረሰብ የበዓል አከባበር መሰረት ጎፋ መስቀላ ዮ __________ የሚወርድበት የበዓል ሥነ-ስርዓት ነው።
2. ________________ በአካባቢው ባለአባት፣ የዚያ ቀበሌ አስተዳዳሪ እና ባህላዊ መሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ነው።
3. ንግስናውን የሚሰጡት ________ የሚባሉ አንጋሾች ሲሆኑ ንጉሱ ሲሞት በጊዜያዊነት በተዘጋጀ ________________ ውስጥ የንግስና ስርዓቱን ይፈፅማሉ።

4. የጎፋዎች ባህላዊ መጠጥ ________________ ይባላል፡፡
5. ችቦ የሚሰራባቸው ጭራሮዎች ________________-ተብለው ይጠራሉ፡፡
6. የእድሜ ልክ ንግስና የሚሰጣቸው አናታቸው ላይ________________ የሚባል ዘውድ ይደፋሉ፡፡

## መልመጃ ሶስት፡-

ከታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አውዳዊ ፍች ስጡ

*ሥነ-ጽሑፍ የሰው ልጅ ገጠመኝ ማንፀባረቂያ እንዲሁም ልዩ ልዩ የሕይወት መልኮች መገለጫ ነው፡፡ የሰው ገጠመኝና የሕይወት መልክ ደግሞ ስፍር ቁጥር የለውም፡፡ ሕይወት ባለብዙ ፈርጅና ባለብዙ ቀለም መሆኗ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የሥነ-ጽሑፍ ክልል እዚህ ድረስ ነው ተብሎ ሊገደብ አይችልም ማለት ነው፡፡ ሥነ-ጽሑፍ ማንኛውንም የሰው ልጅ ገጠመኝ፣ የተከሰተንና ሊከሰት የሚችልን ነገር እንዲሁም በሰው የምናብ አድማስ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታሰብን ነገር ሁሉ ሊያካትት ይችላል፡፡ እይታውም እጅግ ሰፊ ብቻም ሳይሆን ገደብ አልባም ነው፡፡ የሰው ልጅ አያሌ ተግባራትም በሥነ-ጽሑፍ ይንጸባረቃሉ፡፡*

# ክፍል ሁለት፡- መናገር

## ትዕዛዝ፡-

በቡድን በመሆን ስለማኅበራዊ ግንኙነት ምንነትና ጠቀሜታ መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ውይይት አድርጋችሁ የደረሳችሁበትን የጋራ ሀሳብ በቃል አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ

### “የሀገራችን ምርጥ ማኅበራዊ እሴቶች”



### ቅድመ ንባብ

1. በጽሑፍ ውስጥ ፈሊጣዊ ንግግሮችን መጠቀም ምን ጥቅም ያለው ይመስላችኋል?
2. ማኅበራዊ ግንኙነት ለምን የሚያስፈልግ ይመስላችኋል?
3. በአካባቢያችሁ ሰዎች በህብረት በመሆን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ዘርዝሩ?

### ጊዜ ንባብ

**ትዕዛዝ፡-**

“የሀገራችን ምርጥ ማኅበራዊ እሴቶች” የሚለውን ምንባብ ድምጽ በማሰማት ተራ በተራ አንብቡ፡፡ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍች እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

### “የሀገራችን ምርጥ ማኅበራዊ እሴቶች”

“ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው” እንደሚባለው በሀገራችን ሰዎች ለአንድ ሰው አድካሚና እጅ እጅ የሚለውን ስራ በህብረት የመስራት ልማድ

አላቸው፡፡ በደስታና በሀዘን ጊዜ በማኅበረሰባችን ውስጥ መረዳዳትና መደጋገፍ የተለመደ ነው፡፡ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች በርካታ ተባብሮ የመስራት እሴቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ የማኅበረሰቡ ልማዶች መካከል ደቦና በሃ በግንባር ቀደምነት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## ደቦ ፡-

ደቦ ጅጊ፣ ወንፈል እና ሌሎችንም ስያሜዎች የያዘ ማህበረሰቡ በህብረት ስራዎችን ለማከናወን የሚገለገልበት በተለይም በገጠራማው የሀገራችን ክፍል በጋራ በመተባበር ስራ የሚሰራበት ባህላዊ ስርዓት ነው፡፡ በእርሻ፣ በዘር፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ ወቅት የሀገሬ ሰው ጉልበቱንና መሳሪያውን በማዋጣት ደቦ የጠራውን ሰው ይረዳል፡፡ በአንድ ሰው ጉልበት ቢገፉት ቢገፉት ፈቀቅ የማይለው ስራ በተባበረ ክንድ በአጭር ጊዜ ይጠናቀቃል፡፡ ከእርሻ ስራ ውጪ ለቤት ግንባታ፣ ለቀብርና ለሰርግ ደቦ ሊጠራ ይችላል፡፡

ደቦ ጠሪው ደቦ ለሚወጣው ሰው ምግብና መጠጥ ለማዘጋጀት ሽር ጉድ ይላል፡፡ ይህን ኃላፊነት ብዙውን ጊዜ የሚወስዱት የደቦ ጠሪው ሚስትና የጠሪው የቅርብ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ የሚዘጋጀው ምግብና መጠጥ እንደየአካባቢው የሚለያይ ሲሆን ድግሱም ወቅቱን ያገናዘበ ይሆናል፡፡

በደቦ ስራ ወቅት የአካባቢው ሰው በነቂስ ይወጣል፣ ድምፀ መረዋ የሆኑ ሰዎች እየዘፈኑ የሰራተኛውን የስራ ተነሳሽነት ይቀሰቅሳሉ፤ አባቶች ይመርቃሉ፤ ጨዋታ አዋቂዎች በጨዋታ ሰውን ያዝናናሉ፡፡ ከብቶቹ፣ አዝመራው፣ መንደሩ እና ሳር ቅጠሉ ሳይቀር በዜማ ይወደሳሉ፤ ይመሰገናሉ፡፡ አልፎ አልፎ ቀረርቶና ፉከራ የተለመደ ነው፡፡ በተመሳሳይ የእድሜ ክልል ያሉ ወጣቶች ለተለያዩ ጉዳዮች ደቦ መጠራራት የተለመደ ነው፡፡ በደቦ ውስጥ ከሚዘፈኑ ዘፈኖች መካከል አንዱ ይሄን ይመስላል፡፡

> እሽሩሩ በርዬ እሽሩሩ
> አንተ በሰራኸው ይኖራል ሀገሩ
> በሬና ገበሬ ቢጣሉም አይበጂ
> እንዲያው ሰተት ብሎ ይጠመዳል እንጂ
> በሬ የሌለው ሰው ማዕረግም አይደርሰው
> ከሸንጎ ቢወጣ ሰው አይዋሰው
> በሬ አንተን የጠላ ጎኔ እንተን የጠላ
> የገና የጥምቀት ይለምናል ጠላ

በርዬ በርታልኝ ትንፋሽህ ምንድን ነው
ምርቱ የኔ ቢሆን ገለባው ላንተ ነው
በርዬ ምሩቁ በርዬ ምሩቁ
አንተ ካልዞርክበት አይሰበር ምርቁ
በዱላ ቢመቱ በመንሽ ቢደልቁ
የበሬን ውለታ መጫወት ነው ማታ
በሰፊ ገበታ በዋንጫ ጋጋታ

*ተማሪዎች እጅ በእጅ፣ ፈቀቅ የማይል፣ በተባበረ ክንድ ለሚሉት ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

*በሃ ምን አይነት ማህነበራዊ ግንኙነት ይመስላችኋል?

## በሃ፡-

በሃ የሐረር ሴቶች እርስ በእርሳቸው ለመረዳዳት የሚያቋቁሙት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመረዳጃ ማኀበር ነው፡፡ ከበሃ በተጨማሪም አፎጫ የሚባል የሐረር ሴቶች የሚገለገሉበት ባህላዊ የመረዳጃ ማኀበር አለ፡፡ አፎጫን ከበሃ የሚለየው ነገር ቢኖር የሐረር ሴቶች በበሃ ማኀበር የሚሳተፉት በፈቃደኝነት ሲሆን የአፎጫ አባልነት ግን ባህላዊና ማኀበራዊ ግዴታ ያለበት መሆኑ ነው፡፡ ሌላው የሁለቱ ባህላዊ ማኀበራት ልዩነት ያታን የተመለከተ ነው፡፡ በአፎጫ ማኀበር ሴቶችም ወንዶችም የሚሳተፉ ሲሆን በሃ ግን ሴቶችን ብቻ የሚመለከት ነው፡፡

በሃ የእቁብ አይነት ማኀበር ሲሆን አባላቱ በየጊዜው ገንዘብ ይቆጥባሉ፡፡ የቆጠቡትን ገንዘብ በተለያዩ ሁነቶች (ደስታ ወይም ሃዘን) ሲያጋጥም ይጠቀሙበታል፡፡ ብዙውን ጊዜ የበሃ አባል የሚሆኑት ወጣት ሴቶች ናቸው፡፡ የዚህም ዋነኛው ምክንያት በሃ ከአፎጫ ይልቅ በአንፃሩ ለወጣቶቹ ሴቶች ለነፃነታቸው የሚያመች ማኀበር መሆኑ ነው፡፡ የበሃ አባላት በየሳምንቱ ይገናኛሉ፡፡ በስብሰባቸውም ላይ ሻይ ተፈልቶ ግብዣ እየተካሄደ ጸሎት ያደርሳሉ፡፡ በዚሁ ስብሰባ ላይ መዋጮ በነፍስ ወከፍ የሚሰበሰብ ሲሆን እያንዳንዷ የበሃ አባል የአቅሟን ታዋጣለች፡፡ እርዳታ በሚያስፈልግበት ጊዜም የሚሰጣት የገንዘብ መጠን ያዋጣችው ተሰልቶ ነው፡፡

ብዙውን ጊዜ የአንድ በሃ አባላት ብዛት በቁጥር ከሃያ እስከ ሰላሳ አይዘሉም፡፡ ይህም የሚሆነው አባላቱ እንዳይበዙና ለአስተዳደር እንዲያመች እንዲሁም በአባላቱ መካከል የጠበቀ ቤተሰባዊ ትስስርን ለመፍጠር በማሰብ ነው፡፡ የበሃ ማኀበር በተለይም

በሰርግና በቀብር ላይ ትልቁን ኃላፊነት በመወጣት በሐረር ሴቶች ማኅበራዊ ህይወት ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

ምንጭ፡- (ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወልደ መስቀል ስብስብ ስራዎች ለክፍል ደረጃው እንዲመጥን ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ደቦ ምንድን ነው? ለማኅበራዊ ግንኙነትስ ምን ጠቀሜታ ይሰጣል?
2. በደቦ ስራ ወቅት ምግብ የሚያዘጋጁት እነማን ናቸው?
3. ስራው በሚከናወንበት ሰዓት የሚዘፈኑ ዘፈኖች፣ ቀረርቶዎችና ሙገሳዎች አገልግሎታቸው ምንድን ነው?
4. “ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክም ለሃምሳ ሰው ጌጡ ነው” ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. የበሃ አባላት እስከ ስንት ይደርሳሉ?
6. ወጣት ሴቶች ከአፎጫ ይልቅ በሃን የሚመርጡበት ምክንያት ምንድ ነው?
7. በሃ ከአፎጫ ጋር የሚያመሳስለው ምንድን ነው? የሚያለያየውስ?

### መልመጃ ሁለት፡-

ከምንባቡ ለወጡ ፈሊጣዊ ንግግሮች ጥንድ ጥንድ በመሆን ፍች ስጡ፡፡

ምሳሌ፡- ግንባር ቀደም - ቀዳሚ (ተጠቃሽ)

1. በነፍስ ወከፍ
2. ድምፀ መረዋ
3. ሳር ቅጠሉ
4. በነቂስ ይወጣሉ

### መልመጃ ሶስት፡-

ከላይ ፍች በሰጣችሁባቸው ፈሊጣዊ ንግግሮች ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች የማኅበራዊ ግንኙነትን በተመለከተ የቀረበውን ምሳሌ ጽሑፍ በማንበብ ከተሰጡት ርዕሶች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ባለ ሁለት አንቀፅ ጽሑፍ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- የኢድ አልፈጥር በዓል የሚከበረው ሙስሊሙ ማኅበረሰብ የረመዳንን ወር ፆሞ ሲጨርስ ነው፡፡ በዓሉ ሲከበር ምዕመናኑ በአንድ ቦታ ተሰብስበው በስግደት ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ፡፡ በዓሉ ከመከበሩ በፊት ሁሉም የእለት ጉርሱን መሸፈን የሚችል የሀይማኖቱ ተከታይ የሆነ ምዕመን በአካባቢው ለሚገኙ አቅመ ደካሞች ዘካተል ፈጥር ይሰጣል፡፡ የቤተሰቡ አስተዳዳሪ አባወራ በሀገሪቱ ከሚበቅሉና ከሚመገባቸው የእህል ዘሮች የተሻለውን በመምረጥ በቤተሰቡ ቁጥር ልክ ሁለት ኪሎ ተኩል ያዋጣል፡፡ ይህም የሚሆነው አቅመ ደካሞች በዓሉን ካላቸው ጋር እኩል ተደስተው እንዲውሉ በማሰብ ነው፡፡ ይህም አንዱ የመተባበርና ጠንካራ የማህበራዊ እሴት ማሳያ ነው፡፡

ሀ. እድር
ለ. እቁብ
ሐ. የበዓል አከባበር

### መልመጃ ሁለት፡-

የፃፋችሁትን አንቀፅ ለጓደኞቻችሁ በማንበብ እርስ በእርስ ተራረሙ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### የቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች

### መልመጃ አንድ፡-

በ “ሀ” ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ“ለ” ስር ከቀረቡት ተመሳሳይ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1 | መዋጮ | ሀ. | መደጋገፊያ |
| 2 | መረዳጃ | ለ. | መዋቢያ |
| 3 | ገበታ | ሐ. | የሚሰበሰብ |
| 4 | ሚና | መ. | ጉባዔ |
| 5 | ሸንጎ | ሠ. | አስተዋፅኦ |
| 6 | ጌጥ | ረ. | ባህል |
| 7 | ልማድ | ሰ. | መጠጥ |
| 8 | ሸክም | ሸ. | ታስቦ |
| 9 | ተሰልቶ | ቀ. | ጫና |
| | | በ. | ምግብ |

## መልመጃ ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት በ"ለ" ስር ከቀረቡት ተቃራኒ ፍቻቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | | "ለ" |
|---|---|---|---|
| 1 | በህብረት | ሀ. | ዘመናዊ |
| 2 | ግዴታ | ለ. | ምርት |
| 3 | ገለባ | ሐ. | በተናጠል |
| 4 | ነፃነት | መ. | ማጠራቀም |
| 5 | ባህላዊ | ሠ. | እርግማን |
| 6 | መቆጠብ | ረ. | ባርነት |
| 7 | ምርቃት | ሰ. | ማባከን |
| | | ሸ. | መብት |

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች በቀረበው ምሳሌ መሰረት የተሰጡትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮች ወደ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ለውጡ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. አባቴ መጣ፡፡ (ነጠላ ዓረፍተ ነገር)

ለ. እኔ ደስ አለኝ፡፡ (ነጠላ ዓረፍተ ነገር)

አባቴ ስለመጣ ደስ አለኝ፡፡ (ውስብስብ ዓረፍተ ነገር)

1. ሀ. በትምህርቴ አንደኛ ወጣሁ፡፡
   ለ. ሽልማት ተሰጠኝ፡፡
2. ሀ. ምስጋናው ጠዋት ቶሎ አልተነሳም፡፡
   ለ. ምስጋናው ጠዋት ትምህርት ቤት ረፈደበት፡፡
3. ሀ. ህፃናት በእንክብካቤ ያድጋሉ፡፡
   ለ. ህፃናት ጤናማ ይሆናሉ፡፡
4. ሀ. ዘምዘም የማጠቃለያ ፈተና ደረሰባት
   ለ. ዘምዘም ጠንክራ ታጠናለች፡፡
5. ሀ. አንሻ ጎበዝ አርሶ አደር ናት፡፡
   ለ. አንሻ በግብርና ስራዋ ውጤታማ ሆናለች ፡፡
6. ሀ. ሰዎች ያለጥንቃቄ በመንገድ ላይ ይጓዛሉ፡፡
   ለ. ሰዎች የትራፊክ አደጋ ይደርስባቸዋል፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች አዎንታዊ፣ አሉታዊ፣ ትእዛዛዊ፣ መጠይቃዊና አጋኗዊ መሆናቸውን የ"√" ምልክት በመጠቀም ለዩ፡፡

| ተ.ቁ | ዓረፍተ ነገር | የዓረፍተ ነገር አይነቶች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎንታዊ | አሉታዊ | ትዕዛዛዊ | መጠይቃዊ | አጋኗዊ |
| 1 | ለምለም አስተዋይ ልጅ ናት፡፡ | | | | | |
| 2 | ወደ ወንዶ ገነት የምንሄደው መቼ ነው? | | | | | |
| 3 | ከበደ ዘፈን አይወድም፡፡ | | | | | |
| 4 | በጣም ይገርማል! ኳሷን ሰማይ አደረሳት! | | | | | |
| 5 | ሳትውል ሳታድር ወደ ክፍለ ሀገር መጓዝ አለብህ፡፡ | | | | | |
| 6 | አካል ጉዳተኞች እኩል የስራ እድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡ | | | | | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለፈሊጣዊ አነጋገር፣ ስለውስብስብ ዓረፍተ ነገር፣ ስለቃላት ተመሳሳይ እና አውዳዊ ፍች ተምረናል፡፡
- ፈሊጦች የተናጋሪውን/የፀሃፊውን ቋንቋ ውበትና ለዛ በማላበስ የአድማጭን/የአንባቢን ስሜት የሚኮረኩሩ የአነጋገር ስልቶች ናቸው፡፡
- ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ሁለትና ከዚያ በላይ ግሶች ያሉት የዓርፍተ ነገር አይነት ነው፡፡
- የቃላት ተመሳሳይ ፍች የምንለው የቃላት መዝገበ ቃላዊና ቀጥተኛ ፍች ሲሆን አውዳዊ ፍች የምንለው ደግሞ አንድ ቃል በአንድ ዓረፍተ ነገር ወይም ምንባብ ውስጥ ሲገባ የሚኖረውን ፍች ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

1. ከታች ለቀረቡት ፈሊጦች ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

   ሀ. ባዶ ቤት ለ.ዓይን አውጣ ሐ. ሆደ ባሻ መ. እግረ ደረቅ
2. ሶስት ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡
3. ማኅበራዊ ግንኙነት ከሚለው ርዕስ ምን ቁም ነገር እንደጨበጣችሁ በቃል ግለፁ፡፡

# ምዕራፍ ስምንት ፰

# ሱስ

## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- ምንባቡ ሲነበብላችሁ አዳምጣችሁ ተመሳሳይ ጽሑፍ ትጽፋላችሁ፡፡
- ሱስ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽዕኖ ትገልጻላችሁ፡፡
- የጽሑፉን ዋና ሀሳብ በተመለከተ የቃል ዘገባ ታቀርባላችሁ ፡፡
- ያዳመጣችሁትን ሀሳብ በቡድን ሆናችሁ እንደገና ታዋቅራላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

"ትምባሆ"



### ቅድመ ማዳመጥ

1. ሱስ ምንድን ነው?
2. በጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የሱስ አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
3. ሰዎች ትምባሆ ለምን የሚያጨሱ ይመስላችኋል?

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ:-

“ትምባሆ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ:-

ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ትምባሆ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የአድሬናልን ዝውውር ይጨምራል፡፡
   ለ. የልብ ምትን ይቀንሳል፡፡
   ሐ. ሆርሞኖችን በብዛት ያመነጫል፡፡
   መ. የምግብ ፍላጎትን ይቀንሳል፡፡
2. በትምባሆ ውስጥ ከሚገኙ ጎጂ ንጥረ ነገሮች ውስጥ የሚመደበው የቱ ነው?
   ሀ. ታር ሐ. ኒኮቲን
   ለ. ካርቦን ሞኖ ኦክሳይድ መ. ሁሉም
3. ኢትዮጵያ የዓለም የጤና ድርጅት ትምባሆን ለመቆጣጠር ያወጣውን አዋጅ ያፀደቀችው መቼ ነው?
   ሀ. የካቲት ሃያ አምስት ሁለት ሺ አራት
   ለ. የካቲት አምስት ሁለት ሺ አራት
   ሐ. የካቲት አስራ ሁለት ሁለት ሺ አምስት
   መ. የካቲት ሃያ አንድ ሁለት ሺ አራት
4. በዓለም ላይ በትምባሆ ምክንያት በየዓመቱ ስንት ሚሊዮን ሰዎች ይሞታሉ?
   ሀ. አምስት መቶ ሚሊዮን ሐ. አራት ሚሊዮን
   ለ. ሃምሳ ሚሊዮን መ. አስራ አምስት ሚሊዮን

5. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

ሀ.ሰዎች ትምባሆ እንዲጠቀሙ ማበረታታት

ለ.የትምባሆ ተጠቃሚዎችን ቁጥር በዓለም ላይ እንዲጨምር ማበረታታት

ሐ.የትምባሆ ጠቀሜታን ማብራራት

መ.የትምባሆን ጉዳት ማብራራት

## መልመጃ ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ቃላት አውዳዊ ፍቻቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| | "ሀ" | "ለ" |
|---|---|---|
| 1 | ትንበያ | ሀ. ፋንታ |
| 2 | ድርሻ | ለ. ተወሰነ |
| 3 | ልውውጥ | ሐ. አዘጋጀ |
| 4 | ፀደቀ | መ. ሽግግር |
| 5 | ቀረፀ | ሠ. ቁጥር |
| 6 | ያውካል | ረ. መረዳት |
| 7 | አሃዝ | ሰ. ግምት |
| | | ሸ. ይረብሻል |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር፡-

ስለ ትምባሆ ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሰረት በማድረግ የምንባቡን መልዕክት ጠቅለል አድርጋችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ፡፡

# ክፍል ሶስት፡- ንባብ

## "እኔን ያየ ይቀጣ"





## ቅድመ ንባብ

1. ከላይ በትይዩ ከቀረቡት ምስሎች ምን ተረዳችሁ?
2. በአካባቢያችሁ ወጣቶች በምን በምን ሱስ ውስጥ ተጠምደው አይታችኋል?
3. ሰዎች ወደሱስ እንዳይገቡ ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ?

## ጊዜ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

"እኔን ያዬ ይቀጣ" የሚለውን ምንባብ ድምጽ ሳታሰሙ በየግላችሁ በማንበብ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች በቃል ምላሽ እየሠጣችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡

## "እኔን ያዬ ይቀጣ"

በ2002 ዓ.ም በተሰጠው የዩኒቨርስቲ መግቢያ ፈተና ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የወላጆቹን እና የትምህርት ቤቱን ስም ከፍ አድርጎ አስጠርቷል፡፡ በ2003 ዓ.ም በዲላ ዩኒቨርስቲ የሲቪል ምህንድስና ትምህርት ክፍል ተመድቦ ወደዚያው አቀና፡፡

ለቤተሰቡ የበኩር ልጅ ሲሆን በጥሩ ሥነ ምግባር የታነፀና በትምህርቱም ጠንካራና ታታሪ ልጅ ነው፡፡

ተማሪ ቡሎ ተግባቢና አስተዋይ ልጅ በመሆኑ ከጓደኞቹ ለመግባባት ጊዜ አልፈጀበትም፡፡ ለግቢው አዲስ ቢሆንም ሰላምታ አሰጣጡ በሥነ-ምግባር ተኮትኩቶ ያደገ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከቡሎ ጋር በአንድ ዶርም የተመደቡት ስድስት ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከሁሉም ተማሪዎች በበለጠ ከተማሪ ሙጂብ ጋር በጣም ተወዳጅተዋል፡ ፡ በግቢው ውስጥ እንዲሁም ወደ ክፍልና የመመገቢያ አዳራሹ ሲሄዱ ተለያይተው አያውቁም፡፡

የትምህርት አሰጣጡ፣ የምግቡ ሁኔታው፣ የአየር ፀባዩና የቤተሰብ ናፍቆት ቢያስቸግራቸውም ሁለቱን ከመግባባት አላገዳቸውም፡፡ አንድ የትምህርት ክፍል ስለደረሳቸው በጋራ ያነባሉ፣ ይመገባሉ፣ እየተጋገዙ ጥሩ ውጤት ያመጣሉ፡፡ ቡሎ በክፍል ውስጥ በመሳተፉ መምህሮቹ ይወዱታል፡፡ በዚሁ ዓመት በትምህርቱ ከፍተኛ ውጤት አምጥቷል፡፡

በአዲስ ዓመት የመስከረምን መጥባት ተከትሎ ዩኒቨርስቲያቸው የሁለተኛ ዓመት የቴክኖሎጂ ተማሪዎችን ጠራ፡፡ ተማሪ ቡሎ ለሁለት ወር ከቤተሰቡ ጋር እረፍቱን ካሳለፈ በኋላ እንደገና ወደ ግቢ ተመልሶ ከጓደኞቹ ጋር ተገናኝቷል፡፡ ምንም እንኳን ዩኒቨርስቲውን እየለመዱት ቢመጡም አመት እየጨመረ በመጣ ቁጥር ትምህርቱም ክብደት ጫን እያለ በመምጣቱ የማንበቢያ ሰዓታቸውን ለማሻሻል ተስማሙ፤ እንቅልፋቸውን እንዴት ማሸነፍ እንዳለባቸው ግራ በተጋቡበት ሰዓት መፍትሄ ነው ያሉትን ሀሳብ ጫት በመቃም ለመነቃቃት እና በደንብ ለማንበብ ወሰኑ፡፡

ቀን ቀንን እየወለደ የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ተጠናቆ የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት አዳዲስ ኮርሶችን ተመዝግበው መውሰድ ጀምረዋል፡፡ እንደዋዛ እንቅልፍን አባሮ በማጥናት ሰበብ የተጀመረው ጫት አሁን ወደ ሱስ ደረጃ አድጎ ሲጋራን ወደማጨስም ተሸጋግሯል፡፡ ሥነ-ምግባሩ፣ ትህትናው እና ጉብዝናው እንደ ጉም በኖ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የቡሎ ሁለንተናዊ ባህሪ ተቀይሯል፡፡ ይባስ ብሎ የዶርም አባል ተማሪዎች ሲጋራ እያጨሰ አላስተኛ ብሎናል ብለው ለዶርም ተቆጣጣሪው ከሰውታል፡፡ ያኔ በጉብዝናውና በሥነ-ምግባሩ የሚወዱት መምህሮቹ በድርጊቱ ተበሳጭተው ደጋግመው መክረውታል፡፡ ቢሆንም ከዚህ ድርጊቱ ሊመለስ አልቻለም፡፡ ከጊዜ በኋላ ይህ አሳፋሪ ድረጊቱ ከዩኒቨርስቲው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ደረሰ፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ታሪክ ምን ተረዳችሁ? ባለታሪኩ ወደፊት ምን

የሚገጥመው ይመስላችኋል?

በተደጋጋሚ ተመክሮ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ተመልሶ ላይወጣ ሰፊ የሱስ ባህር ውስጥ በመስመጡ ሊመለስ አልቻለም፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች ማስታወቂያ ቦርድ ላይ ውጤታቸውን ለማየት ቆመው ይተራመሳሉ፤ ከማስታወቂያ ቦርዱ በቀኝ በኩል ከፍ ብሎ የቡሎን ከዩኒቨርስቲ መባረር የሚያሳውቅ ወረቀት ተለጥፏል፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች ደነገጡ "አመት ባለሞላ ጊዜ ውስጥ የሰው ልጅ ባህርይ እንዲህ ሲቀያየር ያሳዝናል" አለች ከመካከላቸው አንዷ ሁሉም በመገርም ተመለከቷት፡፡

ቡሎ ወደ ቤተሰቦቹ መመለስ አልፈለገም፡፡ መባረሩ አላስጨነቀውም ግን ያኔ ስለ እሱ የመሰከሩ አንደበቶች፣ ስለ እሱ ሥነ-ምግባርና ታታሪነት ያጨበጨቡ እጆች ታወሱት፡፡ አሁን ከትምህርት ተባረረ ሲባል ምን እንደሚፈጠር ሱስ ባደነዘዘው ጭንቅላቱ ማሰብ ጀመረ፡፡ ወደ ቤቱም አልተመለሰም በዚህም ምክንያት ደብዛው መጥፋት ያሳሰበቸው ቤተሰቦቹ እየተመላለሱ ቢፈልጉትም የውሃ ሽታ ሆኖባቸው እጅጉን ተጨንቀዋል፡፡

የቅርብ ጓደኛው የነበረው ሙጂብ እንደሱ ሱስ ውስጥ ገብቶ የነበረ ቢሆንም የሰውን ምክር በመስማቱ ከገባበት ሱስ ቶሎ ተመልሶ በአሁኑ ጊዜ ተመርቆ ዲላ ላይ በኮንስትራክሽን ሙያ ውስጥ ተሰማርቶ እየሰራ ይገኛል፡፡ የሰውን ምክር መስማት የተሳነው ቡሎ ግን መጨረሻው ሳያምር ብርድና ረሀብ እየተፈራረቀበት ኑሮውን በጎዳና ላይ አድርጓል፡፡ ሁሌም ጧት ጧት ለስራ የሚወጡ ሰዎች ቡሎ የቆሻሻ ገንዳ ውስጥ የጫት ገራባ ሲያገላብጥ ማየት የለመዱት ተግባር ሆኗል፡፡

በርካታ ወጣቶች ልክ እንደ ቡሎ ሳያስቡት ወደ ሱስ ውስጥ ይገቡና መውጣት ይሳናቸዋል፡፡ ቤተሰብና ሀገር ትልቅ ተስፋ ጥለውባቸው ሳለ እነሱ ግን ለቤተሰብና ለሀገር ይቅርና ለራሳቸውም መሆን አቅቷቸው አወዳደቃቸው የከፋ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ወደ ሱስ ከገቡ በኋላ በቀላሉ ለመውጣት ስለሚያስቸግር ከእንደዚህ አይነት ድርጊት መቆጠብ ይገባል፡፡

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ ሀሳብ ከያዙ እውነት፣ ትክክለኛ ሀሳብ ካልያዙ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ፤ ለመልሳችሁም ምክንያት ስጡ፡፡

1. ቡሎ ወደ ሱስ ውስጥ የገባው ከመጀመሪያውም ፍላጎት የነበረው

በመሆኑ ነው፡፡

2. ባለታሪኩ አወዳደቁ የከፋው የሰው ምክር መስማት ባለመቻሉ ነው፡፡
3. ለጥናት ተብሎ የሚጀመር ጫት መቃም ወደ ለየለት ሱስ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡
4. ለቡሎ ከዩኒቨርስቲ መባረር ምክንያት የውጤቱ መቀነስ ነው፡፡
5. በምንባቡ መሰረት ባለ ታሪኩ መጨረሻ ላይ ከሱስ ተመልሶ ከዩኒቨርስቲ ተመረቋል፡፡
6. የቡሎ የቅርብ ጓደኛ ሙጂብ የጓደኛው ግፊት ተጽዕኖ ቢያሳድርበትም ይህን ተቋቁሞ ለውጤት በቅቷል፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች ለቀረቡት ቃላት እና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. የበኩር
2. ተኮትኩቶ
3. መጥባት
4. ጠነሰሱ
5. ነጎደ
6. ይተራመሳሉ
7. ደብዛው
8. የውሃ ሽታ
9. ይሳናቸዋል
10. ከፍቶ

### መልመጃ ሶስት፡-

በምንባቡ መሰረት ወጣቱን ወደ ሱስ ውስጥ የሚያስገቡ ምክንያቶችን እና የሚያስከትሉትን ጉዳት በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በተወካያችሁ አማካኝነት በክፍል ውስጥ በቃል አቅርቡ፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### ማስታወሻ

#### ሥርዓተ ነጥቦች

በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ ሥርዓተ ነጥቦች የጎላ ድርሻ አላቸው፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ በማገልገል ላይ የሚገኙ በርካታ ሥርዓተ ነጥቦች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን እንመልከት፡፡

1. አንድ ነጥብ (•)፡- አንድ ነጥብ ይዘት ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል፡፡
   - ቃላትን በምህፃረ ቃል አሳጥሮ ለመፃፍ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ተ.መ.ድ  የተባበሩት መንግስታት ድርጅት

   - ብርና ሳንቲሞችን እንዲሁም ሙሉና ክፍልፋይ ቁጥሮችን ለመለየት

ምሳሌ፡- 6.50  ስድስት ብር ከሃምሳ ሳንቲም

2.9  ሁለት ነጥብ ዘጠኝ

2. ሁለት ነጥብ (፡)፡- ሁለት ነጥብ ከታች የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡
   - በቃላት መካከል በመግባት አንዱን ቃል ከሌላው ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ቶሎሳ፡ ምሳውን፡ በላ፡፡

   - ሰዓትና ደቂቃን ለመለየት ያገለጋል፡፡

ምሳሌ፡- 2፡30  ሁለት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ

3. ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (፡-) ፡- ሁለት ነጥብ ከሰረዝ ቀጥለው የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡
   - መሪ ሃሳቡን ተከትለው ወደሚመጡ ዝርዝር ነገሮች ለማንደርደር ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ቋንቋ ለተግባቦት ሲውል አራት ክሂሎችን መሰረት አደርጎ ነው፡፡ እነሱም፡- ማንበብ፣ መፃፍ፣ መናገርና ማዳመጥ ናቸው፡፡

   - ምሳሌ ለመጥቀስ ያገለግላል፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት፡፡ ምሳሌ፡- ዓባይ፣ ዋቤሸበሌ፣ ባሮ፣ ኦሞ፣ ጊቤ፣ ወዘተ

4. ነጠላ ሰረዝ (፣/፥)፡- ነጠላ ሰረዝ ተከታታይ የሆኑ ቃላት ለመለየት ያገለግላል፡፡
   ምሳሌ፡- ድርጅታችን ጨው፣ ስኳር፣ ዘይት፣ ወዘተ. ያከፋፍላል፡፡

5. ድርብ ሰረዝ (፤)፡- ድርብ ሰረዝ የሀሳብ አንድነት ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮች ለመለየት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- በጧት ተነሳ፤ ልብሱን ለበሰ፤ ቁርሱን በላ፤ ደብተሩን ይዞ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ፡፡

6. ትዕምርተ-አንክሮ(!)፡- ቃለ አጋኖ በመባልም ይጠራል፡፡ መገረምን፣ መደነቅን፣ ንዴታማ ትእዛዝን፣ ማሞካሸትን፣ ማድነቅን፣ ቁጣን፣ ጩኸትንና ለቅሶን የመሳሰሉትን ለማመልከት ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- ዛሬ መሄድ አለብህ! (ትእዛዝን ለመግለፅ)

7. ትዕምርተ-ስላቅ (¡)፡- ምፀትን፣ ቀልድና ተሳልቆን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- አቤት ውፍረት¡ በር አያስገባትም እኮ (ቀጭን የሆነችን ልጅ)

8. ትዕምርተ-ጥያቄ(?)፡- የጥያቄ ምልክት በመባልም ይታወቃል፡፡ ጥያቄያዊ ጽሑፎች ለመፃፍ ያገለግላል፡፡

ምሳሌ፡- የቤት ስራህን ሰርተሃል?

9. ቅንፍ ( )፡- ወይም የሚለውንም አማራጭ ቃል ተክቶ ይገባል፡፡

ምሳሌ፡- ነገ ጧት ወላጅህን (አሳዳጊህን) ይዘህ ና፡፡

## መልመጃ አንድ፡-

ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ከታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አስገቡ፡፡

ምሳሌ፡- ከየት እየመጣህ ነው

ከየት እየመጣህ ነው?

1. በአዋሽ ፓርክ ውስጥ አንበሳ ቀበሮ ጅብ ሚዳቋ ዝንጀሮ እና ጦጣ የመሳሰሉት እንስሳት ይገኛሉ
2. በርቀት እንደተቀመጠ አያት እሷም አይታው ነበር
3. ወደዚህ ስፍራ ከዚህ ቀደም መጥቶ አያውቅም
4. ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን በቂ ነው በማለት ብንያም በለጠ ተናገረ
5. የትምህርት ቤቱን ሥነስርዓት ማክበር የሁሉም ተማሪ ግዴታ ነው
6. ጎሽ የኔ አንበሳ ከመቶው ሰላሳ አመጣህ
7. ተመድ የወባ በሽታ ወረርሽኝን ለመቀነስ ጠንክሮ እየሰራ ነው
8. ሀገርን የማልማት ኃላፊነት የማን ነው
9. የቀለም አባቴ መምህሬ ጎበዝ እንድሆን መከረኝ
10. ኢትዮጵያ የበርካታ ወንዞች ባለቤት ናት እነሱም አባይ ባሮ ተከዜ ዋቤ ሸበሌ ወዘተ ናቸው

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች በቀረበው አንቀፅ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ ተገቢውን ሥርዓተ ነጥብ አስገቡ፡፡

ግጥም ___1___ ልቦለድ ___2___ ተውኔት ___3___እንዲሁም ሌሎች የሥነ-ጽሑፍ ስራዎችን የሚፈጥርና የሚጽፍ አካል ___4___ ደራሲ ይባላል ___5___ ፈጣሪ በገሃዱ ዓለም ሰውና ተፈጥሮን እንደፈጠረ ሁሉ ደራሲም በሥነ-ጽሑፍ ዓለም የራሱን ሰዎች ___6___ ተፈጥሮ ___7___ ሀሳብና ሌሎች ነገሮችን ምናባዊ አድርጎ ይስላል 8___ ነፍስ ይዘራባቸዋል ___9___ ቢፈልግ ገድላቸዋል ___10___ሲያሻውም እንደገና ሊያሥነሳቸው ይችላል ___11___ ባጠቃላይ የተፃፈው ጽሑፍ ድርሰት ሲባል _ 12___ ጸኃፊው ደግሞ ደራሲ ይባላል ___13___

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ትዕዛዝ፡-

በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ቃላት ከታች በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛው ቦታቸው አስገቡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ብልሀቶችን | ትልቅ | ክፍፍል |
| ውጤት | በለጋ | ለስቃይ |
| በፅኑ | ልማዳዊ | የውዴታ ግዴታ |

1. የተለያዩ የጥናት __________በመጠቀም ውጤታማ መሆን አለብን፡፡
2. ____________ እድሜው በርካታ ኃላፊነቶችን ተቀብሏል፡፡
3. ግብር መክፈል የሁሉም ሰው ___________ ነው፡፡
4. የወላጆቿንና የመምህሮቿን ምክር ባለመስማቷ ________ተዳርጓል፡፡
5. ሞሚና ___________ በመታመሟ ሆስፒታል ገባች፡፡
6. ጎጂ ________ ድርጊቶችን መዋጋት የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡
7. በቤተሰብ ውስጥ ትክክለኛ የስራ ________ መኖር አለበት፡፡

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ትእዛዝ፡-

በምሳሌው መሰረት አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሌራ መጽሐፍ ማንበብ ስለሚወድ የተረት መጽሐፍ ገዛ።

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

- በዚህ ምራፍ ስለስርዓተ ነጥቦች፣ ስለውስብስብ ዓረፍተ ነገር፣ ስለአውዳዊ ፍች ተመልክተናል።
- ስርዓተ ነጥቦች በወረቀት ላይ የሰፈረ ሀሳብ መልዕክቱ ግልፅ ሆኖ እንዲተላለፍ ለማድረግ የጎላ ድርሻ አላቸው። በጽሑፉ ላይ ሥርዓተ ነጥቦችን አስተካክሎ ካለመጠቀም የተነሳ የዓረፍተ ነገሮቹ ትርጉም ሊያሻማ፣ ሊዛባ ወይም ሙሉ በሙሉ ሊለወጥ ይችላል።
- ተዘውታሪ ቃላት በእለት ተእለት ሕይወታችን በብዛት የምንጠቀምባቸው (የምንገለገልባቸው) ቃላት ናቸው።

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. ከታች በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን ስርዓተ ነጥቦች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱW

| | | | |
|---|---|---|---|
| ? | ፣ | ¡ | ፤ |
| ! | ። | “ ” | ፡- |

2. ቀጥለው ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ውስብስብ ዓረፍተ ነገር የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አልማዝ ትምህርት ቤት መጣች።

   ለ. ኢብራሂም ጠንክሮ ስላጠና ጥሩ ውጤት አመጣ።

   ሐ. መምህሩ በመኪና ወደ መርካቶ ሄደ።

   መ. የትምህርት ቤታችን ቤተ መጻሕፍት ግንባታ ተጠናቀቀ።

3. ስለሱስ አስከፊነት የተገነዘባችሁትን በአጭሩ በቃል አብራሩ።

# ምዕራፍ ዘጠኝ ፱

# የሀገር ፍቅር


## ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ የጽሑፉን ፅንሰ ሀሳብ ከሕወታችሁ ጋር ታዛምዳላችሁ ።
- የሀገር ፍቅርን ምንነት ትገልፃላችሁ።
- የመረጣችሁትን ጽሑፍ ለተለያየ ዓላማ ታነባላችሁ።
- የሀገር ፍቅር መገለጫዎችን ለይታችሁ ትዘረዝራላችሁ።
- ምስሎችን ትገልፃላችሁ።

## ክፍል አንድ ፡- ማዳመጥ

"የአድዋ ድልና የሀገር ፍቅር ስሜት"










## ቅድመ ማዳመጥ

1. ርዕሱና የቀረቡት ምስሎች ምን ግንኙነት ያለው ይመስላችኋል?
2. ሀገር ማለት ለእናንተ ምንድን ነው?
3. የሀገር ፍቅር ምንድን ነው? በምን በምን የሚገለፅ ይመስላችኋል?

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ፡-

“የአድዋ ድልና የሀገር ፍቅር ስሜት” በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመፃፍና በንቃት በማዳመጥ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክል ከሆኑ እውነት፣ ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሀሰት በማለት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. አስራ ሰባት አንቀፆች ያሉት የውጫሌ ውል የተደረገው ሚያዝያ 25/1880 ዓ.ም ነው፡፡
2. የአድዋ ጦርነት የተካሄደው  በውጫሌ አካባቢ ነው፡፡
3. እቴጌ ጣይቱ ለአድዋ ጦርነት ድል መገኘት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡
4. ለመጀመሪያ ጊዜ የአድዋ ድል በዓል የተከበረው 1895 ዓ.ም ነው፡፡
5. በምንባቡ ሀሳብ መሰረት ጦር ሜዳ ሄዶ ያልተዋጋ ዜጋ አርበኛ ሊሆን

አይችልም።
6. አርበኝነት የሚለው ቃል ክብር፣ ማንነትና ተግባር የሚገለፅበት ቃል ነው።

### መልመጃ ሁለት:-

ከታች በሳጥን ውስጥ የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በቀረቡት ያልተሟሉ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ አውዳቸው አስገቡ።

| | | |
|---|---|---|
| ገድል | ለመቀራመት | መና |
| የጋራ ክንዳቸውን | ሉዓላዊነት | የተከናነበበት |
| አይበገሬ | መናገሻ | አርነታቸውን |

1. በሀገር ____________ላይ ከመጣ ጠላት ጋር ድርድር አያስፈልግም።
2. አባቶቻችን ለሀገር ፍቅር ሲሉ የፈፀሙትን ____________እኛ ማስቀጠል አለብን።
3. የሀገር ፍቅር ስሜት ከሰማይ የሚወርድ -------- ሳይሆን በጠንካራ ስራ የሚገለፅ ነው።
4. አውሮፓዊያን የአፍሪካን አህጉር በቅኝ ግዛት____________በርካታ ስልቶችን ተጠቅመዋል።
5. የአፍሪካ ሀገራት____________ለማግኘት በርካታ ተጋድሎ አድርገዋል።
6. ዜጎች --------- አስተባብረው ሀገራቸው በምትፈልገው የስራ መስክ መሰማራት አለባቸው።
7. የጀግኖች አባቶቻችን_______-ስሜት ሀገራችን ታፍራና ተከብራ እንድትኖር አድርጓል።
8. አጼ ምኒሊክ ወደ አድዋ የዘመቱት ከ____________ከተማቸው በመነሳት ነው።
9. የአድዋ ጦርነት ወራሪው የኢጣሊያ ጦር የሽንፈትን ካባ_________ነው።

## ክፍል ሁለት:- መናገር

### ትዕዛዝ

ከታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ

### የደረሳችሁበትን ድምዳሜ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

1. የሐገር ፍቅር ለምን ያስፈልጋል? ምንስ ጥቅም አለው?
2. በአሁኑ ሰዓት ለሀገራችሁ ምን አተዋፅኦ እያደረጋችሁ ትገኛላችሁ? ወደ ፊትስ ምን ለማድረግ አስባችኋል?

## ክፍል ሶስት፡- ማንበብ




### "የልብ ወጌሻው"

### ቅድመ ንባብ

1. ከላይ ከቀረበው ርዕስና ፎቶው ምን ተረዳችሁ?
2. ለሀገራችን ትልቅ አስተዋፅኦ ካደረጉ ኢትዮጵያውያን መካከል የምታውቋቸውን ሰዎች ስም ተናገሩ።
3. በሀገራችን ብቸኛ ስለሆነው የልብ ቀዶ ጥገና ማዕከል ምን ታውቃላችሁ?

### ጊዜ ንባብ

#### መልመጃ አንድ

"የልብ ወጌሻው" የሚለውን ምንባብ በየግላችሁ ድምጻችሁን ሳታሰሙ አንብቡ።

መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ ስጡ።

## "የልብ ወጌሻው"

የዛሬ 43 ዓመት ገደማ በ1970 በአሜሪካን ነው በኢትዮጵያ የልብ ህክምና ማዕከል የማቋቋም ሀሳብ የተጠነሰሰው፤ በልብ ህክምና ሙያ ለመሰልጠን (ስፔሻላይዝድ ለማድረግ) በዶክትሬት ዲግሪ የተመረቅኩበትን የትምህርት ማስረጃና የወደፊት ፍላጎቴን የሚገልጽ ሃሳብ ለኒዮርክ ዩኒቨርስቲ አቀረብኩ ።ቃለ መጠይቅ ያደረገችልኝ ፕሮፌሰር የምንቀበለው አስር ሰዎችን ነው፤ አንተ የተቀመጥከው አስረኛ ላይ ነው፤ ባቀረብከው ማመልከቻ ውስጥ ጥሩና ደስ የሚሉ ነገሮች አይቻለሁ፤ ስላቀድካቸው ነገሮች ከአንደበትህ መስማት እፈልጋለሁ፤ እውነት ትምህርቱን ስትጨርስ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ በልብ ህክምና ትሰራለህ? በማለት ስትጠይቀኝ አዎ! በማለት መለስኩላት።

ፕሮፌስርም ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ የልብ ህክምና ሆስፒታል በሌለበት፣መስሪያ ቤት በሌለበት፣ ባለሙያ በሌለበት፣ እንዴት ነው የልብ ህክምና እሰራለሁ የምትለው ሲሉ ደጋግመው ጠየቁኝ። እኔም በመላ ልወጣው እንደምችል ነገርኳቸው ።

ወደ ቤቴ ስመለስ ፊቴ ላይ የመከፋትና የሀዘን ስሜት ያየችው ባለቤቴ፣ ምነው ተከፋህ አልተቀበሉህም እንዴ? በማለት ጠየቀችኝ። መቀበሉንስ ተቀብለውኛል። ነገር ግን አራት ነገሮች አርግዤ መጣሁ አልኳት፤ የልብ ሆስፒታል ለመገንባት ውድና ልዩ የሆኑትን የህክምና መሳሪያዎች ማሟላት፣ የልብ ሃኪም ማፍራትና ሆስፒታሉን በገንዘብ አቅም ዘላቂና ቀጣይነት ያለው አገልግሎት እንዲሰጥ ማስቻል የሚሉት በዶክተር በላይ አበጋዝ የተረገዙት ራዕዮች መሆናቸውን ዘርዝረው አስረዷቸው ።

ለዚህ ራዕያቸው ሳይታክቱ የወጡና የወረዱት ዶክተር በላይ አበጋዝ፣ ሆስፒታሉን በኢትዮጵያ ህዝብና በሼህ ሙሃመድ ሁሴን አሊ አላሙዲ ትብብርና ድጋፍ አሰርተው በ2001 ዓ.ም አስመርቀዋል። ውድ የሆኑ ዘመናዊ የልብ ቀዶ ህክምና መሳሪያዎችንም በአጋር ድርጅቶች አሟልተዋል። የልብ ቀዶ ጥገና ሃኪሞችንም በሚኒያ ፖሊስ የልብ ቀዶ ሃኪም በሆኑት በዶክተር ቪብ ክሽንትና ታዋቂ በሆነው የህንድ ናርያና ሆስፒታል በሰለጠኑና ዛሬ ለተደረሰበት ደረጃ ማድረስ የቻሉ የአገር ባለ ውለታ ናቸው።

እኚህ የአገር ባለውለታ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት የምስጋናና የእውቅና የክብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። የተሰበረ ልብ ጠጋኙ ይህ ሽልማት ቢያንስባቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይደለም። በኢትዮጵያ በየአመቱ 50 ሺህ ህጻናት ከልብ በሽታ ጋር

ይወለዳሉ፡፡ በተጨማሪም ከ50 እስከ 60 ሺህ የሚሆኑት ደግሞ ከተወለዱ በኋላ የልብ በሽተኛ ይሆናሉ፡፡ ህክምናውን ባለማግኘታቸው ይሞታሉ፡፡ ይህንን ታሪክ ለመቀየር ላለፉት 41 ዓመታት የደከሙትን ኢትዮጵያዊ ሁሉም ወገን ሊያመሰግንና አርአያነታቸውን ሊከተል ይገባል፡፡ የዶክተር በላይን መንገድ ልብ ብሎ ላስተዋለ ልባም ሁሉ የሚናገረው ሀቅ ማንም ቢሆን በተሰማራበት የሙያ መስክ ሊደክምለትና ሊያሳካው የሚገባው የሀገር ውለታ እንዳለበት ነው፡፡

ምንጭ፡- (አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ቁጥር 285፣ ሰኔ 15/2011ዓ.ም)

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልሱ፡፡

1. በሀገራችን በየዓመቱ ስንት ህጻናት ከልብ በሽታ ጋር ይወለዳሉ?
2. የባለታሪኩ ራዕይ ምን ነበር? አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡
3. ዶክተር በላይ አበጋዝ አራት ነገሮችን አርግዤ መጣሁ ካሉት ውስጥ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡
4. ባለታሪኩ ለሀገርና ለወገን ላደረጉት አስተዋፅኦ የእውቅና ሽልማት የተበረከተላቸው ከማን ነው?
5. የልብ ህሙማን መርጃ ማዕከሉ መቼ ተመረቀ?
6. ከዶክተር በላይ አበጋዝ ታሪክ ምን ቁም ነገር አገኛችሁ?

### መልመጃ ሁለት፡-

ቀጥለው ለቀረቡት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

1. መላ
2. አርግዤ
3. ሳይታክቱ
4. አጋር
5. ውለታ
6. ልባም
7. ሀቅ
8. ወጌሻ
9. እውቅና
10. መከፋት

### መልመጃ ሶስት፡-

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን የንባብ ማስታወሻ በመውሰድ "መረጃን ለማግኘት ማንበብ" የሚለውን የንባብ ዓላማ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን የአሃዝ (የቁጥር) መረጃዎች ከታች በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ ሙሉ፡፡

የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከ2003 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም የፀረ ኤች አይቪ ህክምና አገልግሎት የመድኃኒት ስርጭት መጠንን እንደሚከተለው ይገለፃል፡ ፡ በ2003 ዓ.ም መድኃኒቱን ከጀመሩ 333,434 ሰዎች መካከል 247,805 ያህሉ መድኃኒት በመውሰድ ላይ ያሉ ሲሆን ይህ በመቶኛ ሲሰላ 42.65 % ይሆናል፡ ፡ በ2004 ዓ.ም መድኃኒቱን ከጀመሩ 342,954 ሰዎች መካከል ደግሞ 270,543 ያህሉ መድኃኒቱን ወስደዋል፤ ይህ በመቶኛ ሲሰላ 44.92% ነው፡፡

የ2005 ዓ.ም ስንመለከት ደግሞ መድኃኒቱን ከጀመሩ 439,301 ሰዎች መካከል 308,860 ያህሉ መድኃኒቱን የወሰዱ ሲሆን ስሌቱ 41.49 % ነው፡፡ በ2006 ዓ.ም ደግሞ ከ492,689 ሰዎች መካከል 344,344 ሰዎች መድኃኒቱን ተጠቅመዋል፡፡ ይህ ደግሞ በመቶኛ ሲሰላ 42.73% ነው፡፡ (ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር)

| ከ2003-2006 ዓ.ም የፀረ ኤች አይቪ መድኃኒት ስርጭት መጠንን የሚያሣይ ሰንጠረዥ | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2003 ዓ.ም | | | 2004 ዓ.ም | | | 2005 ዓ.ም | | | 2006 ዓ.ም | | |
| የጀመ[illegible] | የወሰዱ | በ% | የጀመሩ | የወሰዱ | በ% | የጀመሩ | የወሰዱ | በ% | የጀመሩ | የወሰዱ | በ% |
| 333,434 | 247,805 | 42.65 | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | |

## ክፍል አራት፡- መጻፍ



## ትዕዛዝ

ከላይ የቀረበውን ምስል መሰረት በማድረግ ስለ አድዋ ጦርነት ሁለት አንቀፅ ፃፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

### ያልተዘወተሩ ቃላት

#### መልመጃ አንድ፡-

ከታች በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ለተሰመረባቸው ያልተዘወተሩ ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

1. ወንደሰን ከባላጋራዎቹ ጋር ከረጅም ዓመታት በኋላ እርቅ ፈፀመ፡፡
2. ሸማኔው የሰራልኝ ቡልኮ ለአይን ያሳሳል፡፡
3. በኮባ ቅጠል የተጋገረው ዳቦ ይጣፍጣል፡፡
4. ሁሉም ቤተሰብ ከሰፊው ማዕድ የአቅሙን ያህል ተቋደሰ፡፡
5. ሙክታር ጭራሮ ለመልቀም ወደ ጫካ ሄደ፡፡
6. ፈተና ሲደርስ ጉድ ጉድ ማለት መፍትሄ አይሆንም፡፡
7. ለሰርጉ በተጣለው ዳስ ውስጥ ጭፈራው ደርቷል፡፡
8. ንጉሱ የንግስናውን ዘውድ ደፋ፡፡
9. ለዓይን ያዝ ሲያደርግ ጉዞውን ጀመረ፡፡
10. ለጊዜያዊ ጥቅም ብሎ ሀገርን የሚጎዳ ተግባር መፈፀም ተገቢ አይደለም፡፡

#### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች የቀረበውን ግጥም በማንበብ ለተሰመረባቸው ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

ሁለት በሬ ሰዎች ሲያልፉ በጎዳና

እቃ መሬት ወድቆ ብልጭ ሲል አዩና

ተሽቀዳድመው ሄደው ከቦታው ሲደርሱ

ተፎካከሩበት ሁለቱም ሊያነሱ፡፡

በኋላም ተማተው በጥፊ በጡጫ

አንደኛው ነጠቀ በጉልበቱ ብልጫ

አገላበጠና ቢመለከት ፈጥኖ

እቃውን አገኘው ማበጠሪያ ሆኖ፡፡

እስኪ ሁላችሁም በሉ ፍረዱት

እሱ ራሰ በራ ጠጉር የለበት

ሮጦ ተማቶ ቀምቶ ቢያመጣ

ምን ያድርግለታል ሚዶ ለመላጣ፡፡

(ከበደ ሚካኤል፣ ብርሃነ ህሊና፣ 1961)

1. በጎዳና
2. ተሽቀዳድመው
3. ተፎካከሩበት
4. ተማተው
5. በጉልበቱ
6. አገላበጠና
7. ፍረዱት
8. ሚዶ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ትዕዛዝ፡-

ቃላትን በትክክለኛ ቅደም ተከተላቸው አዋቅራችሁ ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

1. ቤት ገባ ሀኪም ስለገጨው መኪና፡፡
2. ተዳረገች ስለማትጠብቅ ለጽኑ የግል ንፅህናዋን ህመም፡፡
3. ያስፈልጋል ከውጭ ለመጠበቅ ሀገርን ጠላት አንድነት፡፡
4. ሰርተዋል ሁሉም ተማሪዎች የቤት ስራውን በጥሩ ሁኔታ፡፡
5. ያስፈልጋል ንፅህናን መጠበቅ የአካባቢ መጠበቅ የውሃ ብክለትን ለመከላከል፡፡
6. ትላንትና ማታ የገዛችልኝ ጠፋብኝ ቦርሳ አክስቴ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለንባብ አይነቶችና ዓላማ እንዲሁም ስለሀገር ፍቅር ምንነትና መገለጫዎች ተምረናል፡፡
- የንባብ ዓይነቶች ከፍጥነት (መረጃ ከማግኘት) አንፃር የዝግታ ንባብ፣ የፍጥነት ንባብ፣ የገረፍ ገረፍ ንባብ ወዘተ. በማለት ይከፈላሉ፡፡
- ሰዎች ለተለያዩ ዓላማዎች ያነባሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ፡- ለጥንቃቄ፣ ለመዝናናት፣ አዲስ ነገር ለመማርና ለማወቅ እንዲሁም መረጃን ለማግኘት ወዘተ. የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- የሀገር ፍቅር ማለት ሀገርን የሚጠቅም ስራ መሰራት፣ መስዋዕትነትን መክፈል ወዘተ. ማለት ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

ከታች ለቀረቡት ከምዕራፉ የወጡ ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡፡

7. አምስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡
1. የንባብ አይነቶችና ዓላማዎችን ዘርዝሩ፡፡
2. የሀገር ፍቅር ምንድን ነው? መገለጫዎቹንም ዘርዝሩ፡፡

# ምዕራፍ አስር ፲

# የቃል ግጥም

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ተምራችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ፡-

- ጽሑፉን አዳምጣችሁ ጭብጡን በቃል ትገልጻላችሁ፡፡
- ለቃላዊ ግጥም ብያኔ ትሰጣላችሁ፡፡
- የቃል ግጥም አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ዜማውን ጠብቃችሁ ግጥም ታነባላችሁ፡፡



## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### የቃል ግጥም



## ቅድመ ማዳመጥ

“ቃላዊ ግጥም” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ከማዳመጣችሁ በፊት የቀደመ እውቀታችሁን መሰረት በማድረግ የሰንጠረዡን ሁለት ረድፎች በደብተራችሁ ላይ በትክክል ሙሉ፡፡ ምንባቡ ካለቀ በኋላ ተመልሳችሁ ያወቅሁት የሚለውን ክፍል በትክክል ሙሉ፡፡

| ቃላዊ ግጥም | | |
|---|---|---|
| ስለቃላዊ ግጥም የማውቀው | ስለቃላዊ ግጥም ማወቅ የምፈልገው | ስለቃላዊ ግጥም ተጨማሪ ያወቅሁት |
| - | - | - |
| - | - | - |
| - | - | - |
| - | - | - |

## ጊዜ ማዳመጥ

### ትዕዛዝ፡-

“የቃል ግጥም” የሚለውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን ማስታወሻ በመያዝ በንቃት አዳምጡ፡፡ መምህራችሁ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

## ድህረ ማዳመጥ

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች የቀረቡት ጥያቄዎች የያዙት ሀሳብ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት በምንባቡ መሰረት መልሱ፡፡

1. ቃላዊ ግጥም ከትውልድ ወደ ትውልድ በጽሑፍ የሚተላለፍ የሥነ-ቃል አይነት ነው፡፡
2. የቃላዊ ግጥም ባለቤት ማኅበረሰቡ (ህዝቡ) ነው፡፡
3. የአንድ ማኅበረሰብ ባህል በቃላዊ ግጥሞች አማካኝነት ጎልቶ ይወጣል፡፡

4. ቃላዊ ግጥሞች የቋንቋ አጠቃቀማቸው በዘፈቀደና ያልተቆጠበ ነው፡፡
5. የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በጽሑፍ መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት ቃላዊ ግጥምን ይጠቀሙ ነበር፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

በ "ሀ" ስር ለቀረቡት ቃላት በ "ለ" ስር ከቀረቡት ቃላት ተመሳሳያቸውን በመፈለግ አዛምዱ፡፡

| "ሀ" | | "ለ" | |
|---|---|---|---|
| 1 | ክስተት | ሀ. | መጀመሪያ |
| 2 | ደራሲ | ለ. | ያበለጽጋል |
| 3 | ነጎደ | ሐ. | ጸኃፊ |
| 4 | ጎልቶ | መ. | የማይዘረዝር |
| 5 | መነሻ | ሠ. | በፍጥነት ሄደ |
| 6 | አስማምቶ | ረ. | ግልጽ ሆኖ |
| 7 | ያጎለብታል | ሰ. | አሻራ |
| | ቁጥብ | ሸ. | አጋጣሚ |
| | | ቀ. | መርማሪ |
| | | በ. | አስተካክሎ |

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

### ተግባር አንድ፡-

በአካባቢያችሁ እናንተ ወይም ሌሎች ሰዎች የሚያዜሟቸውን ቃላዊ ግጥሞች ሰብስባችሁ አምጡና ተወያዩባቸው፡፡

### ተግባር ሁለት፡-

ከሰበሰባችኋቸው የቃል ግጥሞች ውስጥ አንዱን በመምረጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በክዋኔ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ንባብ

### ቅድመ ንባብ

1. ቀጥሎ የቀረበው ምስል ምንን የሚገልጽ ይመስላችኋል?
2. ቃላዊ ግጥም ከጽሑፋዊ ግጥም በምን የሚለይ ይመስላችኋል?
3. የምታውቋቸውን የቃላዊ ግጥም አይነቶች ዘርዝሩ፡፡

### ጊዜ ንባብ

#### ትዕዛዝ

“ቃላዊ ሀብቶቻችን” የሚለውን ምንባብ ድምጻችሁን ሳተሰሙ በጥሞና አንብቡ፤ መምህራችሁ በየመሀሉ ለሚጠይቋችሁ ጥያቄዎችም ተገቢውን ምላሽ በቃል ስጡ፡፡

#### “ቃላዊ ሀብቶቻችን”



የቃል ግጥም በግጥም መልክ ከሚቀርቡ ወይም ከሚዜሙ የሥነ-ቃል ዓይነቶች ውስጥ የሚመደብ ነው፡፡ የቃል ግጥም ዓይነቶች በጣም በርካታ ናቸው፡፡ እነሱም፡- የአውዳመት፣ የፉከራ፣ የልመና፣ የሙሾ፣ የስራ ግጥሞች ወዘተ. በቃላዊ ግጥም ውስጥ የሚመደቡ ናቸው፡፡ የቃል ግጥሞች እንደየሁኔታው ሊዜሙ ወይም በእንጉርጉሮ ሊቀርቡ ይችላሉ፡፡ ቃላዊ በመሆናቸው በአብዛኛው አጫጭር ናቸው፡፡ እነዚህ ቃላዊ ግጥሞች ምጣኔ፣ ምትና ዜማ አላቸው፡፡ ግጥሞቹ በአብዛኛው በእኩል ጊዜ እንዲያልቁ ሆነው የተመጠኑ ሀረጋትን ይይዛሉ፡፡ የተመጠኑት ሀረጋት

በተወሰነ ጊዜ ሲደጋገሙ ደግሞ ምትን ይፈጥራሉ፤ ሲነበቡም ዜማ አላቸው፡፡ ግጥሙ እንደሚገልፀው ስሜት ዜማው ይለያያል፡፡

በአብዛኛው የገጠሩ ህዝብ በጋራም ሆነ በተናጥል አንድ ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ ስራውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት ስለሚያግዘው ቃላዊ ግጥሞችን እየደረደረ ያንጎራጉራል፤ ይዘፍናል፤ ይጨፍራል፡፡ በተለያዩ ቡድናዊ የስራ አጋጣሚዎች ላይ ለምሳሌ በአጨዳ፣ በአረም፣ በቤት ስራ ጊዜ ወዘተ. ስራዎችን ሲያከናውን ያዜማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለያዩ ማኅበራዊ አጋጣሚዎች ለምሳሌ በሰርግ፣ በለቅሶ፣ በጦርነት ወቅት ህዝቡን ለማነቃቀትና ስሜትን ለመግለፅ የሚቀርቡ እንደ እንጉርጉሮ፣ ፉከራና ቀረርቶ የመሳሰሉት ቃላዊ ግጥሞች ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ የተወሰኑትን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

*ተማሪዎች እስካሁን ከቀረበው ምንባብ ምን ተረዳችሁ? በቀጣዩ የምንባብ ክፍልስ ምን አይነት የቃል ግጥም የሚቀርብ ይመስላችኋል?

ሀ. የእርሻ ላይ ግጥሞች

እኔስ አርሳለሁ አልማረርም፣

ችግር በወንጭፍ አይባረርም፡፡

ለ. በልጆች ጨዋታ የሚዜሙና የሚገጠሙ

ድንቡሼ ገላ ድንቡሼ ገላ፣

የአብሽ ገለባ፣

ሜዳ ነው ብዬ ገደል ልገባ፡፡

ገደል ገብቼ ልወጣ ስል፣

ጅቡ መጣብኝ ከእግሬ ስር፡፡

ሐ. በቡሄ በዓል ጊዜ የሚዜሙና የሚገጠሙ

እዚያ ማዶ (ሆ) ጭስ ይጨሳል (ሆ)

አጋፋሪ (ሆ) ይደግሳል (ሆ) ...

መ. የሽለላ የቃል ግጥም

ዓባይ ጥቁር ነበር ከሰል የመሰለ፣

እየቀላ መጣ ደም እየመሰለ፡፡

ሰ. የፉከራ ቃል ግጥም

በል በለውና ጉልበት ጉልበቱን፣

እያነከሰ ይውጣው ዳገቱን፡፡

በአጠቃላይ የቃል ግጥሞች የአንድን ማኅበረሰብ የአኗኗር፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ ወዘተ. ልማዶችን የሚያንፀባርቁ በመሆናቸው እንደሌሎች ቅርሶች ሁሉ እነዚህን ቃላዊ ሀብቶች ልንጠብቃቸው ይገባል፡፡

(አንተነህ፣ 2001፣ የአማርኛ ሥነ-ቃል አጭር ቅኝት እና ዘሪሁን፣ 1992፣ የሥነ-ጽሑፍ መሰረታውያን፡፡ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የተወሰደ)

## ድህረ ንባብ

### መልመጃ አንድ፡-

ቀጥለው ለቀረቡት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. የቃል ግጥም አይነቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. ቃላዊ ግጥሞች በአብዛኛው የሚከወኑት በየት አካባቢ ነው?
3. ሰዎች በጋራም ሆነ በተናጠል ስራ ሲሰሩ ቃላዊ ግጥሞችን ለምን ያዜማሉ?
4. በአብዛኛው ቃላዊ ግጥሞች ቅርጻቸው ለምን አጫጭር ይሆናሉ?
5. በቃላዊ ግጥም የሚዳሰሱት የማኅበረሰቡ ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?

### መልመጃ ሁለት፡-

ከታች የቀረቡትን የቃል ግጥሞች አይነት ለይታችሁ ተናገሩ፡፡

ምሳሌ፡- እንኳን ጥሬውን ይብላው ዱቄቱን፣

በሬ አይደለም ወይ ያቀናው ቤቱን፡፡ የእርሻ ቃላዊ ግጥም

1. መታመን ነው እንጂ የሰው ቁም ነገሩ፣

ሞትማ ግብሩ ነው ለሰው ልጅ ባገሩ፡፡

2. እንዳላይሽ እንዳላይሽ፣
   ወርቁን ጋረዱት እናትሽ፡፡

3. ይህ አረም የሚሉት በጣም አደገኛ፣
   ጧት ማታ ቢነቅሉት አሁንም አፍለኛ፡፡

4. ገዳይ በየበሩ በየሽንተረሩ፣
   ይፈለግ የለም ወይ የአዳኝ ውሻ ዘሩ፡፡

5. በለው በንጌ ባፈ ድምድሙ፣
   የማታ ጮራ ሲመስል ደሙ፡፡

6. አይኔን ግንባር ያድርገው ብላችሁ አትማሉ፣
   ይቸግር የለም ወይ መሪ ማባበሉ፡፡

7. ኧረ አምሳለ
   ኧረ አምሳለ

   ኧረ ሆይ ኧረ ሆይ

**መልመጃ ሶስት፡-**

ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ከማስታወሻው በታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች ዜማቸውን ጠብቃችሁ አንብቡ፡፡

## ማስታወሻ

### ግጥም እንዴት ይነበባል?

ግጥም የሚዋቀረው ሐረግ በሐረግ ነው፡፡ ሐረጎች ደግሞ ስንኝን ይመሰርታሉ፡፡ ሐረግ በግጥም ውስጥ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ ሲሆን ስንኝ ደግሞ አንድ የግጥም መስመር ነው፡፡ አንድን ግጥም ዜማውን ጠብቀን ለማንበብ የሚከተሉትን መመሪያዎች መተግበር ተገቢ ነው፡፡ እነሱም፡-

- በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆይታ ማድረግ
- ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ
- የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥንና ከሥነ-ጽሑፋዊ መድረኮች ወዘተ. ማዳመጥ
- ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሀዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውደሴ... መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደየግጥሙ ዓይነት እየቀያየሩ ለማንበብ መሞከር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

1. አንድ እንጀራ በእኔ እንዴት ትኮራለህ፣
   ከባለጠጋ ቤት ትነባበራለህ፡፡
2. እባክሽ እናቴ ውለጅ መንታ መንታ፣
   ግራ እጄ ሲመክት ቀኝ እጄ ተመታ፡፡
3. አንበሳው ወይኖ የዋለበቱ፣
   አረገረገ ሸሸ መሬቱ፡፡
4. ተጉዞ ተጉዞ ሰው እንደ ደመና፣
   መመለሻው ጠፉ ያገሩ ጎዳና፡፡

## ክፍል አራት፡- መጻፍ

### መልመጃ አንድ፡-

ከታች የቀረቡትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች አሟልታችሁ ፃፉ፡፡

1. መቅደላ አፋፉ ላይ ጨኸት በረከተ፣

   የሴቱን አናውቅም ወንድ ________________፡፡

2. ስራ እንደኮሶ እየመረረው፣

   ጠቅልሎ መጉረስ ማን ______________________፡፡

3. ብነግድ አንድ ጨው ባርስ አንድ ቁና፣

   እንግዲህ ምን ልበል ______________________ ፡፡

4. የኔማ እመቤት የፈተለቸው፣

   የሸረሪት ድር ______________________________፡፡

5. ሲሰራው ዋለና ሲያንፀው ሲያንፀው፣

   እንደመፋቂያ እንጨት________________________፡፡

6. የኔማ ጌታ የሰጠኝ ሙክት፣

   አንድ ዓመት ሞላኝ__________________________፡፡

### መልመጃ ሁለት፡-

መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሰረት ተመሳሳይ የቃል ግጥሞችን ጽፋችሁ በመምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

## ዘይቤያዊ አነጋገር

### ትዕዛዝ፡-

መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማስታወሻና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ቀጥለው ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ፡፡

1. ከሚከተሉት መካከል አነፃፃሪ ዘይቤ ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. አይኑ የበርበሬ ማስቀመጫ መስሏል፡፡

   ለ. ፊቱ የሐምሌ ሰማይ መስሏል፡፡

   ሐ. ቁመቱ ዝግባ ነው፡፡

   መ. ጥርሶቹ የዛገ ቆርቆሮ መስለዋል፡፡

2. እሱማ ጨዋ ነው ባህሉን አክባሪ፣

   እርቃኑ ቢታይም ለብሶ ትልትል ሱሪ፡፡
   በአመሉስ ቢሆን ከቶ ማን ያማዋል፣
   ቁማር መጠጥ እንጂ ምን ተገኝቶበታል፡፡ ይህ ግጥም የቀረበው በምን አይነት ዘይቤ ነው?

   ሀ. ምፀት ሐ. ተለዋጭ
   ለ. ተምሳሌት መ. ግነት

3. አንቺ ፀሀይ ያየሽውን መስክሪ? ፡፡ ይህ ሀሳብ የቀረበው በምን አይነት ዘይቤ ነው?

   ሀ. እንቶኔ ሐ. ምፀት
   ለ. ግነት መ. አያዎ

4. ሆዴ ረመጥ ነው፡፡ በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተገለፀው የዘይቤ አይነት ነው፡፡

   ሀ. ግነት ሐ. ተለዋጭ
   ለ. ሰውኛ መ. አነፃፃሪ

5. ከሚከተሉት መካከል በሰውኛ ዘይቤ የቀረበው የቱ ነው?

   ሀ. ዓባይ የሀገር ኩራት ነው ሐ. ሀገር ትጣራለች
   ለ. እናት ኢትዮጵያ መ. አልማዝ ተኮራምታ ቁጭ አለች

6. የገዛሁት እንጀራ እፍ ቢሉት ወንዝ ይሻገራል፡፡ ይህ ሀሳብ የቀረበበት የዘይቤ አይነት ከሚከተሉት መካከል የቱ ነው?

   ሀ. ሰውኛ ሐ. ተምሳሌት
   ለ. እንቶኔ መ. ግነት

7. ሰውዬው የቀን ጅብ ነው፡፡ ይህ አረፍተ ነገር በየትኛው ዘይቤ የተገለፀ ነው?

   ሀ. በምፀት ሐ. በእንቶኔ
   ለ. በግነት መ. በተለዋጭ

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### መልመጃ አንድ፡-

ቀጥለው በሳጥኑ ውስጥ የቀረቡትን አያያዦች በመጠቀም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቢሆንም | እንደ | ነገር ግን |
| ይሁን እንጂ | ስለ | በተጨማሪም |

1. ትዕግስት ከትምህርት ቤት ______________ተመለሰች እጇን ታጠበች፡፡
2. የእንቦጭ አረምን ለማጥፋት ህዝቡ ርብርብ እያደረገ ____ የተፈለገውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም፡፡
3. አሁን የጥናት ሰዓት ----- ደረሰ ቴሌቪዥን መዘጋት አለበት፡፡
4. ያሲን ጠንክሮ አንብቦ ነበር፤____________ ጥሩ ውጤት አላመጣም፡፡
5. ኳስ መጫወት እወዳለሁ _______ በኮሮና ምክንያት አልተሳካልኝም፡፡
6. ጓደኛዬ ከትምህርቱ ____________ የቀን ስራ ይሰራል፡፡

## መልመጃ ሁለት፡-

እስካሁን ስለውስብስብ ዓረፍተ ነገር በተማራችሁት መሰረት አያያዥ ቃላትን በመጠቀም አምስት ውስብስብ አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በዚህ ምዕራፍ ስለ ቃላዊ ግጥም ምንነትና አይነቶች፣ የግጥም አነባበብ ዘዴ፣ የግጥም ቃላት እንዲሁም ስለዘይቤና የዘይቤ አይነቶች ተምረናል፡፡
- ቃላዊ ግጥም ሰዎች ጽሕፈትን መጠቀም ከመጀመራቸው በፊት ስሜታቸውንና ፍላጎታቸውን ሲያንፀባርቁበት የኖረ አሁንም በማገልገል ላይ የሚገኝ ቃላዊ የህዝብ ሀብት ነው፡፡ የቃላዊ ግጥም አይነቶች በርካታ ቢሆኑም የሰርግ፣ የስራ፣ የሀዘን ወዘተ. ተጠቃሽ ናቸው፡፡
- አንድን ግጥም ዜማውን ጠብቀን ለማንበብ በሐረጎችና በስንኞች መጨረሻ የተወሰነ የጊዜ ቆይታ ማድረግ፣ ግጥሙን በተገቢ ዜማዊ ቃና ማንበብ፣ የተለያዩ የግጥም አነባበብ ስልቶችን ከመምህራን፣ ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥንና ከሥነ-ጽሑፋዊ መድረኮች ወዘተ. ማዳመጥ፣ ግጥሙ የቅስቀሳ፣ የሀዘን፣ የግርምት፣ የትዝብት፣ የውደሴ… መሆኑን በማጤን የአነባበብ ለዛውን እንደየግጥሙ ዓይነት እየቀያየሩ ለማንበብ መሞከር የሚሉ መመሪያዎችን መከተል አስፈላጊ ነው፡፡
- ዘይቤ (ዘይቤያዊ ንግግር) የምናስተላልፈው መልዕክት ምስል በመፍጠር መልዕክቱ ጎልቶ፣ አምሮና ደምቆ እንዲታይ የምንጠቀምበት የቋንቋ አጠቃቀም አይነት ነው፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

8. ከታች የቀረቡትን ቃላዊ ግጥሞች አይነት ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. አይዞሽ ሙሽሪት አይበልሽ ከፋ፣

ሁሉም ያገባል በየወረፋ፡፡

ለ. በጠፍጣፋ ድንጋይ ከተዘጋ በሩ፣

እናት አትገኝም እንደወፍ ቢበሩ፡፡

ሐ. ፎጣ መጠምጠም ራስ ይመልጣል፣

ሽንጥን ገትሮ ማረስ ይበልጣል፡፡

መ. ዱብ ዱብ ይላል እንደ በረዶ፣

በልጅነቱ በረሃ ለምዶ፡፡

9. ቀጥለው በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የዘይቤ አይነቶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ከቸኮልክ አትደረስም ብሎ መከረኝ፡፡

ለ. ጠይባ እንደ ንብ ታታሪ ናት፡፡

ሐ. ለሰው ሞት አነሰው አለች ቀበሮ፡፡

መ. የአባቴ ፈረስ ከመኪና ይፈጥናል፡፡

ሠ. ዘነበ አንበሳ ነው፡፡

### የቃላት መፍቻ

| ቃላት | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሃቅ | እውነታ |
| ህልም | በእንቅልፍ የሚታይ፣ራዕይ፣ ምኞት |
| መና | ከንቱ፣ ብልሹ (ሲላላ)፣ ህብስት፣ ምግብ (ሲጠብቅ) |
| መዛመት | መሰራጨት |
| መኾገር | በከብት ላይ ጥገኛ የሆነ ነፍሳት፣ መንቻካ፣ በዝባዥ |
| መደለያ | ማባበያ |
| ሙግት | ክርክር፣ ንትርክ፣ ጭቅጭቅ |

| | |
|---|---|
| ሰለባ | ተጠቂ፣ ተጎጂ |
| ሰርክ | ዘወትር (ሁልጊዜ) |
| ሰናይ | መልካም |
| ስራ ፈት | ስራ የሌለው |
| ረባዳ | ጎድጓዳ (ዝቅተኛ) ቦታ |
| ራዕይ | ወደ ፊት ሊሰራ የታሰበ እቅድ |
| ሸንጎ | ጉበኤ፣ ስብሰባ፣ ዳኝነት የሚሰጥበት ቦታ |
| በነቂስ | በሞላ፣ በሙሉ፣ አንድም ሳይቀር |
| ባልንጀራ | ጓደኛ |
| ባልደረባ | አብሮ የሚሰራ፣ የስራ ጓደኛ |
| ብሂል | አባባል፣ መርህ |
| ነፍስ ወከፍ | እያንዳንዱ፣ በየራሱ |
| አሉባልታ | የውሸት ወሬ |
| አመርቂ | አጥጋቢ |
| አንባ | መንደር፣ ተራራ |
| አሪ | የአፋር ህዝብ ባህላዊ የቤት አሰራር |
| አርነት | ነፃነት |
| አዘቦት | የስራ ቀን |
| አፍላ | ወጣት |
| እንብርት | መሃል |
| እንቅፋት | መሰናክል፣ እግርን የሚያደነቅፍ |
| ወጌሻ | ስብራትን፣ ውልቃትን የሚጠግን ባለሙያ |
| ዋዜማ | ከበዓል በፊት ያለው ቀን |
| ውለታ | አንዱ ለሌላው የሚያደርገው መልካም ስራ |
| በኩር | የመጀመሪያ |
| ገድል | የአንድ ግለሰብ ስራ፣ ጀብዱ |
| ገፀ-በረከት | ስጦታ |
| ፈርጅ | ክፍል ወይም ረድፍ |

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች ከነፍቻቸው | |
|---|---|
| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
| ሃሞቱ ፈሰሰ | ሰነፈ |
| ሆደ ባሻ | ቶሎ የሚከፋው |
| ልባም | ብልህ፣ አስተዋይ |
| ልብ አቁስል | ጨቅጫቂ፣ ነዝናዛ |
| ሳር ቅጠሉ | ሁሉም |
| ቂም አረገዘች | ተቀየመች |
| አመድ አፋሽ | በደግነቱ የማይመሰገን |
| አቅመ ቢስ | ደካማ |
| አይኑ ቀላ | ተናደደ |
| አይን አውጣ | ደፋር፣ ባለጌ |
| አግሬ ደረቅ | እድለ ቢስ |
| አፈ ቅቤ | ክፉ ነገር የማይናገር፣ አታላይ |
| የውሃ ሽታ | አድራሻው የማይታወቅ |
| ጮቤ ረገጠ | ተደሰተ |

# ዋቢ ጽሑፎች


መስፍን ሀብተማሪያም፡፡ 1983፡፡ አውደ ዓመት፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ማርታ እሸቱ፡፡ 2007፡፡ ኩራዝ አማርኛ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ ኢንተርሽናል አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሰለሞን ሐለፎም፡፡ 1997፡፡ የድርሰት አፃፃፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

ሰለሞን ጥላሁን እና ስምረት ገብረ ማሪያም፡፡ 2000፡፡ ደማቆቹ የአንዳንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊያን የሕይወት ውልብታ፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፣ ጥር 18 ቀን፣ ቅፅ 19 ቁጥር 1434፣ 2006 ዓ.ም፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፣ መስከረም 18 ቀን፣ ቅጽ 25 ቁጥር 2026፣ 2012 ዓ.ም፡፡

ባየ ይማም፡፡ 2002፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ብላቴን ጌታ ማህተመ ስላሴ ወልደ መስቀል፡፡ ስብስብ ስራዎች፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ተምሳሌት እፁብ ድንቅ ኢትዮጵያዊያን ሴቶች፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት፡፡ 2007፡፡ አዲስ አበባ፣ ፀሀይ አሳታሚና አከፋፋይ ድርጅት፡፡

ታለጌታ ይመር፡፡ 2007፡፡ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማሪ አጋዥ መፅሀፍ ከ7ኛ-10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለም እሸቱ፡፡ 1999፡፡ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7ኛ- 10ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፡፡

አለምሀይ ወዳጆ፡፡ 2009፡፡ የማታ እንጀራ የግጥም መድብል፡፡ አዲስ አበባ፣ ፋርኢስት ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡፡

አብዱ ራህመቶና ንጉሴ አየለ፡፡ 1979፡፡ ሙሽራው፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ሐምሌ 25/2013 ዓ.ም፡፡

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ ቁጥር 285፣ ሰኔ 15/2011 ዓ.ም፡፡

ኢካሽ 25ኛ ዙር የጋዜጠኝነት ሰልጣኞች መጽሄት፡፡ የካቲት 2013 ዓ.ም፣ ኖቫ ማተሚያ ቤት፡፡

ኤ.ሲ.ፒ. ኤሲ የትምህርት ቦርድ የት/ቤት የበጎ ፍቃደኞች መመሪያ ማኑዋል፡፡

ከበደ ሚካኤል፡፡1961፡፡ ብርሃነ ህሊና፡፡ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ወይ አዲስ አበባ መፅሄት፣ ቅፅ 1፣ ቁጥር8፣ 2013ዓ.ም፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ 1992፡፡ የሥነጽሑፍ መሠረታውያን፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዝክረ ህዳሴ አዲስ አበባ መጽሄት፣ 2013 ዓ.ም፡፡

የሻው ተሰማ፡፡ 1996፡፡ ልሳነ-ብዕር ከመልሳነ ሰብእ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት የታተመ፡፡

የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፡፡ የ2006 ዓ.ም በጀት ዓመት ሪፖርት፡፡

ደበበ ኃይለ ጊዮርጊስ፡፡ 1999፡፡ አማርኛ አጋዥ መጽሀፍ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት

ጂ አይ ዜድ (GIZ) የጀርመን የተራዶ ድርጅት፣ 2020 እ.ኤ.አ የታተመ፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡ 2008፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ጠና ደዎ፡፡ 20008፡፡ ሰው፣ ግብረገብና ሥነ-ምግባር የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕረስ፣ ኢክሊፕስ ማተሚያ ቤት፡፡

## የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 | |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 | |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 | |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | | |